## ማውጫ


**መግቢያ** .......... i

**ክፍል አንድ፡ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት ለምን?** .......... 9

1.1 ማህበራዊ ጥበቃ ምንድን ነው? .......... 9

1.2 . የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት አስፈላጊነት/ አመክንዮ .......... 13

1.3. ዘላቂ ስርዓትን መገንባት .......... 13

**ክፍል ሁለት መነሻ ሐሳብ (ዳራ)** .......... 15

2.1. ልማት እና የፖሊሲ ተጨባጭ ሁኔታ .......... 15

2.2. ድህነት እና የተጋላጭነት ሁኔታ .......... 19

2.3. ለድህነትና ተጋላጭነት ምላሽ መስጫ ሥልቶች .......... 20

2.3.1. ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ ስልቶች .......... 20

2.3.2. መደበኛ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች .......... 22

2.4. ባለድርሻዎች .......... 29

2.6. የተገኙ ትምህርቶች .......... 31

**ክፍል ሦስት፡- ስትራቴጂካዊ ማዕቀፍ** .......... 34

3.1. ሽፋን እና ልየታ .......... 34

3.2 ሁሉን አቀፍ እና የወደፊት ፍላጎትን ያካተተ .......... 36

3.3 ከፕሮገራም ድጋፍ መውጣት/Graduation/ .......... 36

3.4. ተጠያቂነት እና ተግባቦት (ኮሙዩኒኬሽን) .......... 38

3.5 በፆታ፣ እድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት እና ኤች አይቪ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ትኩረት ሰጥቶ ማካተት .......... 39

**ክፍል አራት፡ እስትራቴጂዎችና የማስፈፀሚያ መሳሪያዎች** .......... 41

4.1. ራዕይ፣ ተልእኮና የፖሊስ ዓላማዎች .......... 41

4.2. የትኩረት አቅጣጫ 1፡ ልማታዊ ሴፍቲኔት ማስፋፋት .......... 42

4.3. የትኩረት አቅጣጫ 2፡ የሥራ ዕድልን ማስፋፋትና የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል .......... 45

4.4 የትኩረት አቅጣጫ 3፡ ማኅበራዊ ዋስትናን ማስፋፋት .......... 50

4.5 የትኩረት አቅጣጫ 4፡ ለጤና፣ ለትምህርት እና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ያለውን ፍትሃዊ ተደራሽነት ማሳደግ ........ 52

4.6 የትኩረት መስክ 5፡ ለጥቃት፣ ለብዝበዛ እና ለኃይል ድርጊት ለተጋለጡ ዜጎች ሕጋዊ ጥበቃና ድጋፍ መስጠት ........ 58

4.7. ማጠቃለያ ........ 61

**ክፍል 5 አፈጻጸም (ትግበራ)ና የጊዜ ሰሌዳ** ........ 63

5.1. ተቋማዊ ዝግጅት ........ 63

5.2. የትግበራ አቅሞች ........ 68

5.3 የስርአትዝርጋታ ........ 71

5.4 የጋራ  የክትትል እና ግምገማ ማእቀፍ ........ 74

5.5 የጊዜ ማእቀፍ እና ታሳቢዎች ........ 75

**ክፍል 6: የስትራቴጅው ማስፈጸሚያ የፋይናንስ ጉዳይ** ........ 77

6.1 ለማህበራዊ ጥበቃ በሀገሪቱ የገንዘብ አቅም ውስጥ ያለውን ቦታ መጠቀም ........ 77

6.2 ዋነኛ የፋይናነስ ምንጭ ........ 78

6.3 የፋይናንስ ስትራቴጂ ሲዘጋጅ ታሳቢ ሊሆኑ የሚገባቸው ጉዳዮች ........ 79

1. በማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ውጤታማነትን ማሳደግ፡- ........ 79

6.4 ለማህበራዊ ጥበቃ የፋይናንስ መሰረት ለመፍጠር ሊወሰዱ የሚገባ ቀጣይ እርምጃዎች ........ 80

አባሪ 1 ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ........ 81

ዋቢ ጽሁፎች ........ 96

ህዳግ ማስተዋሻ ........ 101

## ሰንጠረዥ

**ሰንጠረዥ 1 ፡** አራቱ የማህበራዊ ጥበቃ ዓላማዎችን ከትኩረት አቅጣጫዎች ማሳለጥ ........ 11

**ሰንጠረዥ 2፡** የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት ግምት ........ 16

**ሰንጠረዥ 3፡** የድህነት ተጋላጭነት አቅጣጫዎች........ 19

**ሰንጠረዥ 4፡** የማህበረሰብ እንክብካቤ ሕብረት ብዛት በክልል........ 21

**ሰንጠረዥ 5፡** ለትኩረት አቅጣጫዎች ቁልፍ ማስፈጸሚያ መሳሪያዎች ሆነው የተለዩ፤........ 41

**ሰንጠረዥ 6፡** አመልካች ድጋፎችን ብሄራዊ ጥበቃ ፖሊሲው ከለያቸው ተጋላጭ ህብረሰብ ክፍሎ ........ 62

**ሰንጠረዥ 7 ፡** የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት ተግባራዊነት የጊዜ ማእቀፍ እና ታሳቢዎች ማሳያ........ 75

## ምህፃረ ቃላት

| | |
|---|---|
| ማአጤመዋ | ማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድን ዋስትና |
| ማአድ | ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅት |
| የጋተምሥ | የጋራ ተጠቃሚ ምዝገባ ሥርዓት |
| ማአእጥ | የማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት |
| ማዕስባ | ማዕከላዊ ስታትስቲክሰ ባለሥልጣን |
| ሲማድ | ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች |
| አሥመ | የአደጋ ሥጋትን መቋቋም |
| ኢጠኢኤ | የኢትዮጵያ ጤና ኢንሹራንስ ኤጀንሲ |
| ትመ | የትኩረት መስክ |
| ፌጥአኢልኤ | ፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ |
| ፌማጥም | ፌዴራል ማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት |
| ዕትዕ | ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ |
| ቤጥግፕ | ቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ፕሮግራም |
| መመሰኢ | መለኪያን መሰረት ያደረገ የሰብል ኢንሹራንስ |
| መመእኢ | መለኪያን መሰረት ያደረገ የእንስሳት ኢንሹራንስ |
| ቀማጥም | የቀበሌ ማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት |
| አፋተ | አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት |
| መሥአ | የመረጃ ሥርዓት አስተዳደር |
| እተሃሚ | የእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር |
| ትሚ | ትምህርት ሚኒስቴር |
| ገኢትሚ | ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር |
| ጤጥሚ | የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር |
| ፍሚ | የፍትህ ሚኒስቴር |

| | |
|---|---|
| እአሃሚ | የእንስሳትና አሣ ሃብት ሚኒስቴር |
| ሠማጉሚ | የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር |
| ከልቤሚ | የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር |
| ጥአኢ | ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ |
| መያድ | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች |
| ተሀሥአዳ | የተፈጥሮ ሀብቶች ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት |
| ብማጥፖ | ብሄራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ |
| ብማጥኤ | ብሄራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ኤጀንሲ |
| እተህ | እጓለሞታ እና ተጋላጭ ህፃናት |
| አአማልፕ | አርብቶ አደር ማህበረሰብ ልማት ፕሮግራም |
| ኤች አይቪሚሰ | ከኤች አይቪ ጋር የሚኖሩ ሰዎች |
| ግድሠማዋኤ | የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ |
| ፓማጉቋኮ | የፓርላማ ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ |
| መዘማዋኤ | የመንግስት ዘርፍ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ |
| ልሴፕ | ልማታዊ ሴፍቲኔት  ፕሮግራም |
| አጉ | አካል ጉዳተኞች |
| ክማጥም | የክልል ማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት |
| ገቁብህማ | የገጠር ገንዘብ ቁጠባና ብድር የህብረት ሥራ ማህበራት |
| ማጤኢ | የማህበራዊ ጤና ኢንሹራንስ |
| አመኢ | አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ |
| ግምሥ | የግል ምዝገባ ሥርዓት |
| ቴሙትሥ | የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና |
| ሁአመተፕ | ሁሉን አቀፍ መንገዶች ተደራሽነት ፕሮግራም |
| ወማጥም | ወረዳ ማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት |

***መግቢያ***

የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት ካለፉት አሥር ዓመታት ጀምሮ በአማካይ በዓመት ከ10 በመቶ በላይ በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን ቀጣይነት ያለው ዕድገት በመመዝገብ ላይ ቢሆንም፤ በህዝብ ቁጥር መጨመር እና ለተለያዩ የአደጋ ክስተቶች የተጋላጭነት መጠን በመጨመሩ በፍጹም ድህነት ውስጥ የሚኖሩት ሕዝቦች የቀነሰበት ቁጥር አመርቂ አይደለም፡፡ ይህም ከ24.4 ሚሊዮን ወደ 24.3 ሚሊዮን ብቻ ነው፡፡ ይህ የእስትራቴጂ ሰነድ እየተዘጋጀ ባለበት (2007/2008 ዓ.ም) በኤልኒኖ ክስተት ምክንያት ወደ 10.2 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ለጉዳት ተጋልጠው የምግብ ዕርዳታ ፈላጊ ሆነዋል፡፡ አሁንም በኢትዮጵያ 40 በመቶ የሚሆኑ ህፃናት ሥር በሰደደ የስነምግብ ችግር የተጎዱ ናቸው፡፡ ይህም በህፃናቱ የአካልና የአእምሮ ዕድገት ላይ በህይወት ዘመናቸው ሙሉ ሊቀለበስ የማይችል ተፅዕኖ የሚያሣድር በመሆኑ የተለየ ትኩረት ይሻል፡፡ ከዚህ እውነታ አንፃር ሁለተኛው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (GTP-II, 2007/2008፡4) መንግስት ለሚቀጥሉት ዓመታት የድህነትን፤ የሥራ አጥነትን እና የኋላ ቀርነት ተግዳሮቶችን በከፍተኛ ደረጃ ለመፍታት ሁሉን-አቀፍ እና ድሀ ተኮር የልማት ስትራቴጂን መከተል እንደሚገባ ቁርጠኝነቱን አረጋግጧል፡፡

ማህበራዊ ጥበቃ ሁሉን-አቀፍ እና ድሀ ተኮር እድገትና ልማትን ከሚያስፋፉ ዓበይት መንገዶች/መሳሪያዎች መካከል አንዱ መሆኑን መንግስት ተገንዝቧል፡፡ ከዚህ አኳያ ብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ (ብማጥፓ) ተቀርፆ "***የኢትዮጵያ ዜጎች ሁሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነትና ዋስትና ተጠብቆ፤ ማህበራዊ ፍትህ ሰፍኖ የማየት***" ራዕይ ይዞ ፀድቋል፡፡ ፖሊሲው አምስት የተቀናጁ የትኩረት አቅጣጫዎችን እንደ እስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች ለይቶ አስቀምጧል፡፡
እነርሱም፡-

- **ልማታዊ ሴፍቲኔትን ማስፋፋት፡-** ድሀና ተጋላጭ ቤተሰቦች የምግብ ፍጆታቸው እንዲጨምር፤ ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶች እንዲመቻቹላቸው፤ ውጤታማ ሥራ ላይ የሚውል መዋዕለ-ንዋይ እንዲያፈሩ የገንዘብ ወይም የምግብ ድጋፍ ያገኛሉ፡፡ ይህ ድጋፍ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ሁኔታ፤ የአገልግሎቶቹ ዓይነቶች መኖርና አለመኖር እንዲሁም በአገልግሎት ጥራት ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል፡፡
- ***የሥራ ዕድልን ማስፋፋት እና የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል*** **፡-** ፍላጎትን መሠረት በማድረግ ለድሀ ቤተሰቦች የቴክኒክ፤ የገንዘብ እና በሥራ ዕድሎች ላይ መረጃ እንዲያገኙ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ ይህም የኑሮ ሁኔታን ለማሻሻል በእርሻ ላይ እና ከእርሻ ውጭ የተመሰረቱ የኑሮ ሁኔታቸውን ለማሻሻል ያስችላቸዋል፡፡
- ***የማህበራዊ መድንን ማስፋፋት፡-*** ለመደበኛ ዘርፍ ሰራተኞች አስገዳጅ የመድን ዋስትና ማስፋፋት፣ ለገጠር ድሀ እና በከተማ መደበኛ ባልሆኑ ዘርፎች ላይ ለተሰማሩ ሠራኞች ተስማሚ የሆኑ የመድን ዋስትና ስርዓት መዘርጋት የሚያጋጥማቸውን ስጋት እንደ አመጣጡ በተሻለ ሁኔታ ለማስተናገድና ለመቆጣጠር ያስችላቸዋል፡፡
- ***የመሠረታዊ አገልግሎቶች ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ*** **፡-** አካል ጉዳተኞች፣ ነፍሰ-ጡሮች እና የሚያጠቡ እናቶች ከክፍያ ነጻ የጤና አገልግሎት የጤና መድን ድጎማ እና እንዳስፈላጊነቱ ልዩ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፡፡ የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራሞች የማህበራዊ ሥራ ስርዓትን ከማስፋፋት ጋር ተዳምረው በከፍተኛ ደረጃ ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች የአገልግሎቶች ተደራሽነትን ያሻሽላል፡፡

- **ለጥቃትና በደል ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎች የሕግ ጥበቃና ድጋፍ መስጠት፡-** ጥቃትን፣ በደልን እና ብዝበዛን አስቀድሞ መከላከል እና ከተከሰተም በኃላ ተገቢውን ምላሽ በመስጠት በህብረተሰቡ ውስጥ ውሳኔ ሰጭነትን የተነፈጉ እና የተገለሉ የህብረተሰብ አካላትን ከሚደርስባቸው ጥቃት፣ በደል እና ብዝበዛ ለመከላከል እና ለማብቃት ያስችላል፡፡

**በብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ እንደተቀመጠው የማህበራዊ ጥበቃ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-**

- ለድህነትና ለተለያዩ ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ግለሰቦች፤ ቤተሰቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ለከፋ ችግር እንዳይጋለጡ መጠበቅ፤
- የማህበራዊ መድን ሥርዓትን ተደራሽነት ማሳደግ፤
- ፍትሃዊና ጥራት ያለው የጤና፤ የትምህርትና የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎቶችን ማሳደግ፤ የሰው ሀብት ልማትን ማሳደግ፤ ብሎም ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ ያለውን ድህነት ማስቆም፤ በማህበራዊ ችግር ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን የኑሮ ሁኔታ ደረጃ በደረጃ በማሻሻል የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶቻቸውን ማስጠበቅ፤
- በደልን፤ ጥቃትን፤ ማግለልንና ልዩነት ማድረግን መከልከል እና አስፈላጊውን ምላሽ መስጠት፤
- የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲን ለመተግበር ሕብረተሰቡ በየደረጃው ተገቢ ሚናውን እንዲወጣ ማድረግ ናቸው፡፡

በእቅድ ላይ የተመሰረተ ድጋፍ ማድረግ ጠቃሚ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ያለው ሲሆን ለሁለተኛው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2ኛው ዕትዕ) ዓላማዎች ግብ መምታት ሁነኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ አምስቱ የትኩረት አቅጣጫዎች በአንድ ላይ ተዳምረው ሲቀናጁ በመካሄድ ላይ ላለው የማህበራዊ ሽግግር/ ትራንስፎርሜሽን/ ተጨማሪ አቅም ይፈጥራሉ፡፡ ማህበራዊ ሽግግር ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገለፅ የለውጥ ሂደት ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰት የእያንዳንዱን ዜጋ ሕይወት የሚነካ ነው፡፡ የማህበራዊ ጥበቃ ስትራቴጂው የድሆችን፣ የተገለሉ እና የተረሱ የህብረተብ ክፍሎችን ፍላጎት በማሟላት ይህንን ሂደት ለማፋጠን አስተዋጽኦ ያደረጋል፡፡ ይህንን ማሟላት ካልተቻለ ግን ከትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ውጪ ያደረጋል፡፡

የማህበራዊ ጥበቃ ትግበራ የገቢ ማስገኛዎችን በማስፋፋት ለምግብ፣ ለጤና እንክብካቤ እና ለትምህርት የሚሆን ገቢ በማስገኘት ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ በድህነት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ እዲሳተፉ፤ የእድገቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑና እየበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያደርጋቸዋል፡፡ ማህበራዊ ድጋፍ /social transfers/ በድህነት ውስጥ ያሉ ቤተሰቦችን ድህነት በመቀነስ ረገድ ቀጥተኛ ተጽእኖ ያለው ሲሆን በኢኮኖሚው ውስጥ በመዘዋወር የዕቃዎችን እና የአገልግሎቶችን ፍላጎት በመጨመር ሰፊ የኢኮኖሚ አስተዋጽኦ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

**የስትራቴጂው ቀረፃ ሂደት፡-** የስትራቴጂው ቀረጻ ለፖሊሲ ዝግጅትተደርጎ የነበረው የማህበራዊ ጥበቃ ዳሰሳ እና ትንተና ተከትሎ የመጣ ነው፡፡ ከዚሁ ሂደት የተገኙ ግኝቶችም በሀገር አቀፍ ደረጃ በማህበራዊ ጥበቃ ዙሪያ የውይይት መድረክ እንዲካሄዱ አነሳስተዋል፡፡ እነዚህ መድረኮችም ለብሄራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲው ከሁሉም ክልሎች ጠቃሚ ሀሳቦች እንዲመነጩ መሰረት ጥለዋል፡፡ ሂደቱንም ለመምራት ሁሉን አቀፍ የባለድርሻ አካላት ብሄራዊ የጋራ መድረክ ተቋቁሟል፡፡ የዚህ የጋራ መድረክ አባላትም መንግስት፣ የልማት አጋሮች፣ የተ.መ.ድ ኤጀንሲዎች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሲሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ በማህበራዊ ጥበቃ አቅርቦት ዙሪያ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ናቸው፡፡ የስትራቴጂው ቀረፃ ሂደት በፖሊሲው ከተቀመጡት አምስት የትኩረት አቅጣጫዎች ዙሪያ ከተዘጋጁ ስነ-ጽሁፋዊ ቅኝቶች እና የተዘገቡ መልካም ተሞክሮዎችን

በመቀምር  እንደ ግብዓት ተጠቅሟል፡፡ እንዲሁም በወቅቱ በመካሄድ ላይ ከነበሩት የገጠር እና የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች ዝግጅት የተገኙ ልምዶችን እንደ ግብዓት ተጠቅሟል፡፡ በስትራቴጂው ቀረፃ ሂደት በተለያዩ ደረጃዎች ተከታታይ የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረኮች የተዘጋጁ ሲሆን፤ በማጠቃለያውም የሂደቱን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ብሄራዊ አውደ ጥናት ተካሂዷል፡፡

**የስትራቴጂ ሰነዱ አወቃቀር ፡-** ይህንን መግቢያ ተከትሎ ሰነዱ ስድስት ክፍሎች አሉት፡፡

**ክፍል 1** የማህበራዊ ጥበቃን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በመተርጎም ይጀምራል፡፡ እንዲሁም የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት አስፈላጊነትን ያሳያል፡፡ በብሄራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲው አምስት የትኩረት አቅጣጫዎች እርስ በርሳቸው እና ከአራቱ የማህበራዊ ጥበቃ ውጤቶች (ጥበቃ፤ መከላከል፤ ማስፋፋት እና ሽግግር ማምጣት) ጋር ያላቸውን ትስስር ያሳያል፡፡

**ክፍል 2** የኢትዮጵያን የእድገት፤ የድህነትን እና የተጋላጭነት ሁኔታን በመተንተን ያቀርባል፡፡ በተጨማሪ የስትራቴጂው የትኩረት አቅጣጫዎችና የማስፈጸሚያ መሳሪያዎች ለምን እንደተመረጡ ያስረዳል፡፡

**ክፍል 3** የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓትን ለመቀረጽ አግባብነት ያላቸውን የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ያብራራል፡፡

**ክፍል 4** በእያንዳንዱ የትኩረት አቅጣጫ ቁልፍ የማስፈጸሚያ መሳሪያዎችንና የድጋፍ አሰጣጦችን ያቀርባል፡፡

**ክፍል 5** በሚቀጥሉት 10 ዓመታት የሚካሄዱ ዋና ዋና ተግባራትን የጊዜ ሰሌዳ በጥቅሉ ያቀርባል፡፡ ሁሉን አቀፍ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር በአቅም ግንባታና በሥርዓት ቀረፃ ላይ የሚተገበሩ ተግባራትን ለማቀላጠፍ የሚጠበቁ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን ያብራራል፡፡

**ክፍል 6** ለማህበራዊ ጥበቃ የገንዘብን አስፈላጊነት ይገልፃል፡፡ ለእስትራቴጂው በገንዘብ ረገድ መደረግ የሚገባቸውን ድጋፎች የሚመለከቱ ጉዳዮችን በጥቅሉ ይመለከታል፡፡ ፡፡ ዋና ዋና የገንዘብ ምንጮችንም ይዘረዝራል፡፡

## ክፍል አንድ፡ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት ለምን?

### 1.1 ማህበራዊ ጥበቃ ምንድን ነው?

ማህበራዊ ጥበቃ እንደ የሀገሩ ሁኔታ እና ሙያዊ ዝንባሌን መሰረት በማድረግ በተለያየ ሁኔታ ይተረጎማል[55]፡፡ ማህበራዊ ጥበቃ በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ድህነትን፣የዜጐችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስጋት፣ ተጋላጭነትን እና መገለልን ለመቀነስ የሚያስችል እርምጃ በመውሰድ ለሁሉም ተደራሽ የሆነ የተመጣጠነ እድገት በማረጋገጥ ላይ የሚያተኩር የማህበራዊ ፖሊሲ ማዕቀፍ አካል ነው፡፡ እንዲሁም የእድገት ውጤቶች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በዕኩልነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመውሰድ የአደጋን ስጋት፣ ተጋላጭነት እና በደልን በመቀነስ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራት ማከናወንን ይጠይቃል፡-

- የማህበረሰብ አቀፍ  የድጋፍ ስልቶችን ማጠናከርና ከማህበረሰቡ ጋር መስራት፤
- መሰረታዊ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ለማሳደግ ማህበራዊ ድጋፍ  ማድረግ፤
- የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎቶችን ሽፋን ማስፋፋት፤
- ገቢ የሚያስገኙ የስራ እድሎችን ማሳደግ፤ድሃና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በሃገሪቱ ዕድገት በእኩልነት መጠቀማቸውን የሚያረጋግጡ አግባብነት ያላቸውን ህጎች፤ መመሪያዎችና የድርጊት መርሃ ግብር እና ተቋማዊ አደረጃጀቶችን ማጠናከር፤

የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት፤ የጥበቃ፣ የመከላከል፤ የማስፋፋት እና የለውጥ/ሽግግር ማምጣት ስርዓት ነው፡፡ እነዚህ አራት የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት መገለጫዎች በመካከላቸው አንዳንድ የመደራረብና የመደጋገም ሁኔታ ቢኖራቸውም፤ ከዚህ በታች እንደተገለፀው አንዳንድ የሚለያዩበት ገጽታዎችም አሏቸው፡፡

የማህበራዊ ጥበቃ ድጋፎች፤ በከፋ ድህነት ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ከረሀብ እና ከድህነት ከሚመነጩ መሰረታዊ አገልግሎቶች የተደራሽነት እጥረትን ጨምሮ ሊያጋጥሟቸው በሚችሉ የተባባሱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች እንዳይጋለጡ ይከላከላሉ፡፡ ከእነዚህ እጦቶች ዜጎችን መከላከል በተለይ በህይወት ዑደት ውስጥ ወሳኝ በሆኑት በእርግዝና፣ በህጻንነት እና በጉርምስና ጊዜ እጅግ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች በእድሜ መግፋት ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት ሥራ መሥራትና  ገቢ ለማመንጨት ባለመቻላቸው ምክንያት <u>**ጥበቃ**</u> ያስፈልጋቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላትና ረሀብን ለመቀነስ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ወይም ያለቅድመ ሁኔታ  የሚሰጥ የጥሬ ገንዘብ እና/ወይም የምግብ  ዕርዳታ/ድጋፍ ማድረግ ወሳኝ  ነው፡፡

ማህበራዊ ጥበቃ፣ ድሃና ተጋላጭ ቤተሰቦች በዘልማድ ችግሮችን መቋቋሚያ ዜዴ አድርገው ከሚጠቀሙባቸው ጎጂ ልምዶች <u>**ይከላከላል**</u>፡፡ ለምሳሌ የምግብ መጠንን በመቀነስ፤ ልጆችን ከት/ቤት በማስወጣት ወይም በችግር ጊዜ ምርታማ ጥሪቶቻቸውን መሸጥ ከመሳሰሉት ይከላከላል፡፡ የገንዘብ ድጋፍ መኖር ወይም የመድን ዋስትና ክፍያ መክፈል ቤተሰቦች ምግብ እንዲያገኙ፤ ገቢ እንዲኖራቸው፤ የጤና አገልግሎቶች ተደራሽ እንዲሆኑላቸው በማድረግ እና በሰው ሃብት ካፒታል ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ በማስቻል ጎጂ የኑሮ ሁኔታ ማሸነፊያ ዘዴዎችን  ያስቀራል ፡፡

ማህበራዊ ጥበቃ፣ የኑሮ ሁኔታንና እና የስራ እድሎችን በማበረታታት ሀብት (ጥሪት) በመያዝ እና ክህሎት በማዳበር ድሃ የህብረተሰብ ክፍሎች በዘላቂነት ከድህነት የሚወጡበትን መንገድ ያሳድጋል፡፡ የማህበራዊ ጥበቃ ለውጥ የማምጣት ሚናው፤ ተጋላጭና የተገለሉ የህብረተሰቡን ክፍሎችን በኢኮኖሚ በማጠናከርና እና መብቶቻቸውን በመጠበቅና በማስጠበቅ በደልንና ጥቃትን መከላከል ነው፡፡ አብዛኛው የማህበራዊ ማስፈጸሚያ መሳሪያዎች በእነዚህ አቅጣጫዎች ዙሪያ ውጤት ያላቸው ናቸው፡፡ አስፈላጊና ትርጉም ያለው ለውጥ የማምጣት ሚናም አላቸው፡፡ በዚህ እስትራቴጂ የተቀመጡትን አምስቱንም የትኩረት አቅጣጫዎች አፈጻጸም በማሳለጥ ከአቅጣጫዎቹ አኳያ አዎንታዊ ውጤቶችን ያሳድጋል፡፡ ***ሰንጠረዥ 1*** በአምስቱ የትኩረት አቅጣጫዎች በመጠበቅ፣ በመከላከል፣ በማስፋፋት እና እመርታዊ ለውጥ/ሽግግር በማምጣት ረገድ እጅግ በጣም አስፈላጊ ውጤቶችን ያስቀምጣል፡፡

የትኩረት አቅጣጫዎቹ በጋራ የሚታዩ እንጂ የሚነጣጠሉ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ በትኩረት አቅጣጫ 1 የተለዩ ደሃ ቤተሰቦች በማንኛውም ሁኔታ ጉዳት ቢደርስባቸው እና መብታቸው ቢጣስ በትኩረት አቅጣጫ 5 የተጠቀሱት ድጋፎች ተደራሽነት ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡ በተመሳሳይ በሥራና በኑሮ ሁኔታ እንቅስቃሴዎች ላይ የተሰማሩ የሴቶችና የወጣቶች ቡድኖች (የትኩረት አቅጣጫ 2) የሚያጋጥማቸውን የመሰናከል ስጋት ለመቀነስ የማህበራዊ መድን ያስፈልጋቸዋል (ትኩረት አቅጣጫ 3)፡፡ ይህ መስተጋብር እስትራቴጂ ለመቅረፅና የድርጊት መርሃ ግብር ለማዘጋጀት እንዲሁም እስከታችኛው የህብረተሰብ እርከን ድረስ በመቅረብ መርሃ ግብር ለመንደፍ አስፈላጊ ነው፡፡

ሰንጠረዥ 1 ፡ አራቱ የማህበራዊ ጥበቃ ዓላማዎችን ከትኩረት አቅጣጫዎች ማሳለጥ

| ትኩረት አቅጣጫ (ትአ 1) | ከህብት (ጥሪት) መሟጠጥ መጠበቅ | ከህብት (ጥሪት) መሟጠጥ ከባሰ ድህነት መከላከል | የኑሮ ሁኔታን ማስፋፋት | የኑሮ ሽግግር ማድረግ/ ለውጥ ማምጣት |
|---|---|---|---|---|
| ትአ 1፡- ልማታዊ ሴፍቲኔትን ማስፋፋት | ማህበራዊ ድጋፍ የምግብ ዋስትናን ያሻሽላል፣ ለአስፈላጊ አገልግሎቶች ተደራሽ ያደርጋል፡፡ | በችግር ጊዜ፣ ማህበራዊ ድጋፍ በአደጋ ምክንያት የህይወት መጥፋት ንብረት (ጥሪት)፣ ማጣትን ይከላከላል፡፡ በህፃናት ላይ በምግብ እጥረት ምክንያት በህይወት ዘመናቸው ሊመለስ የማይችል ጉዳት እንዳይደርስባቸው ይከላከላል፤ ህፃናት በችግር ምክንያት ከቤተሰቦቻቸው እንዳይለዩ ይከላከላል፤ | ምርታማ ኢንቨስትመንቶችን በማስፋፋት፣ ማህበራዊ ድጋፍ የኑሮ ሁኔታን ያሳድጋል፡፡ | ማህበራዊ ድጋፍ ሴቶችን እና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን በገንዘብ እና ምግብ ላይ ያላቸውን ቁጥጥር በማሳደግ አቅምንና ብቃትን ያሳድጋል፡፡ |
| ትአ 2፡ የሥራ ዕድልን ማስፋፋትና የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል | | | ተስማሚ ተደርጎ የሚዘጋጅ ድጋፍ የድሃ ዜጎችን ሥራና የኑሮ ሁኔታ ደረጃ ያሻሽላል፤ | የሠራተኛ ደረጃዎችን አተገባበር በማሳደግ የተጋላጭ ሠራተኞችን መብቶች ይጠብቃል፤ |
| ትአ 3፤ የማህበራዊ መድንን ማስፋፋት | | ማህበራዊ መድን አሉታዊ /አልፎ አልፎ ሊመለስ የማይችል በህይወት እና በኑሮ ሁኔታ ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት ይከላከላል፤ ያስወግዳል፤ | ማህበራዊ መድን ቤተሰቦች ሥጋትን በተሻለ እንዲቆጣጠሩ በማስቻል ከፍተኛ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ለማሳተፍ ያስችላል፡፡ | |

| ትኩረት አቅጣጫ (ትአ 1) | ከሀብት (ጥሪት) መሟጠጥ መጠበቅ | ከሀብት (ጥሪት) መሟጠጥ ከባሰ ድህንት መከላከል | የኑሮ ሁኔታን ማስፋፋት | የኑሮ ሽግግር ማድረግ/ ለውጥ ማምጣት |
|---|---|---|---|---|
| 4፡ የመሠረታዊ አገልግሎት ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ | የጤና መድን ዋስትና በነፃ ወይም በድጎማ በመስጠትና በችግር ጊዜ በይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ለአስፈላጊ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ያሳድጋል፤፡ | የጤና ችግር ባለበት ጊዜ በነፃ መስጠት፣ የጤና መድን ዋስትና መደጎም እና ማህበራዊ ድጋፍ መስጠት የህይወት መጥፋትን(የሞት አደጋን) እና የቤተሰበብ ጥሪት መሟጠጥን ይከላከላል፤ | የመድን ዋስትና መስጠት በህፃናት ጤና ትምህርት ላይ የረዥም ጊዜ ምርታማነታቸውን ያድጋል፤ | ተጋላጭ ህጻናት ከተማሩ ካልተማሩት ተጋላጭ ህፃናት በላይ ስለመብታቸውና ኃላፊነታቸው የበለጠ ያውቃሉ፤ |
| ትአ5፡ ለጥቃትና በደል ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎች የሕግ ጥበቃና ድጋፍ መስጠት | በደል የተፈፀመባቸውን ጥቃት የደረሰባቸውን የተገለሉትንና ብዝበዛ የተፈፀመባቸውን ተጎጂዎች መልሶ ማቋቋም፤ | ህጋዊ፤ ማህበራዊና የገንዘብ ድጋፍ ስልቶች ለተጎጂዎች ተደራሽ መሆን አለባቸው፤ | የተለያዩ በደሎች፤ ጥቃቶች መገለልና ብዝበዛ...ወዘተ የደረሰባቸውን ድምፅ አልባዎች በመለየትና ዘመቻ በማካሄድ ድምፃቸውን ማሰማት | በደልን፤ ጥቃትን፤ ማግለልንና አድሎን በመከላከልና ምላሽ በመስጠት በከፍተኛ ደረጃ የተጋለጡ ሰዎችን መብት ማስከበር፤ |

## 1.2. የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት አስፈላጊነት/ አመክንዮ

ይህ ስትራቴጂ የተቀረፀው በኢትዮጵያ የማህበራዊ ጥበቃን አስፈላጊነት አስመልክቶ በሰነዶች ላይ ተከታታይ ጥልቅ ምርመራ በማድረግ ነው፡፡ በእነዚህ ማስረጃዎች መሠረት መንግስት በጥቅምት ወር 2007 ዓ.ም ብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲን ቀርጾ አጽድቋል፡፡ ለፖሊሲው መቀረጽ ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች በሶስት ዋና ዋና ነጥቦች ይጠቃለላሉ፡፡

***የመጀመሪያው*** በኢትዮጵያ ሕገመንግስት አንቀጽ 41 እና 90 መሰረት ሁሉም ዜጎች ማህበራዊ ጥበቃ የማግኘት መብታቸው የተረጋገጠ ነው ፡፡[6]

***ሁለተኛው*** ኢትዮጵያ ለማህበራዊ ጥበቃ አስፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞችን መንግስት እንዲቀርጽ የሚጠይቁ በርካታ የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ ህብረት ሰነዶችን አጽድቃለች፡፡

***ሶስተኛው*** ለማህበራዊ ጥበቃ ድጋፍ ማድረግ በአጠቃላይ ለኢኮኖሚና ለሰው ሃብት ልማት አስተዋጽኦ የሚያበረክት በመሆኑ ሲሆን፤ ይኸውም (1) በትምህርት በጤናና በስነ ምግብ ላይ መዋዕለ ንዋይን በማፍሰስ፤(2) በግል እና በጋራ/በማህበረሰብ የሚያጋጥሙ ስጋቶችን በመቀነስ፤ (3) ደሃና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች የገበያ ተሳትፏቸውን በማሳደግ እና (4) በማህበራዊ ጥበቃ የሚሰጡ ድጋፎች ከአካባቢ አልፎ በሰፊው የማዳረስ አቅም አላቸው፡፡

## 1.3. ዘላቂ ስርዓትን መገንባት

በዘላቂ ማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት ግንባታ ሶስት ተቀዳሚ አቅጣጫዎች አሉት፡፡ አንደኛ የማህበራዊ ጥበቃ ዓላማዎችን በሂደት እውን በማድረግ የኑሮ ሁኔታ ደረጃን በማሻሻል ለሁሉም ዜጎች አገልግሎቶች በእኩል ተደራሽ እንዲሆኑ ለማስቻል በተከታታይ ተግባራዊነት ላይ መሳተፍ ነው፡፡

ሁለተኛው፣ ዘላቂ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት ለድሃና ተጋላጭ ዜጎች ቅድሚያ መስጠቱ ነው፡፡ ይህ ስርዓት የተቀናጀ፤ ሁሉን አቀፍ ሲሆን፤ ለሰዎች ፍላጎት ተገቢ የሆኑ እና ደህነትን፣ተጋላጭነትን በበቂ ሁኔታ የሚፈታ ገቢ ማመንጨትን የሚያመለክት ነው፡፡ በተጨማሪም፣ በህይወት ዑደት/life cycle/ ውስጥ የተለያዩ ፍላጎቶችን ለማሟላት በየጊዜው እያደገ የሚሄድ፤ የግለሰቦችን እና የቤተሰቦችን ሁኔታዎች ለውጥ ለማንፀባረቅ በየጊዜው የሚሻሻል ሆኖ፤ ምርታማ አቅም ያላቸው ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ተደግፈው ከአንድ የማህበራዊ ጥበቃ ድጋፍ አይነት ወደ ሌላ የማህበራዊ ጥበቃ ድጋፍ በተገቢው ጊዜ ውስጥ ይሸጋገራሉ፡፡ ብሎም በሂደት ወደ ገበያ ተኮር እና ድጎማ አልባ የድጋፍ ዘርፎች ለምሳሌ ማህበራዊ መድን፣ አነስተኛ መድን እና ሌሎች የገንዘብ አገልግሎቶች ይሸጋገራሉ ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ ምርታማ አቅም የሌላቸው ግለሰቦች እና ቤተሰቦች አስቀድሞ የሚታወቅ እና የረጅም ጊዜ ድጋፍ በነጻ ይደረግላቸዋል፡፡

ሦስተኛው፣ 'ስርዓት' የሚለው ፅንሰ-ሃሳብ ባለድርሻ አካላት በትብብር ለመስራትና ውጤታማ አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲችሉ የተቀናጁ አደረጃጀቶችን ወይም አቅርቦቶችን የሚያመላክት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ይህ 'ስርዓት' የማህበራዊ ጥበቃ ዓላማዎችን በጋራ ለማሳካት የሚሰሩ የመንግስት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ኤጀንሲዎች፤ የልማት አጋሮች፤ የበጎ አድራጎት

ማህበራት በማህብረሰብ አቀፍ ድርጅቶች እና በተወሰነ ደረጃ በግል ድርጅቶች መካከል ባለው ጠንካራ አጋርነት የሚገለፅ ነው፡፡[7]

ስለዚህ ዘላቂ የማህበራዊ ሥርዓት አዲስ ተቋማዊ አደረጃጀትን የሚሻና የሚያስተባብር ሲሆን፣ የአፈፃፀም አቅሞችን የሚያጠናክር፣ ማስፈፀሚያ መሳሪያዎችን ለምሳሌ አንድ ብሔራዊ የምዝገባ ሥርዓት ወይም  የጋራ የተጠቃሚ ምዝገባ ሥርዓት የመሳሰሉትን የሚቀርጽ ነው፡፡

የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት ማጎልበት፣ ኢትዮጵያ  ወደመካከለኛ ገቢ ለምታደርገው ሽግግር ለሚኖራት የማህበራዊ ጥበቃ ማዕቀፍ በር ከፋች ነው፡፡  የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የቀጣይነት ተስፋ ሰጪ  መሆኑ፣ ማህበራዊ ጥበቃ  በሀገር ሀብት ላይ የተመሰረተ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡ ይህም ማህበራዊ ትስስርን በማጠናከር እያንዳንዱን ዜጋ  በዕድገቱ ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት  ሚኖረውን ድርሻ ያረጋግጣል፡፡

**ክፍል ሁለት  መነሻ ሐሳብ (ዳራ)**

**2.1. ልማት እና የፖሊሲ ተጨባጭ ሁኔታ**

i. ***ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት እና የሰው ሃብት ልማት፡-*** በመጀመሪያው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (ዕትዕ) ጊዜ ከ 2003/04 እስከ 2006/07 የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ  በየዓመቱ በአማካይ 10.5 በመቶ እድገት አስመዝግቧል፡፡ ይህም ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገሮች አማካይ እድገት መጠን ከሆነው 5 በመቶ እጥፍ ነው፡፡ ይህ ዕድገት በብሔራዊ ደረጃ ካለው ከድህነት ወለል  በታች ከሚኖረው ህዝብ በመቶኛ ለመቀነስ በዋናነት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ለምሳሌ በ1988/1989 45.5 በመቶ የነበረው በ2003/2004 ወደ 26 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ ይህ በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን መጨረሻ በ2012/2013[8] ወደ 16.2 በመቶ እንደሚወርድ ይገመታል፡፡ የሰው ሃብት ልማትም እንዲሁ መሻሻል አሳይቷል፡፡ ለምሳሌ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ የህፃናት ሞት በ1998 123 በ1000 በህይወት ከተወለዱ ልጆች ውስጥ የነበረው በ2004 ወደ 88 ዝቅ ብሏል፡፡ ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን (ማዕባ 2004) በተገኘው መረጃ ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመግባት ጠቅላላ ምጣኔ በ1997-2004 ባለው ጊዜ ከ74 በመቶ ወደ 91 በመቶ አድጓል፡፡ የምግብ ዕጥረት የረዥም ጊዜ ውጤቱ በተለይ መቀንጨር፤ የምግብ እጥረት አይነቶችን ለማስወገድ  ግንዛቤ ከፍ ያለ  ሲሆን፤ በተጨባጭ ችገሩን ለመቅረፍ ከፍተኛ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው (ማዕባ 2005) ፡፡ እስካሁን ድረስ ከታዩት መሻሻሎች ኢትዮጵያ (1) በዓመት በተከታታይ ሁለት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በህፃናት ላይ የሚታየው መቀንጨር መቀነስ እያሳየች ሲሆን (2) መቀንጨር ባለበት ከቆመባቸው ወይም መቀነስ ከሚታይባቸው ሃገሮች መካከል አንዷ ናት፡፡ (3) የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ምልክቶች በአንድ ላይ ተደራርበው በትንሹ ከሚታዩባቸው ሃገሮች መካከል አንዷ ናት፡፡አለም-ዓቀፍ የሥነ-ምግብ ሪፖርት (2007) እንደሚያሳየው በአሁን ጊዜ መቀንጨር እና መቀጨጭ ብቻ ናቸው የሚደራረቡት፡፡  ለተመጣጠነ ምግብ ትኩረት የሚሰጥ ግብርና በመቅረጽና  በተመጣጠነ ምግብ እጥረት ምክንያት የሚከሰተውን የህፃናት ዕድገት ውሱንነት ለመቀነስ ጥረት በመደረግ ላይ ነው፡፡

ii. ***ከሥነ-ህዝብ ዕድገት ትሩፋት ፡- ዕድሎች እና ተግዳሮቶች፡-***

የኢትዮጵያ ህዝብ 95.2 ሚሊዮን እንደሚሆን የሚገመት ሲሆን 20.4 በመቶ በከተማ አካባቢ ይኖራል፡፡ በ2030 ዓ.ም. ማለትም ከ2000 ዓ.ም. የህዝብ ቆጠራ 30 ዓመት በኋላ የህዝብ ቁጥር 135.6 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ ***(ሰንጠረዥ 2 ይመልከቱ)***[10] በህዝብ መዋቅራዊ ለውጥ ሳቢያ የህዝቡ ክፍፍል እንደሚከተለው ነው፡፡

- ***የህፃናት ብዛት፡-*** የማዕከላዊ ስታትስቲክ ባለሥልጣን ግምት እንደሚያሳየው የህፃናት (ከ0-14 ዓመት) ድርሻ መጠን ከአጠቃላይ ህዝቡ ሲታይ እየቀነሰ ነው፡፡ ከፍተኛ ውልደት መጠን/high fertility rate/ ታሳቢ በማድረግ በ2000 ዓ.ም. 43.8 በመቶ ከነበረው በ2007 ዓ.ም. ወደ 27 በመቶ ይቀንሳል ተብሎ ተገምቷል፡፡ ዝቅተኛ የመውለድ መጠን/low fertility rate/ ከተወሰደ 34 በመቶ  ይቀንሳል ተብሎ ተገምቷል፡፡ የመቀነሱ አዝማሚያም መልካም ዜና ነው ምክንያቱም  በአምራች ዕድሜ ክልል ላይ ያለው የጥገኝነት መጠን/dependency ratio/ ይቀንሳል ማለት ነው፡፡

- ***በመሥራት ዕድሜ ክልል ያለ ህዝብ መጠን*** ፡-ከላይ በተጠቀሰው የሚ.ዕ.ባ የሕዝብ ግምት፣ በመሥራት ዕድሜ ክልል (15-64) ላይ ያለው የህዝብ መጠን እንደሚጨምር ያሳያል (**ሰንጠረዥ 2 ይምልከቱ**)፡፡ እንደሚያሳየው በ2000 ዓ.ም በመስራት እድሜ ክልል ውስጥ ከነበረው 39.0 ሚሊዮን በ30 ዓመት ውስጥ ወደ 89.1 ሚሊዮን እንደሚጨምር ይገመታል፡፡ ከጠቅላላው ህዝብ ውስጥ ወደ 64 በመቶ ሊሆን እንደሚችል መረጃው ጨምሮ ያሳያል፡፡ ምንም እንኳን ከፍተኛው የህዝብ ቁጥር የሚታይበት ከ15-24 እድሜ ክልል ያለው በትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኘው ቢሆንም፤ በመሥራት ዕድሜ ክልል ያለው ሕዝብ ከፍተኛ የዕድገት መጠን እንደሚያሳይ አይካድም፡፡

- **እድሜው ከ65 ዓመት እና በላይ የሆነው የህዝብ** ብዛት በ2000 ዓ.ም. 2.5 ሚሊዮን (3.3 በመቶ) ሲሆን፤ በ2030 ወደ 6.4 ሚሊዮን (4.5 በመቶ) ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡

የህዝብ የዕድሜ መዋቅር ለውጥ እንደ መልካም አጋጣሚ ቢወሰድም፤ ለአዲስ ሥራ ፈላጊዎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተግዳሮት ሊሆን ስለሚችል ከወዲሁ ሊታሰብበት ይገባል፡፡ በዚህም ረገድ መሻሻል እንዳለ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ የሥራ አጥ መጠን ከ1992 8.06 በመቶ፣ በ1998 5.06 በመቶ የነበረው በ2006 በብሄራዊ ደረጃ ወደ 4.5 በመቶ መቀነስ ያሳያል፡፡

ፍጹም የሥራ አጥነት/open unemployment/ በከተሞች አካባቢ ይበልጥ ሰፍቶ የሚታይ ሲሆን በሰኔ 2013 እ.ኤ.አ በከተሞች 16.5 በመቶ ነበር፡፡ በገጠር በሰፊው የሚታየው ከአቅም በታች መስራት/under employment/ ደግሞ 2.0 በመቶ ነበር፡፡ በጾታ ሲለይ ወደ 27 በመቶ በከተሞች ያሉ ሴቶች እና 14 በመቶ የሚሆኑ በከተሞች ያሉ ወንዶች ሥራ አጥ ነበሩ፡፡ ዕድሜያቸው ከ20-24 በሆኑ የከተማ ወጣቶች (37 በመቶ ሴቶች እና 23 በመቶ ወንዶች) ሥራ አጥ ናቸው፡፡ ስራ ሳይኖራቸው የሚቆዩበትን ጊዜ ስናይ ከሥራ አጦች መካከል ግማሽ ያህሉ ከ6 ወራት በታች ያለሥራ የሚቆዩ ሲሆን ሩብ ያህሉ ብቻ ለአንድ ዓመት ስራ ሳይኖራቸው ይቆያሉ፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት ግምት**

| የዕድሜ ክፍል | 2000 | | 2030 | |
|---|---|---|---|---|
| | የህዝብ ብዛት (‘000) | % | የህዝብ ብዛት (,000) | % |
| 0-4 | 11995 | 16.2 | 13495.3 | 9.9 |
| 5-9 | 10796 | 14.6 | 13353.3 | 9.8 |
| 10-14 | 9607 | 13.0 | 13255.7 | 9.7 |
| **15-19** | **8426** | **11.4** | **13055.7** | **9.6** |
| **20-24** | **6983** | **9.5** | **12623.3** | **9.3** |
| **25-29** | **5785** | **7.8** | **11787.7** | **8.7** |
| **30-34** | **4496** | **6.1** | **10855** | **8.0** |
| **35-39** | **3643** | **4.9** | **9939.3** | **7.4** |
| **40-44** | **2888** | **3.9** | **8747.3** | **6.5** |
| **45-49** | **2333** | **3.2** | **7529.7** | **5.6** |
| **50-54** | **1824** | **2.5** | **6093.7** | **4.5** |
| **55-59** | **1440** | **2** | **4881.3** | **3.6** |
| **60-64** | **1140** | **1.5** | **3592.3** | **2.6** |
| 65-69 | 871 | 1.2 | 2655.7 | 2.0 |
| 70-74 | 627 | 0.8 | 1803.3 | 1.3 |
| 75-79 | 401 | 0.5 | 1123.7 | 0.8 |
| 80+ | 588 | 0.8 | 819 | 0.6 |
| በሁሉም ዕድሜ | 73843 | 100 | 135611.3 | 100.0 |

**በስራ ዕድሜ ክልል ያለ ህዝብ**

***<u>ምንጭ፡-</u> ማዕባ (2007) የህዝብ ቁጥር በ2030 በ30 ዓመት ከመለኪያዎች (ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣ መካከለኛ)***

የዕድሜ ባለፀጋ ዜጎችብዛት መጨመርን ተከትሎ የሚመጣውን ፍላጎት ማሟላት ሌላው የሃገሪቱን የሚያጋጥም ተግዳሮት ነው፡፡ የዕድሜ ባለፀጋ ዜጎች ህዝብ ብዛት ቁጥር በቀጣይ ጊዜያትም የሚጨምር ሲሆን 65 እና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያለው ህዝብ ብዛት በ2030 ወደ 6.4 በመቶ የሚያድግ ሲሆን ይህ ከጠቅላላው ህዝብ ብዛት አንፃር ሲታይ አነስተኛ ቢሆንም ቁጥሩ ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ ውስጥ ለአረጋውያን ፍላጎት የማይሰጥ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዕድሜና ፆታ ስብጥር የሃብት ክፍፍል ሲደረግ፤ ለወጣት እና ለአረጋውያን ቤተሰቦች እኩል ሊመስል ይችላል፡፡ ነገር ግን ሰዎች እድሜያቸው በገፋ ቁጥር እየተገለሉ ይሄዳሉ፤ ብቻቸውን እንዲኖሩ ይገደዳሉ ስለዚህም የተለየ እንክብካቤ እና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በሃገራችን ሲተገበር የቆየው ባህላዊ የመደጋገፍ ሥርዓት እንዲቀጥል ማድረጉ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በመጨረሻም የህዝብ ቁጥር መጨመር በሃገሪቱ ያለውን ከድህነት ወለል በታች የሚኖር ሕዝብ ቁጥር ይበልጥ ለመቀነስ አዳጋች ያደርገዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከህዝቡ 25.7 ሚሊዮን ወይም 26.0 በመቶ የሚሆነው ከድህነት ወለል በታች የሚገኝ ነው፡፡

### iii. የድህነት ቅነሳ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፡-

የኢትዮጵያ መንግስት ድህነትን ለመቀነስና የኢኮኖሚ ልማትን ለማስፋፋት በርካታ ዘላቂና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ለማስመዝገብ የሚችሉ ፖሊሲዎች፤ ዕቅዶች እና ስትራቴጂዎች በመቅረጽ አውጥቷል ፡፡ የግብርና ልማት መር ኢንዱስትሪ ስትራቴጂና የልማትና የድህነት ቅነሣ ፕሮግራም (1995-1997) በተሳካ ሁኔታ መተግበራቸውን ተከትሎ፤ መንግስት ድህነትን ለማስወገድ ፈጣንና ዘላቂ የልማትን ዕቅድ (ከ1998-2002) በማውጣት ሥራ ላይ አውሏል፡፡ እነዚህ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች በ2003/04 እና 2007/08 መካከል ባሉት ጊዜያት ሥራ ላይ የዋለው የመጀመሪያው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ለመቅረጽ መሠረት በመሆን አገልግለዋል፡፡ ይህ ዕቅድ በሁሉም የኢኮኖሚ መስኮች በተገኘው እድገት አማካኝነት ድህነትን ለመቀነስ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት አስተዋጽኦ አስችሏል ፡፡ እንዲሁም ለሁሉም የሴክተር ፖሊሲዎች ማህበራዊ ጥበቃን ጨምሮ መሠረት በመሆን አገልግሏል፡፡

የሁለተኛው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2013) ዋነኛ ዓላማ ኢትዮጵያ በ2018 መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ የማሰለፍ ራዕይን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ይህም እንዲሳካ በዓመት አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት መጠን በ11 በመቶ እንዲያድግ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ መፍጠር፤ ፈጣን የኢንዱስትሪ እና መዋቅራዊ ሽግግር የሚያመሩ ወሳኝ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል (ብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን 2008፡፡

### vi. ለከፋ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ድጋፎች ማድረግ፤

በማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ውስጥ መንግስት የተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ችግር ለመፍታት ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችንና የድርጊት መረሃ ግብሮችን[12] በማዘጋጀት ቁርጠኝነቱን አሳይቷል፡፡ ለምሳሌ ህፃናትን በሚመለከት፤ የኢትዮጵያ ሴቶች እና ህፃናት ልማት ዕቅድን (2003)፣ ረቂቅ የህፃናት ፖሊሲን (2004)፣ አማራጭ የህፃናት እንክብካቤ መመሪያን (2002)፣ ብሔራዊ የቅድመ መደበኛ ትምህርት የህፃናት እንክብካቤ እና የትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍን (2003) እና ወላጆቻቸውን ላጡ ተጋላጭ ህፃናት አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎች መመሪያን (2004) አውጥቷል፡፡

አረጋውያንንና አካል ጉዳተኞችን በሚመለከትም ተመሳሳይ ቁርጠኝነት አለ፡፡ እነዚህም የአካል ጉዳተኞች ሥራ የማግኘት መብት የሚያረጋግጠውን አዋጅ ቁጥር 568/2001 ፣ በመንግስት ስራ ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት የወጣውን የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999፤ ለአካል ጉዳተኞች የመንቀሳቀስ ችግራቸውን ለመፍታት የሚያስችሉ ባለሞተር ብስክሌቶችን፤ ተሽከርካሪ ወንበሮች ና ክራንቾች ከቀረጥ ነፃ ማስገባት እንዲችሉ የሚፈቅደውን መመሪያ ቁጥር 36/91 (መመሪያ ቁጥር 41/2008 ተብሎ የተሻሻለ)፤ ህንጻዎችን ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ለማድረግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 624/2002፤ እና የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ድርጊት መርሃ ግብር (2005-2014) መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከኤች አይቪ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ዘርፈ ብዙ የኤችአይቪ/ኤድስ ፖሊሲ/2005/ ከትምህርት፣ ከመኖሪያ፣ ከሥራ ቅጥር እና ከጤና እንክብካቤ ጋር በተያያዘ መድሎ እንዳይኖር የሚከለክለው ቁልፍ ድንጋጌ ነው፡፡ በአሰሪዎች ከኤችአይቪ ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ላይ የሚደረገውን ልዩነት ለማስወገድ ለሥራ ቅጥር አስገዳጅ የኤችአይቪ ምርመራ ማድረግ በኢትዮጵያ የአሰሪና ሰራተኛ ህግና በመንግስት መ/ቤቶች የሥራ ቦታ ኤችአይቪ ኤድስ መመሪያዎች በጥብቅ ተከልክሏል፡፡

**2.2. ድህነት እና የተጋላጭነት ሁኔታ**

የብሔራዊ ማህበራዊ ስትራቴጂ የተቀረፀው በኢትዮጵያ የድህነትና ተጋላጭነት ሁኔታ በሥነ ፆታ እና በህይወት ዑደት ዕይታ አንፃር በመቃኘት ነው[13]፡፡ ይህ ክፍል አጭር መግለጫ ያቀርብልናል፡፡

ድሃና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ የተለዩ ሲሆን፤ በሦሥት ዋና ዋና ክፍሎች ስር የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡ መጀመሪያ፣ ከድህነት ወለል በታች ያሉት ሆነው የዕለት ፍጆታቸውን እንኳን ማሟላት የማይችሉ 'የፍጆታ ድሃ' ቤተሰቦች አሉ፡፡ ለድሃ የኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ደግሞ ምግብ ከፍተኛውን የፍጆታ ወጪ የሚይዝ ስለሆነ፤ የፍጆታ ድህነት ከምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ሁለተኛው፣ የአንዳንድ ቤተሰቦች ድህነት ዘርፈ ብዙ ሲሆን እነዚህም ለሞት፣ ለጤና፣ ለተመጣጠነ ምግብ እጥረት እንዲሁም ለውሃና ለአካባቢ ንፅህና፣ ለትምህርት እና ሌሎች ለኑሮ መሠረታዊ ፍላጎቶች ያለመሟላት የሚያጋጥማቸው ናቸው፡፡

ሦስተኛው፣ አንዳንድ ወይም አብዛኞዎቹ ተጋላጭ ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ማህበራዊ መገለል የሚደርስባቸው ናቸው፡፡ ለአገልግሎቶች የመግቢያ ክፍያ መክፈል ባለመቻላቸው ወይም በአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት ስላለባቸው ብቻ የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዳያገኙና በሕብረተሰቡ ውስጥ በተለያዩ ተግባራት እንዳይሳተፉ ይገለላሉ፡፡ እነዚህ የተገለሉና ድሃ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በመገለል ሥጋት (ተጋላጭ) ውስጥ የሚኖሩ ናቸው፡፡ ሰንጠረዥ 3 የነዚህን ዘርፈ ብዙ ተጋላጭነት መሳለጥ/መደራረብ ያሳያል፡፡

በእርግጥ እነዚህን ዘርፈ ብዙ ተጋላጭነት ነጣጥሎ ማየት አይቻልም፡፡ የፍጆታ ድሃ የሆኑ ቤተሰቦች ከሌሎች የበለጠ ዘርፈ ብዙ ክልከላ ወይም መገለል ይደርስባቸዋል፤ ተጋላጭነታቸውም ከፍተኛ ነው፡፡ በሌላ በኩል እነዚህ ዘርፈ ብዙ የተጋላጭነት ባህሪዎች የማይሳለጡበት ሁኔታም አለ፡፡ ለምሳሌ ምንም እንኳን የተሻለ የኑሮ ደረጃ ቤተሰብ ውስጥ ቢኖሩም፣ ሴቶች፣ ህፃናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ድምፃቸው ላይሰማ ይችላል፤ ለበደልና መገለል ወይም ጥቃት ይበልጥ የተጋለጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ዘርፈ-ብዙ የድህነት ገፅታዎችን ለመፍታት የፖሊሲና ፕሮግራም አንድምታዎች እንዳሉት መንግሥት ይገነዘባል፡፡ ለዚህም ነው የብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ (የዚህ ስትራቴጂም) አምስቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ዘርፈ ብዙ የድህነት እና የተጋላጭነት ገጽታዎችን ለመፍታት በተገቢው መንገድ የተቀረፁት፡፡ የትኩረት አቅጣጫዎቹ ተደጋጋፊም ናቸው፡፡ ለምሰሌ ብዝበዛ እና መረሳት ወይንም መጣል (ትኩረት አቅጣጫ 5) የሚደርስባቸው ሰዎች ሙብት ለማስከበር፣ ለቤተሰቡ ኃላፊ የገንዘብ ድጎማ ማድረግ በቂ አይሆንም፡፡ የተገለሉ ሰዎችን የማብቃት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡ ስጋት ባለበት ሁኔታ ውስጥ የሥራ እድል እና የኑሮ ሁኔታን የሚያሻሽሉ ዕድሎችን መስጠት (ትኩረት አቅጣጫ 2) ብቻ በቂ አይሆንም፤ አነስተኛ መድን አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ አስፈልጊ ነው(ትኩረት አቅጣጫ 3)

ሰንጠረዥ 3፡ የድህነት ተጋላጭነት አቅጣጫዎች

| | የዕለት ፍጆታን ማሟላት | ዘርፈ ብዙ አቅጣጫዎች /ሰብአዊ/ | ማህበራዊ መገለል |
|---|---|---|---|
| ድሃ (በተግባር የተገለሉ) | ከድህነት ወለል በታች /በምግብ ዋስትና ያላረጋገጡ ቤተሰቦች/ | የጤና ጉድለት ያለባቸው የቤተሰብ ሃላፊዎች ወይም ግለሰቦች<br>የቀነጨሩ፤ ከፍተኛ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ያለባቸው ወይም የትምህርት ተደራሽነት ያላገኙ ህፃናት | አቅም ስለሌላቸው ራሳቸው ለአድሎ ለጥቃት ለመገለል ወይም የጉልበት ብዝበዛ በቤት ወይም በስራ ቦታ የተጋለጡ |
| ተጋላጭ (በመገለል አደጋ ውስጥ ያሉ) | ከድህነት ወለል በታች እና/ወይም የምግብ ዋስትናቸው ያልተረጋገጡ ቤተሰቦች | ያለጤና ዋስትና ወይም የጤና/የትምህርት ክፍያቸውን የሚሸፍንላቸው የሌላቸው ወይም ያለ ንፁሕ ውሃ እና የጤና አካባቢ የሚኖሩ በሕይወት ኡደት ውስጥ ሥነ ህይወታዊ ተጋላጮች (ምሳሌ ጨቅላ ሕፃናት እና ነፍሰጡር እናቶች) | በፆታ፤ በአካል ጉዳተኝነት፤ በኤች አይቪ ሁኔታቸው፤ በዕድሜ፤ ወላጆቻቸውን ላጡ ሕጻናት፤ በብሔር፣ በቦታ ወይም በሌላ ጉዳይ ከማህበረሰቡ መገለል የሚደርስባቸው ወይም ሰዎች በማህበረሰቡ ወይም በቤተሰባቸው ውስጥ ለአገልግሎቶች ወይም ለሥራ ተደራሽነት ልዩነት የሚደረግባቸው ወይም የወሳኝነትና ስልጣንና ሃይል እና ድምጽ አልባ ሰዎች፤ |

## 2.3. ለድህነትና ተጋላጭነት ምላሽ መስጫ ሥልቶች

### 2.3.1. ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ ስልቶች

ማህበረሰብ አቀፍ የድጋፍ ስልቶች በኢትዮጵያ ረዥም ታሪክ ያላቸው ናቸው[14]፡፡ እነዚህ የድጋፍ ስልቶች በሥነ-ልቦናዊም ይሁን በማህበራዊ (ማህበረሰብ አቀፍ) ደረጃ ችግሮች ሲኖሩ የመጀመሪያዎቹ የድጋፍ መልስ ሰጭ ስልቶች ናቸው፡፡ በተለያየ ደረጃ አራቱን የማህበራዊ ጥበቃ ዓላማዎች ያገለግላሉ፡፡ ጥበቃና መከላከል የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ ሥርዓት ዋነኛ ተግባሮች ሲሆኑ ኑሮን ማሻሻል በተወሰነ ደረጃ፤ ማህበራዊ ሽግግርን ውስን በሆነ መልኩ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡
ምንም እንኳን የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ ሰጪዎች ትክክለኛ ቁጥር ባይታወቅም፤ ዕድሮች፣ ዕቁቦች እና ማህበራት በስፋት የሚታወቁ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ ሰጪዎች ናቸው፡፡[15] አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ቢያንስ የአንድ ዕድር አባል ነው፡፡ ይህ መረጃ በገጠርና ከተማ ሲለይ፣ 87 በመቶ የከተማ ነዋሪና እና 70 በመቶ የገጠር ኗሪ ቢያንስ አንድ ዕድር አላቸው፡፡[16] የአባልነት መስፈርቱም (ሀ) መኖሪያ አካባቢ (ለ) የመመዝገቢያ ክፍያ መክፍል መቻል (ሐ) ወርሃዊ መዋጮ ማዋጣት ናቸው፡፡ ለምሳሌ የከተማ ዕድር አባል በየወሩ ብር 10 (አስር ብር) መዋጮና የመመዝገቢያ ክፍያ ብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) ያዋጣል፡፡ የመዋጮ መጠኑ የሚወሰነው ዕድሩ እንዳጠራቀመው የሀብት (ጥሪት) መጠን ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአብዛኛው እንደሚስተዋለው ዕድሮች ልዩነት የማያደርጉ አካታች መሆናቸው ይታመናል፡፡ ድሃ ቤተሰቦች የተሻለ አቅም ካለው ቤተሰብ የሚያንሱበት ሁኔታ የለም፡፡

ዕድሮች ለተመዘገቡ አባሎቻቸው በሞት ጊዜ ለዕድሩ አባል ወይም ለአባሉ የቅርብ ቤተሰቦች ገንዘብ ይከፍላሉ (እንደ መድህን አባል)፡፡ ከዕድር የሚከፈለው ክፍያ ከቀብር ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ለመሸፈን ነው፡፡ ዕድሮች ሥነ-"ልቦናዊ ድጋፍም" ይሰጣሉ፡፡ ቀሪው ቤተሰብ እንዲፅናና ያደረጋሉ፡፡ አንዳንድ ዕድሮች ለየት ያሉ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ ለምሳሌ የቤት ቃጠሎ ወይም የህክምና ወጭ፣ በፀና ህመም ተኝቶ ለሚታከም አባል፣ ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናትና ከኤች አይቪ ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

ከዕድሮች በተጨማሪ ሌሎች ማህበረሰብ አቀፍ የድጋፍ ስልቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- **ዕቁቦች**፡- ተዘዋዋሪ ገንዘብ ሲሆን አባላት የአጭር ጊዜ የገንዘብ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ወይም ለኢንቨስትመንት ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ተደራሽነታቸው በከተማ እና በገጠር አካባቢዎች መካከል ይለያያሉ፡፡ የገጠር አካባቢዎች ትንሽ ሲሆኑ የከተማ አካባቢዎች ንግድ ሥራ ለመጀመር ወይም ለማስፋፋት ብዙ ገንዘብ ያንቀሳቅሳሉ፡፡
- **ጉዲፈቻ (ማደጎ)**፡- ይህ የድጋፍ ስልት የተጋላጭ ህፃናትን ህይወት እና ዕድገት ያረጋግጣል፡፡ በኑሯቸው የተሻሉ ቤተሰቦች ከድሃ ቤተሰቦች ወይም አሳዳጊ ዘመዶች ልጆችን (ባብዛኛውወንዶች ልጆችን) በጉዲፈቻ በመውሰድ እንደራሳቸው ልጅ ያሳድጋሉ ፡፡ ፡፡ የተፈጥሮ ወላጆች የወላጅነት መብታቸውን አሳልፈው ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ጉዲፈቻ አለም-አቀፋዊ ክስተትም ነው፡፡ ሆኖም የአገር ውስጥ ጉዲፈቻን ለማበረታታት ጥረቶችን በማካሄድ ላይ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያውያን ድሃ ልጆችን በጉዲፈቻ እንዲወስዱ እና እንዲያሳድጉ ይበረታታሉ፡፡
- **ሂርጳ እና ዳባሬ**፡- የአርብቶ አደር አካባቢዎች የድጋፍ ስልቶች ናቸው፡፡ ችግር ለሚገጥመው ቤተሰብ ዘመድ አዝማድ እንስሳት እና ሌሎች ሀብቶች በማስተላለፍ ይሳተፋሉ፡፡ ይህ የአርብቶ አደሮች የድጋፍ ስልት በምላሽ/reciprocity/ እና የልውውጥ አይነት ነው፡፡ ዛሬ ተቀባይ የሆነው ሰው ነገ ሰጭ ይሆናል የሚል መርህ ነው፡፡ ወይም የተገላቢጦሽ ማለት ነው[19]፡፡
- **ደቦ/ጅጊ**፡- ጉልበት የማግኛ ስልት ነው፡፡ የገጠር ቤተሰቦች የሥራተኛ ዕጥረቶችን የሚያቃልሉበት ዘዴ ነው፡፡ በተለይም በመሬት ዝግጅት፣ በሰብል መዝራት እና መሰብሰብ ጊዜ የሚያገለግል ዘዴ ነው። ይህ ስልት ከበፊቱ እየቀነሰ የመጣበት ሁኔታ ይታያል፡፡ የማህበራዊ መዋቅር ለውጥን ጨምሮ፣ የትምህርት መስፋፋት የእርሻ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም መጨመር (ለምሳሌ ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ግዢና ስርጭትን) እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡
- **የማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች**፡- በቅርቡ እንደ ማህራዊ ድጋፍ ስልት ብቅ ያለ ስልት ነው[20]፡፡ በግለሰቦች እና/ወይም ቡድኖች በሃገር ደረጃ የተቋቋሙ ሲሆን እነዚህ ተቋማት ከኤች አይቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን ለመንከባከብናበማህበረሰቡ ውስጥ ተጋላጭ ለሆኑ ሕፃናት ድጋፍ ለማድረግ የጋራ ዓላማ ባላቸው ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ድርጅቶች ጥምረት የተቋቋሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥምረቶች የቤተክርስቲያኖች ተወካዮች፣ ፈቃደኞችና ሌሎች በዕምነት ላይ በተመሠረቱ ተቋማት በመንግስት፣ በንግድ እና ሌሎች ሙያዎች ቤተሰቦችን አካተው ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶችን በማካተት የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ጥምረቶቹ የሚሰጡት አገልግሎትም ከቁሳቁስ እና ገንዘብ ከመስጠት ጀምሮ በዓይነት፣ ቁሳቁስ በመስጠትና ችገረኞች በሚገኙበት ቦታ በአካል በመገኘት ድጋፍ እስከማድረግ የሚደርስ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡የማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች በኢትዮጵያ ስርጭት በሰንጠረዥ 4 ተመልክቷል፡፡ አንድ ማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረት ለአንድ ቀበሌ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ አሁን ያለው ሽፋን 9 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ትግራይ መቶ በመቶ ሽፋን አለው፣ አማራ፣ ጋምቤላ እና ኦሮምያ 98.5፤11.7 እና 0.7 በመቶ ሽፋን በቅደም-ተከተላቸው፡፡ በአፋር፣ በሃረሪ፣ በድሬዳዋ እና ቤንሻንገል አካባቢዎች ጥቂት የማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች አሉ፡፡

ስለዚህ የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረቶች ለማህበራዊ ጥበቃ ስትራቴጂ መተግበር ቁልፍ መሣሪያዎች ስለሆኑ ሽፋናቸውን ለማስፋፋት ጥረት መደረግ አለበት፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡- የማህበረሰብ እንክብካቤ ሕብረት ብዛት በክልል**

| ክልል | የቀበሌዎች ብዛት (በከተማ እና በገጠር) | የማክሕ ብዛት | የማክሕ ጠቅላላ ቀበሌ በ% |
|---|---|---|---|
| ትግራይ | 802 | 802 | 100 |
| አፋር | 410 | 0 | 0 |
| አማራ | 3496 | 3445 | 98.5 |
| ኦሮሚያ | 6886 | 50 | 0.7 |
| የኢትዮጵያ ሱማሌ | 985 | 26 | 2.6 |
| ቤንሻንጉል | 475 | 0 | 0 |
| ደቡብ ሕዝቦች ክልል | 3887 | 160 | 4.1 |
| ጋምቤላ | 256 | 30 | 11.7 |
| ሃረሪ | 36 | 0 | 0 |
| ድሬደዋ | 47 | 0 | 0 |
| አዲስ አበባ | 116 | 0 | 0 |
| **ጠቅላላ** | **17388** | **1590** | **9.1** |

ምንጭ፡ ሰማጉሚ

### 2.3.2. መደበኛ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች

#### 2.3.2.1. የገጠር ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮገራም 4 *(2016-2020*)

የኢትዮጵያ መንግሥት በ1997 ዓ.ም. ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራምን እንደ አንድ ዋና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ዘርፍ ጀመረ፡፡ ፕሮግራሙ በገጠር አካባቢዎች ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን ቤተሰቦች ፍላጎት የሚያሟላ ነው፡፡ ፕሮግራሙ እንዲያስገኝ የታሰበው ውጤት (ሀ) የምግብ ፍጆታን ማረጋገጥ (ለ) የጥሪት መሟጠጥን መከላከል (ሐ) በገንዘብ ድጋፍ አማካኝነት ገበያን ማነቃቃት (መ) የአገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ እና (ሠ) በማህበረሰብ የጉልበት ሥራ አማካኝነት የተፈጥሮን አካባቢ መልሶ እንዲያገግም ማድረግ ናቸው፡፡

የአራተኛው ዙር ፕሮግራም በ411 ወረዳዎች ሥር የሰደደ የምግብ እጥረት ባለባቸው የገጠር ሕዝቦች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በእነዚህ ወረዳዎች ለሚገኙ 10 ሚሊዮን የሚሆኑ ችግረኛ ሕዝቦች የሚደርስ ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥ 8.3 ሚሊዮን የሚሆኑት ሰዎች ሥር የሰደደ የምግብ እጥረት ያለባቸው፤ 1.7 ሚሊዮን የሚሆኑት ደግሞ አስቸኳይ የምግብ እጥረት የሚያጋጥማቸው ናቸው፡፡ 83 በመቶ የሚሆኑት በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም-4 የታቀፉ ቤተሰቦች በማህበረሰብ አቀፍ የጉልበት ሥራ

በመሳተፍ የገንዘብ ወይንም የምግብ ድጋፍ ይሰጣቸዋል፡፡ 17 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የጉልበት ሥራ ለመሥራት የሚያስችል አቅም ለሌላቸው ያለ ቅድመ ሁኔታ ድጋፍ የሚያገኙ ናቸው፡፡ ሴቶች እና ወንዶች እንደ ቅደም-ተከተላቸው 51 እና 49 በመቶ በእነዚህ ፕሮግራሞች ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ዓላማውን እያሳካ ነው፡፡ የማህበረሰብ አቀፍ የተጠቃሚዎች ልየታ ሥርዓት ምስጋና ይግባውና የሚሰጠው ድጋፍ ለተገቢው ተጠቃሚዎች እየደረሰ መሆኑን፤ በአፍሪካ ዙሪያ ካሉት ሴፍቲኔቶች ጋር ሲነፃፀር ድጋፉ ላልተገባ የመድረሱ ዕድል አነስተኛ ነው፡፡በምስራቅ አፍሪካ እ.ኤ.አ በ2011 የተከሰተውን ከፍተኛ የምግብ ቀውስ በማስወገድ ፕሮግራሙ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ በፕሮግራሙ የታቀፉት ቤተሰቦች በ2008 በተከሰተው ኢ.ሊ.ንኖ ምክንያት በድርቅ ራሳቸውን መከላከል አልቻሉም ፡፡

የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ፕሮግራም የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች ሁለተኛው አካል ሆኖ የተቀረፀ ሲሆን የምግብ እጥረት ላለባቸው ቤተሰቦች የገቢ ምንጭ በማስፋት እና ምርታማ ጥሪት በመጨመር አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ባለፉት አምስት አመታት በግብርና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አማካኝነት የቴክኒክ ድጋፍ አድርጓል፡፡ እንዲሁም በአነስተኛ የገንዘብ ተቋማት (እና በገጠር የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ተቋማት) አማካኝነት የገንዘብ አቅርቦት አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ ይህን እንጂ፣ የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ፕሮግራም የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራምን ያህል ተደራሽነት አልነበረውም፡፡ ለምሳሌ፣ 9 በመቶ የህብረተሰብ ጉልበት ሥራ ተሳታፊዎች፣ 4 በመቶ የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች እና 3 በመቶ የቅርብ ጊዜ የልማታዊ ሴፍቲኔት የፕሮግራም ተሳታፊዎች ብቻ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶችና የብድር አገልግሎት አግኝተዋል (የግ.ሚ. 2007). ይህን የፕሮግራም ትሥሥር ችግር ለመፍታት አዲሱ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ጋር በመቀናጀት በአንድ አመራር ስር እንዲሆኑ ተደረጓል፡፡ ይህም በመሆኑ፣ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ቤተሰቦች በኑሮ ሁኔታ መሻሻል ተግባራት ላይ ለመሳተፍ ከአለፉት ዓመታት የተሻለ ዕድል ይኖራቸዋል፡፡

#### 2.3.2.2. የከተማ ልማተዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም እና ሌሎች ድጋፎች

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በአብዛኛው ገጠራማ ብትሆንም፤ ከተሜነትም እየጨመረ ሲሄድ ድህነት የበለጠ የከተማ ችግር ይሆናል፡፡ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የኢትዮጵያ መንግስት እና የልማት አጋሮቹ የከተማ ድሃና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመደገፍ ረዘም ያለ ልምድ አላቸው፡፡ መንግስት ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ድሃ የከተማ ሰዎች የከተማ ቤት ተደራሽነትን ለማሻሻል የተለያዩ ፕሮግራሞችን ቀርፆ በማካሄድ ላይ ነው፤ የጋራ ህንፃ ግንባታን ጨምሮ፡፡ እነዚህ ፕሮግራሞች ለሴቶች ቅድሚያ በመስጠት ይታወቃሉ፡፡ እንዲሁም የገበያ ግሽበትን ለማረጋጋት፣ ከብሄራዊ የምግብ ክምችት አነስተኛ ገቢ ላላቸው ከገበያ ዋጋው ዝቅ አድርጎ በማቅርብ፣ እና እህል ወደ ውጪ መላክን በመቆጣጠር ገበያውን ለማረጋጋት እርምጃዎችን ወስዷል፡፡

የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በዚህ ልምድ ላይ ተመስርቶ የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ የከተማ ቤተሰቦችን እና ግለሰቦችን ገቢና የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ያለመ ነው፡፡ እንዲሁም የፕሮግራም ፈፃሚዎችን አቅም በመገንባት የተሻለ ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ የመጀመሪያው ዙር በ11 ከተሞች ይጀመራል፤ ከአዲስ አበባ እና ድሬደዋ በተጨማሪ ከዘጠኙ

ክልላዊ መንግስታት ከእያንዳንዳቸው አንድ  አንድ ከተማ  ይጨምራል፡፡  በእነዚህ ለናሙና በተመረጡ ከተሞች ሕዝብ ብዛት ወደ 5.0 ሚሊዮን ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1.0 ሚሊዮን (20 በመቶ) ከድህነት ወለል በታች ነው፡፡ በሙከራ ትግበራ  604,000 ለሚሆኑ ሰዎች ድጋፍ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ከድህነት ወለል በታች (55.2በመቶ) የሚሆኑ ናቸው፡፡

አዲስ አበባ ትልቋ የከተማ ማዕከል በመሆኗ 75 በመቶ የሚሆነውን ድጋፍ ትወስዳለች፡፡ ከሙከራ ጊዜ በኋላ የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም 972 ከተሞችንና የገጠር ከተማ መንደሮችን፤ 4.5 ሚሊዮን የከተማ ድህና ተጋላጭ ሰዎችን ይደርሳል፡፡[23] የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት እንደገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ሁለት መሰረታዊ ክፍሎች አሉት፤ የማህበረሰብ ጉልበት ስራ ላይ የሚሰማሩ 84 በመቶ እና ቀጥታ ድጋፍ 16 በመቶ ናቸው፡፡

በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የሚታቀፉት የማህበረሰብ ጉልበትሥራዎች ከገጠር ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም የበለጠ ስፋት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ብዙ የሰው ጉልበት የሚጠይቁ አነስተኛ ደረጃ መሰረተ ልማት፤  ማህበራዊ አገልግሎት ልማት፣ እድሳት እና ጥገናን፤ ከተማ ማስዋብ፤ የተፋሰስ ልማት፣ የወንዝ ተፋሰስ ፅዳት እና የፍሳሽ ማስወገጃን ማፅዳት እና የከተማ ግብርና ላይ በመሰማራት የሚሳተፍባቸው ናቸው፡፡

ለሙከራ ትግበራ የከተማ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች  የከተማ ፍጹም ድሃዎች  ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በዕድሜ መግፋት፣ በአካል ጉዳት እና የተለያዩ ስር የሰደዱ እና የማይድን ሕመም ያለባቸው፤ ሥራ መስራት የማይችሉ  ናቸው፡፡ የእነዚህ ሰዎች የመጨረሻ እድል ልመና እና በቂ ገቢ የማያስገኙ አነስተኛ ሥራ ላይ መሰማራት ነው፡፡ ፕሮግራሙ ሲስፋፋና ሲያድግ፣ በብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ የተለዩትን  ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን በሙሉ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ይጠበቃል፡፡

**2.3.2.3. የመዋጮ ማህበራዊ ዋስትና መስፋፋት**

በኢትዮጵያ መደበኛ መዋጮ ላይ የተመሰረተ የመድን ዋስትና ሽፋን በ1956 ዓ.ም. ለመንግስት ሰራተኞች፣ ለፖሊስና ለሀገር መከላከያ አባላት ተቋቋመ፡፡ ፡፡ የጡረታ መዋጮ የሚከፍሉ ሰራተኞች  ጡረታ በሚወጡበት ጊዜ ቢያንስ ብር 500 ያገኛሉ፡፡ እንዲሁም በሥራ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ጥቅሞችን ያገኛሉ፡፡ የሟች ጡረተኛ ወራሾች የጥቅማቸውን ከፊል የማግኘት መብት አላቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በመንግስት ጡረታ 1 ሚሊዮን የሚሆኑ መዋጮ እየከፈሉ ያሉና ወደ 700,000 የሚሆኑ ደግሞ የማህበራዊ ዋስትና ተጠቃሚዎች አሉ፡፡ በ2006 መንግስት ብር 1.87 ቢሊዮን የከፈለ ሲሆን 5 ቢሊዮን ሰብስቧል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ መርሀ ግብር የህዝቡን 1 በመቶ ብቻ የሚደርስ ነው፡፡ ስለዚህ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ  መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ እና በራሳቸው ሥራ ለሚተዳደሩ ችግረኛ ቤተሰቦች በራሳቸው የማህበራዊ ዋስትና አጠቃቀም ዘዴ፤ በማህበረሰብ ማህበራዊ ጥበቃ እና የሰብአዊ ምላሽ ላይ ብቻ የተወሰኑ ነበሩ፡፡ ለዚህ ሁኔታ በከፊል ምላሽ ይሆን ዘንድ፣ መንግስት የግል መደበኛ ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን በ2004 በማቋቋም የግል ዘርፉን ማህበራዊ ዋስትና ገንዘብ በማስተዳደር ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ወደ 800,000 የሚሆኑ የግል ዘርፍ መደበኛ ሠራተኞች የማህበራዊ መዋጮ የሚከፍሉ ሲሆን ወደ

6,000 የሚሆኑ ደግሞ የጥቅሙ ተካፋይ ናቸው፡፡ በአዋጅ ቁ.715/2004 መሰረት መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች፤ በሃይማኖት ተቋማት፤ በፖለቲካ ድርጅቶች፤ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና፤ በሲቪክ ማህበረሰብ ውስጥ የሚሰሩ ግለሰቦች በፈቃደኝነት በማህበራዊ ዋስትና ሽፋን ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ መዋጮውን የሚከፍሉት ጡረታ በሚወጡበት ጊዜ ብር 540 ያገኛሉ፡፡ የክፍያ መዋቅሩ እንደመንግስት ዘርፍ ተመሳሳይ ነው[25]፡፡

ለመንግስት ሠራተኞች፡ መደበኛ ለሆኑ የግል ዘርፍ ሠራተኞች እና ለበጎ አድራጎት ሰራተኞች የድንገተኛ ወጭያቸውን ለመሸፈን የሚያስችል የማህበራዊ መድን ዋስትና ሽፋንን ለማስፋፋት መንግስት ቁርጠኛ አቋም ወስዷል፡፡ ሁለት የጤና መድን ዋስትና ሽፋኖች ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ የመጀመሪያው የማህበራዊ ጤና መድን ዋስትና (ማጤመዋ) በክፍያ ላይ የተመሰረተው ሲሆን፤ በመንግስት እና በመደበኛ የግል ዘርፎች ሠራተኞች የመድን ዋስትና አቅድ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 690/2003 መሰረት ቀጣሪም ተቀጣሪም ለማህበራዊ ጤና መድህን ዋስትና ያዋጣሉ፡፡ የኢትዮጵያ የጤና መድን ዋስትና ኤጀንሲ (ኢጤመዋኤ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 191/2003 ተቋቁሟል፡፡ በመላ ሃገሪቱም 24 ቅርንጫፎች በመክፈት የሥርዓት አደረጃጀቱን አጠናቋል፡፡

ሁለተኛው የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድን ዋስትና (ማአጤመዋ) መዋጮ ላይ ያልተመሰረተ፤ መደበኛ ላልሆኑ ዘርፎች ሠራተኞች እና ለገጠር ደኃ የህብረተሰብ ክፍሎች የተቀረፀ ነው፡፡ በ198 ወረዳዎች ተሞክሮ በአምስት አመት ውስጥ ብሔራዊ ሽፋን ለማሳካት ታቅዷል፡፡ ከዚህ አንፃር የማ.አ.ጤ.መ.ዋ የማስፋት ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡ ስትራቴጅው የማ.አ.ጤ.መ.ዋን ሕጋዊ እና ተቋማዊ ማዕቀፍ ለማጠናከር ይጥራል፡፡ የማ.አ.ጤ.መ.ዋ መዋጮ ለመወሰን የምንጠቀምባቸው መለኪያዎች (1) በቤተሰብ ብዛት፤ (2) በአንድ በተወሰነ ወቅት ወደ ጤና ተቋማት የተደረገ ምልልስ እና (3) የቤተሰብ/የግል ወጪን ያካትታሉ፡፡

### 2.3.2.4. መሰረታዊ የጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት እና ማስፋፋት

የጤና ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (ጤዘልፕ) ማዕቀፍ ውስጥ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም (ጤኤፕ) ለገጠርና ለከተማ ህዝብ በእኩልነት ደረጃ መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ፕሮግራሙ 38,000 ያህል የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን (ጤኤሠ) አሉት፡፡ ሁሉም ሴቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ፕሮግራሙ 3 ጤ.ኤ.ሠ ለ 1 ቀበሌ ወይም 1ለ500 ቤተሰቦች ጥምረት ማህበረሰቡንና ቤተሰቦችን ለማዳረስ ይጠቅማል፡፡ ለእነዚህ ከህብረተሰቡ ጋር ታች ወርደው ለሚሰሩት የጤና ሰራተኞች ምስጋና ይግባቸውና ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ህፃናትን ሞት በ1990 ዓ.ም 204/1000 ከነበረው በ2003/04 ዓ.ም ወደ 64/1000 ሊወርድ ችሏል፡፡ በተጨማሪም በወሊድ ምክንያት የሚከሰተው ሞት 69 በመቶ በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ወርዷል፡፡ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን በየአመቱ በ11 በመቶ ቀንሷል (የፕላን ኮሚሽን 2007)፡፡

**2.3.2.5. የትምህርት ተደራሽነትን ማስፋፋት**

ባለፉት 20 ዓመታት በገጠር እና በከተማ አካባቢዎች የትምህርት ተደራሽነት አመርቂ እድገት አሳይቷል፡፡ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት ጨምሮ በትምህርት ዘርፍ የልማት ፕሮግራም 4 (2002/03 - 2006/07) ለመድረስ አስቸጋሪ የሆኑትን የሕብረተሰቡ ክፍሎች ተሳትፎ ጭምር ለማሳደግ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ በትምህርት አዋጅ ቁጥር 72/1995 የአካል ጉዳተኞችን የትምህርት ተደራሽነት ለመጨመር አዎንታዊ አንቀፆች ተካተዋል፡፡

በዚህም ምክንያት አጠቃላይ ወደ ትምህርት ቤት የመግባት ጥምረት/gross enrolment/ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት (ከ1-8ኛ ክፍል) 101.3 በመቶ (97.8 በመቶ ለልጃ ገረዶች) ደርሷል፡፡ ጠቅላላ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት በአንደኛ ደረጃ (ከ1-8) የሚሳተፉ 70,477 (41.8 በመቶ ሴቶች) ናቸው፡፡ በተጨማሪም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ7000 በላይ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች አሉ፡፡ ይህም በደረጃ ሲተነተን በዝቅተኛው ሁለተኛ ደረጃ (ከ9-10) 6,115 ተማሪዎች፤ ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (ከ11-12) 1258 ይሆናሉ፡፡  ይህንን መረጃ ከሚመዘግቡት ሠራተኞች መካከል የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጽንሰ ሃሳብ ካለመረዳት ሊሆን ይችላል እንጂ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ህፃናት ቁጥር ከዚህ በላይ ሊልቅ እንደሚችል መንግስት ይገነዘባል፡፡

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከል በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ላሉት የህብረተሰብ ክፍሎች የትምህርት ተደራሽነትን ለማዳረስ ጥቅም ላይ ካዋሉት ስልቶች አንዱ ነው፡፡ ወደ 900,000 የሚገመቱ የገጠር ህፃናት (65 በመቶ ልጃገረዶች) መደበኛ ትምህርት ከሚገኝበት እርቀው ስለሚኖሩ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላትን ይጠቀማሉ (ትሚ 2007)፡፡

የትምህርት ቤት  ምገባ ፕሮግራም ለቤተሰቦች ያለ መዋጮ እገዛ እንደማግኘት ቆጠራል፡፡ እንደሌሎቹ  የምግብ ወይም የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች  ተመሳሳይ የትምህርት እና የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት ጥቅሞች አሉት፡፡ በማህበራዊ ጥበቃ ማዕቀፍ ውስጥ የትምህርት ቤት ምገባ ለችግረኛ ቤተሰቦች አስተማማኝ የገቢ ማስተላለፊያ ምንገድ  ነው፡፡ የትምህርት እና የምግብ ወጪዎችን በመቀነስ ስር የሰደደ የምግብ እጥረት ባለባቸው ቤተሰቦች ለህፃናት የተመጣጠነ ምግብ ለማቅረብ ያገለግላል፡፡ ብተሰቦች  ከአደጋ ጊዜ እና ከአደጋ በኃላ ቀድሞ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ያስችላል፡፡ እንዲያውም ህፃናትን ከትምህርት ቤት የማውጣት ሁኔታን ይቀንሳል፡፡ በአሁኑ ጊዜ 650,000 ተማሪዎች በ1200 ትምህርት ቤቶች ስር የሰደደ የምግብ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎችን ሸፍኗል፡፡ የትምህርት ሚኒስቴር ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከሴቶች እና ወጣቶች ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የቅድመ ህፃናት እንክብካቤ እና ትምህርት ማዕቀፍ ፖሊሲ ተቀርጿል፡፡

**2.3.2.6. ስነ ምግብ**

ይህ እስትራቴጂ ሲቀረፅ ከለሳ ላይ የነበረው የብሔራዊ ስነ-ምግብ ፕሮግራም ዓላማ እጅግ በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ እናቶች እና ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ ሁኔታን ለማሻሻል ነው፡፡ አጀማመሩ አስቸኳይ ያልተመጣጠነ ምግብ ችግረ ላይ ትኩረት በማድረግ ነበር፡፡ ከ 2003 ዓ.ም ጀምሮ ስር የሰደደ ያልተመጣጠነ ምግብ እጥረት እና መቀንጨርን ለመቀነስ ትኩረት

ሰጥቷል፡፡ የሥነ-ምግብ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከሚሰጡት 16 የጤና አገልገሎቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ከቁልፍ መልዕክቶች መካከል የሕጻናት አመጋገብ ስርዓት ማሻሻል፣ አራርቆ በመውሰድ ፣ በመውሰድ ዕድሜ ክልል ያሉት ሴቶች የአመጋገብ ስርዓትን ማሻሻል እና ጠቃሚ ማዕድናት አንዲያገኙ ማድረግ ይገኙበታል፡፡

ግብርናው ሥነ ምግብ ተኮር እንዲሆን መንድስት ጥረት እያድረገ ነው፡፡ የግብርና ኤክስቴንሽን ስርዓቱ የተመጣጠነ ምግብ ለማምረት የሚያስችል ስትራቴጂ የቀረፀ ሲሆን፤ ይህም አርሶ አደሮች ለተመጣጠኑ ምግቦች አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሰብሎች እና እንስሳት ለህብረተሰቡ እንዲያቀርቡ የሚያበረታታ ነው፡፡ የልማት ሰራተኞች ሥነ ምግብ ተኮር ግብርና ላይ ስልጠና ወስደዋል፡፡ በተጨማሪም የምግብ ዋስትና ድጋፎች ለምሳሌ እንደ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የመሳሰሉት ሥነ ምግብ ተኮር ሆነዋል፡፡

#### 2.3.2.7. ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች

በ1997 ዓ.ም መንግስት የአገልግሎት ሁለንተናዊ ተደራሽነት ፕሮግራም/Universal Access Program/ አጽድቋል፡፡ ይህም ንፁህ ውሃ ለሁሉም ዜጎች ለማቅረብ የሚያስችል ነው፡፡ ይህንን ቃል-ኪዳን ለማሟላት የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በገጠር፣ በከተማ እና በሃገር ደረጃ እንደቅደም ተከተላቸው 98 በመቶ፣ 100 በመቶ እና 98.5 በመቶ ንፁህ ውሃ ለማቅረብ ግብ አስቀምጦ ነበር፡፡ በሰኔ 2006 ዓ.ም. ከገጠር እና ከከተማ የውሃ አቅርቦት ተደራሽነት እንደ ቅደም ተከተላቸው 75.5 እና 84.1 በመቶ የነበረ ሲሆን በሃገር ደረጃ ደግሞ 76.7 በመቶ ነበር[27]፡፡ የመሠረታዊ አገልግሎት ጥበቃ ፕሮግራም መተግበር ለእነዚህ ስኬቶች ምክንያት መሆኑን ማስታዋስ ይገባል፡፡ ይህ ፕሮግራም በትምህርት፣ በጤና፣ በግብርና፣ በውሃ አቅርቦት እና አካባቢ ንፅህና በገጠር መንገዶች ጥራት ተደራሽነትን ለማሻሻል የረዳ ነው (ዓለም ባንክ 2008) ፡፡

#### 2.3.2.8. የአደጋ ስጋት ስራ አመራር እና የአየር ለውጥ

ኢትዮጵያ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ከሚጋለጡ ሃገሮች አንዷ ናት፡፡ ድርቅና ጎርፍ በተደጋጋሚ ሀገሪቱን የሚያጠቁ የተፈጥሮ አደጋዎች ናቸው፡፡ ከሰው ሰራሽ አደጋዎች የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ችግሮች መልስ ለመስጠት መንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተለያዩ መንገዶች (ለምሳሌ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች) ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል ፡፡ ሃገሪቱ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ምላሽ ስልቶችን በማሻሻል ከአደጋ ቀውስ ምላሽ ወደ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ተሸጋግራለች፡፡ ለዚህም መገለጫው የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲ፣ እስትራቴጂ፣ ፕሮግራም እና፤ የኢንቨስትመንት ማዕቀፍ፤ ለአየር ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን መቅረጹ ነው ፡፡

የዝናብ መጠን ከመደበኛው በታች በሚሆንበት ጊዜ የመድን ሽፋን የሚሰጥ የአየር ለውጥ መድን ለማስተዋወቅ እና ለማስፋፋት ጥረቶች አሉ፡፡ ይህ በግል የመድን ዋስትና ኩባንያዎች እና (ለምሳሌ ኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር፣ የኦሮሚያ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር) እንዲሁም ከእርዳታ ሰጪዎች ማህበረ ረድኤት ትግራይ ትብብር በትግራይ መተግበር ጀምረዋል፡፡ የኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ የሰብልና የእንስሳት አየር ለውጥ ምክንያት የሚሰጠው የሙከራ መድን ፕሮጀክት ግምገማ እንደሚያሳየው አብዛኞች ተጠቃሚዎች የኑሮ ሁኔታቸው ከፍ ያለ ገበሬዎች ሲሆኑ፤ ደሃ ገበሬዎች የመድን

ዋስትናውን ለመውሰድ ፍላጎት የላቸውም፡፡ ይህም የመድን ዋስትና ደሃ ገበሬዎችን ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን እንዳለበት ይጠቁማል (ማኢደዜ 2004) ፡፡

ከዚህ አንፃር የትግራይ መንግስት የሃሪታ/አር4 ዘርፈ-ብዙ አጋሮች ያሉበት (መንግስት/የግል/ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) ፕሮጀክት ነድፏል፡፡ ይህም አደጋን ለመቀነስ የሚያስችለው ፕሮግራማቸው ደሃ ገበሬዎችን የአየር መድን ዋስትና እንዲሰጡ የሚያስችል ነው፡፡ ከልማታዊ ሴፍቲኔት ጋር በማያያዝ የማህበረሰብ ጉልበት ሥራ ተሳታፊዎች የመድን አርቦውን በከፊል በዓይነት (በጉልበት) እና በገንዘብ እንዲሸፍኑ አማራጭ የሚሰጥ ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠቃሚዎቹ ምርታማ ውጤት ስላገኙ የመድን አረቦዎን እንደማስያዣ በመጠቀም በአነስተኛ ብድር ማግኘት ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የዓለም እንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት (ኢ.ል.ሪ) እና የኦሮሚያ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን የእንስሳት መድን ዋስትና ፕሮግራም ጀምረዋል፡፡

### 2.3.2.9. ሥራና የሠራተኛ መብቶች

ድሃና ተጋላጭ ቤተሰቦች የሚመርጡት የኑሮ ሁኔታ የሚወሰነው በራሳቸው አቅም እና በሚያገኙት ድጋፍ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የኢኮኖሚ እና የፖሊሲ ሁኔታ ጭምር ነው፡፡ ይህንን በሚመለከት መንግስት የተለያዩ ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች እየተገበረ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂን (1994 ዓ.ም.)፣ የከተማ ልማት ፖሊሲን (1997 ዓ.ም.)፣ የአነስተኛ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እስትራቴጂ (2003 ዓ.ም.)፣ የአርብቶ አደር ልማት ፖሊሲ (2000 ዓ.ም. ከ1995-2010)፣ የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክት (ከ1995-2010 ዓ.ም.) እና ብሄራዊ የሥራ ፖሊሲ (2006 ዓ.ም.) ይገኙበታል፡፡

የሰው ሃብት ልማትን በመገንባት ምርታማነትን ማሳደግ፤ አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ማልማት የሃገሪቱ የልማት ስትራቴጂ ማዕከል ናቸው፡፡ ባለፉት 5 ዓመታት ከ 4 ቢሊዮን ብር በላይ የአነስተኛ ገንዘብ ብድር ከመሰጠቱም በላይ 1.2 ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎች የቴክኒክ እና የሙያ ትምህርትና ስልጠና በማግኘታቸው በአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ወደ 1.5 ሚሊዮን የሚጠጋ አዲስ የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ የፌዴራል አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ሁሉን አገልግሎት በአንድ መስኮት/one-stop-shop/ በመላ ሃገሪቱ በማስፋፋት ስራ የሌላቸው ሰዎች ስራ እንዲፈጥሩ ወይም ስራ እንዲያገኙ ድጋፍ ሰጥቷል፡፡

የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 የስራ ላይ ተጋላጭነትን ለማስወገድ የጤና እና ደህንነት፤ የኢንዱስትሪ ሰላም ለአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት፤ እንዲሁም የስራ ቦታዎች ሊያሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶችን አስቀምጧል፡፡ አዋጁ ከ14 ዓመት በታች ያሉ ህፃናትን ቅጥርን ከልክሏል፡፡ ከ14-16 እድሜ ያሉትም አደጋን ሊያስከትሉ የሚችሉ ስራዎች ላይ እንዳይሳተፉ ይከለክላል፡፡

በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክልል ወቅታዊ የሥራ ፍለጋ ሥደት የተለመደ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የስራ መረጃ በአግባቡ አላደገም፡፡ በአብዛኛው ቅጥር የሚፈጸመው በገበያ ቀናት ሲሆን፣ ወጣት ሴት እና ወንድ ስራ ፍለጊዎች ወደ እሩቅ ቦታ ዋስትና በሌለው ሁኔታ በማጓጓዝ ነው፡፡ በገጠር አካባቢዎች የገበሬዎች ስልጠና ማዕከላት ለገበያ መረጃ ማዕከል እና ለስልጠና መገልግል

ይችላሉ፡፡ እነዚህ ማዕከላት የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙት ከመንግስት እና ከተለያዩ ፕሮጀክቶች ሲሆን (ለምስሌ አይፒኤምኤስ) ገበሬዎችም አንዳንድ ወጪዎችን ይሸፍናሉ፡፡ የኤክስቴሽን ሰራተኞች በገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል ሰሌዳ ላይ የገበያ መረጃዎችን ይሰጣሉ፤ በየሳምንቱም ወቅታዊ ያደርጉታል፡፡ የገበያ ኮሚቴ ቋሚ ያልሆኑ የገበሬ ኮሚቴዎች፣ የገበያ ቦታዎችን በሌሎች አካባቢዎች እየተዘዋወሩ ይጎበኛሉ፤ ወይም በስልክ ያገኙዋቸዋል፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት የእህል ዋጋና አቅርቦትን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ የገበያ መረጃ ስርዓት ፍጹም አይደለም፡፡ በገበሬዎች ስልጠና ማዕከላት የሚሰጡት መረጃዎች ጠቅለል ያሉ ሲሆን በአካባቢው ባሉት የሰብል ዓይነት ላይ አያተኩርም፡፡ በመንግስትና በለጋሾች የሚደገፈው የግብርና እድገት ፕሮግራም እነዚህን ማእከላት ወደ ግብርና ንግድ እና ገበያ መርጃ ማዕከላት ለማሳደግ ያለመ ነው፡፡

#### 2.3.2.10. የፍትህ ተደራሽነት

መንግስት ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መብቶች መጠበቅ የሚያስችሉ አስፈላጊ የህግ ማሻሸያዎችን አድርጓል፡፡ ለምሳሌ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በ1952 የፍትሃብሔር ሕግ ውስጥ የነበሩትን ክፍተቶች እና ወጥነት የሚጎድላቸውን ድንጋጌዎች ለማሻሻል ችሏል፡፡ በሴቶች የኢኮኖሚ መሻሻል ላይም አወንታዊ ለውጥ አምጥቷል፡፡[28] ሌሎች የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ እና የተሻሻለው የወንጀል ሕግ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የህፃናት እና የሴቶችን መብቶች እና ደህንነቶች ስለሚጎዱ ወንጀል ሆነው ተደንግገዋል፡፡ በትምህርት ቤት ፆታዊ ጥቃትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል የስነምግባር ደንብ አለ፡፡

በፍትህ ሚኒስቴር የሴቶች፣ ወጣቶች እና ህፃናት ማሰተባበሪያ ጽ/ቤት በጾታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶችን እንዲሁም ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍል መብቶችን የሚጥሱ ወንጀሎችን ለመመርመር እና ለሕግ ለማቅረብ የሕግ ድጋፍ ይደርጋል ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የዚህ አይነቱ ድጋፍ በአዲስ አበባ የሚገኝ ሲሆን መንግስት በክልሎችም ለማስፋፋት አልሟል፡፡ ለሴቶችና ለልጃገረዶች ጥቃት ምላሽ የሚሰጥ ስርዓት ተዘርግቷል፡፡ ለምሳሌ፣ በፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት ለሚድርስባቸው ለሴቶች መጠለያዎች በዋናነት በአዲስ አበባ የሚገኙ ሲሆን፤ ከተ.መ.ድ የሴቶች ፕሮግራም ጋር በመተባበር በሌሎች አካባቢዎችም ለማስፋፋት እቅዱ አለ፡፡

በጥቃት የተጎዱ ህፃናት የተለያዩ የስነ-ልቦና አገልግሎቶች፣ ለምሳሌ መጠለያ፣ ምክር እና የህክምና ድጋፎች ያገኛሉ፡፡ መንግስት ከዩኒሴፍ ጋር በመተባበር በፌደራል ፍ/ቤቶች ማህበራዊ ሠራተኞች ቁጥር ከ14 ወደ 25 ጨምሯል፡፡ በክልል ፍ/ቤቶችም የህፃናትን ጉዳት የሚያዩ ማህበራዊ ሠራተኞች አሉ፡፡

### 2.4. ባለድርሻዎች

በማህበራዊ ጥበቃ ሥርአት ቁልፍ ባለድርሻ አካላት በሁሉም የአስተዳደር አካላት ያሉ አግባብነት ያላቸው የመንግስት ተቋማት፣ የልማት አጋሮች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣/ሲቪል ማህበረሰብ፣ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶችና የግል ዘርፍና የሂደቱ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ የእነዚህና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ዝርዝር ስልጣን እና ተግባር ***አባሪ 1*** ይመልከቱ፡፡ አጭር ማብራሪያ ከዚህ እንደሚመለከተው ቀርቧል፡፡

***መንግስት***፡- አዋጅ ቁጥር 916/2008 የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ቁልፍ ሚ/ር መስሪያ ቤቶችን፣ ኤጀንሲዎችን፣ እና ኮሚሽኖች ስልጣንና ተግባር ዘርዝሯል፡፡ ሌሎች አስፈፃሚ አካላትም በተለያዩ አዋጆች ተቋቁመዋል፡፡ ***አባሪ-1*** በማህበራዊ ጥበቃ ሥርአት እንደቁልፍ ባለድርሻዎች 23 የመንግስት ተቋማትን የለየ ሲሆን ይሰሩት የነበረውን ማህበራዊ ጥበቃ ሥራ አጠናክረው ይቀጥላሉ ፡ ነገር ግን በዚህ እስትራቴጂ እንደተገለፀው ከአዲሱ ስርዓት ጋር ማጣጣም ይጠበቅባቸዋል፡፡

**የልማት አጋሮች፡-** የልማት አጋሮች /የሁለትዮሽ፣ በይነመንግስታት እና የተ.መ.ድ የረጅም ጊዜ የልማት ፕሮግራሞችን በመደገፍ፤ በአደጋ ጊዜ ሰብዓዊ እርዳታ በመለገስ፤ የከተማ የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት፤ የከተማ እና የገጠር ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም በመደገፍ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ መንግስት እውቅና ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ለብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ዝግጅት ሁነኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ወደፊትም በኢትዮጵያ ዘላቂ ማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት እንዲዘረጋ ጥረታቸው እንደሚቀጥል ይጠበቃል፡፡

**በመ.ያ.ድ/ሲቪል ማህበራት ድጋፎች፡-** መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ለከፋ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በሚሰጡት ድጋፍ የሚጫወቱት ሚና መንግስት እውቅና ይሰጣል፡፡ እነዚህ ድርጅቶች የሚያደርጉት ድጋፍ የብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ ራዕይ ተልዕኮ እና አላማዎች ጋር የሚጣጣሙበት ሁኔታ ላይ መንግስት ተከታታይ ምክክር ያደርጋል፡፡

**ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች፡-** የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት እና እድሮች የመንግስትን ማህበራዊ ጥበቃ እስትራቴጂዎች ለመተግበር ዋና ሞተሮች ናቸው፡፡ ለህብረተሰቡም ቅርብ በመሆናቸው ከሌላ ድርጅቶች የበለጠ ማን በይበልጥ ተጋላጭ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ፕሮግራማቸውን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ከነዚህ ድርጅቶች ጋር ይሰራሉ፡፡ ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች የማህበራዊ ጥበቃ ጉዳዮችን ለማስፈጸም እንዲችሉ ከተለያዩ የአቅም ግንባታ ድጋፎች ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡

**ቀጥታ እና ቀጥታ ያልሆኑ ተጠቃሚዎች /ደንበኞች/**፡- በብሄራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ በግልጽ እንደተቀመጠው ቀጥታ እና ቀጥታ ያልሆኑ የማህበራዊ ጥበቃ ተጠቃሚዎች /ደንበኞች/ የተለዩት ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ እነዚህም (1) በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ህፃናት (ለምሳሌ ወላጆቻቸውን ያጡ፤ በጎዳና የሚኖሩ) (2) ተጋላጭ ነፍሰ ጡሮች እና የሚያጠቡ እናቶች ፣ (3) የአካል እና የአእምሮ ጉዳተኛ ሰዎች/ህፃናት/፣ (4) ተንከባካቢ እና ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያን፣ (5) ስራ ለመስራት ጉልበት የሌላቸው ዜጎች፣ (6) ሴት ቤተሰብ አስተዳዳሪዎች (እማወራዎች)፣ (7) የተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ተጠቂዎች ለምሳሌ ለማኞች፣ የጎዳና ልጆች፣ በሴተኛ አዳሪነት የተሰማሩ፣ አደንዛዥ እጽ እና የሌሎች ሱሶች ተጠቂዎች (8) በኤች አይቪ ኤድስ እና ሌሎች ስር በሰደዱ በሽታዎች የተጠቁ (9) ለጥቃት እና ለበደል የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች (10) በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች፤ (11) ስራ አጥ ወንድ፣ ሴት እና ወጣቶች (12) ማህበራዊ የመድን ዋስትና ሽፋን በሌለው መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማሩ ዜጎች እና (13) በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ወደ ሃገራቸው በግዳጅ እንዲመለሱ የተደረጉ ከስደተኞች ተመላሾች ናቸው፡፡

ቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ከሚደርግላቸው በስተቀር፣ አብዛኞቹ  የሚሰጠውን የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ በመጠቀም  ከጥገኛነት ተላቀው እራሳቸውን እንዲችሉ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የማህበራዊ ጥበቃ ክትትል እና ግምገማ ለሚያደርጉ ባለሙያዎች ስላሉበት የኑሮ ደረጃ ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ፡፡ በ መረጃ ስርዓቱ  የተከማቹ እነሱን የተመለከተ መረጃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ የመረጃው አስተዳዳሪዎች ስለ ግለሰቦች የሚይዙት እና የሚጠብቁትን መረጃ ምስጢራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.6. የተገኙ ትምህርቶች

### 2.6.1. ሽፋንና በቂነት

ከዚህ በላይ ቀረቡት በርካታ ጥረቶች እንዳሉ ሆኖ ሽፋናቸው እጅግ ውሱን ነው፡፡ ለምሳሌ መዋጮ ላይ የተመሰረተው ማህበራዊ መድህን ዋስትና የሚደርሰው ከሀገሪቱ  ህዝብ 1.0 በመቶ የሚሆነውን ብቻ  ሲሆን የሚሰጠው ሽፋን ዉስን ነው፡፡ ለአካል ጉዳተኞች፤ በጾታ ላይ መሰረት ያደረገ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች እና ለአረጋውያን የሚሰጡት ልዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች ቀጣይነት የሌላቸው እና በከተማ ላይ ያተኮሩ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ነፃ ሕክምና ድጋፍም በቂ አይደለም፡፡

ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የተሻለ ሽፋን ያለው ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ወደ 7.9 ሚሊዮን ህዝብ ለመድረስ ችሏል፡፡ ነገር ግን አሁንም ቢሆን የምግብ ዋስትናቸው ያልተረጋገጠ ቤተሰቦች ሙሉ ለሙሉ አልተሸፈኑም፡፡ ፕሮግራሙ ሁሉንም የገጠር ወረዳዎች ካለመሸፈኑም በላይ በከተማ አካባቢዎች አሁን ድረስ ስራ ላይ አልዋለም፡፡

በልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ሙሉ ቤተሰብ በመሸፈኑ (የመጠቀም ድርሻው ከቤተሰቡ ብዛት መመጣጠኑ) በቂ እገዛ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የጥሪት ማሚጣጠን በመከላከል ከእገዛው  ለማውጣት ሂደቱ ያደረገው አስተዋጽኦ በቂ አይደለም፡፡ በቂ ድጋፍ ካልተደረገ ድህነትን በዘላቂነት ለማሸነፍ ይከብዳል፡፡ ያለው በጀት ውሱን በመሆኑ የቤተሰብ ሽፋን ሲጨምር የድጋፍ መጠን ይቀንሳል፤ የድጋፍ መጠን ሲጨምር የቤተብ ቁጥር ይቀነሳል፡፡

### 2.6.2. ድጋፍ የሚፈልጉትን ወገኖች መለየት

ለማህበራዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች፣ ድጋፍ ፈላጊዎችን የመለየት ስልቶች ተቀርጾአል፡፡ የኢትዮጵያን ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም የልየታ ስልቱን በየጊዜው በማሻሻል በይበልጥ ድሃ ተኮር በማድረግ በደጋማ አካባቢዎች ውጤታማ ሆኗል፡፡ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ዙሪያ ካሉት ተመሳሳይ ማህበራዊ ድጋፍ ፕሮገራሞች ሲወዳደር ጥሩ ነበር[29]፡፡ ሌሎች ማህበራዊ ጥበቃ ድጋፎች ተጠቃሚ በመለየት ረገድ ስኬታቸው አነስተኛ ነው፡፡፡ ለምሳሌ የማህበረሰብ ጤና መድን ዋስትና ሙከራ ፕሮጀክት የድሀዎች አርቦ (መሬት፣ ቤት ወይም ማናቸውም ዋጋ ያለው ንብረት በሌላቸው እንደተገለፀው) ስለሚደጎም ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን መለየት በበጀት ምደባው መጠን የሚወሰን ነው፡፡

ቤተሰቦች ወይም ግለሰቦች ከልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ያለአግባብ ወጥተናል የሚል ቅሬታ ካላቸው፤ አቤቱታቸዉን የሚያቀርቡበት መድረክ ፕሮግራሙ አዘጋጅቷል፡፡ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ጥበቃ ፕሮጀክት ማህበራዊ ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ ስኮር ካርዶች እና የዜጎች ሪፖርት ካርዶች ስራ ላይ በማዋሉ፣ ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ

ለመለየት ከዘረጋው ስርዓት ጋር ተዳምረው ውጤታማ ያድርጉታል ፡፡ ይሁን እንጂ የአቅርቦቱን ጥራትና ለዜጎች ያለውን ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ ስምምነት የተደረሰበት የአገልግሎት ደረጃ የለም፡፡ ውጤታማ የቅሬታ ሰሚ ስርዓት ማሟላት ከሚገባቸው መመዘኛዎች (ሀ) ዜጎች ፕሮግራሙ የሚጠቀምባውቸን የልየታ መመዘኛዎች ተገቢ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል; (ለ) ተጠቃሚዎች መብታቸውን ሊያዉቁ ይገባል፤ (ሐ) ገለልተኛ የቅሬታ አቀራረብ ስልት ሊኖር ይገባል፡፡ እንዲሁም (መ) በፕሮግራሙ ቀረጻና አተገባበር መሻሻል ላይ ዜጎች ግብረ መልስ ሊሰጡ ይገባል፡፡

### 2.6.3 ማቀናጀትና ማስተባበር

ከቀድሞ ዓመታት በተለየ መልኩ፤ አራተኛው የልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ማህበራዊ ደህንነትና የኑሮ ሁኔታ ማሻሻያ ድጋፍን ያቀናጀ ፕሮግራም ነው፡፡ በዚህ ስትራቴጂ እንደሚጠበቀው ማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓቱን ለመቅረጽ መሰረት የጣለ እና የተቀናጀ አገልግሎት የመስጠት ሥርዓት ሲሆን በጊዜ ከተገደበ ፕሮግራም፣ ውጤታማ ወደ ሆነው የማህበራዊ ጥበቃ እና የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር የሚያሸጋግር ፕሮግራም ነው፡፡ ብዙ ተዋንያን በማህበራዊ ጥበቃ መሳተፋቸው ጠንካራ ጎን ያለውን ያህል ተግዳሮቶችም አሉት፡፡ የማህበራዊ ጥበቃ መርጃ ስርዓት የተበታተነ ነው፡፡ በባለድርሻዎች መካከል የመረጃ እና ተሞክሮ ልውውጥ ውስን ነው፡፡ በዘርፉ ዙሪያ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ለማስፈፀም ሕጋዊ ክፍተት አለ፡፡ በፌዴራልና በክልል መዋቅሮች መሀከል በማህበራዊ ጥበቃ ተሳትፎ ረገድ የመናበብ ድክመት አለ፡፡

### 2.6.4. አቅሞች

የብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ ለመቅረጽ ይረዳ ዘንድ የተከናወነው የማህበራዊ ጥበቃ ተደራሽነት ዳሰሳ እና ክፍተት ትንተና፣ የማህበራዊ ጥበቃ ድጋፎችን ለመቅረጽና ለመተግበር በተወሰነ ደረጃ አቅም እንዳለ አሳይቷል፡፡ ለምሳሌ፣ የገጠር ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ለመንግስት እና የማህበረሰቡ መዋቅሮች ስር በሰደደ የምግብ እጥረት ፍላጎት ላይ መረጃ እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ግንዛቤ ተፈጠሯል፡፡ በፌዴራል፣ በክልል፣ በወረዳ ያሉ የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች እና የማህበረሰብ የምግብ ዋስትና ግብረ ኃይሎች ዕውቀት እና ልምድ አግኝተዋል፡፡

በዚህ ስኬት በመበረታት መንግስት በከተማ ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ቀርፆ አጠናቋል፡፡ ይህም በከተማ ተመሳሳይ የመንግስት እና የማህበረሰብ መዋቅሮች አቅምን ይገነባል፡፡ የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መንግስት እና ለጋሽ ድርጅቶች (ለምሳሌ ዩኒሴፍ) ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ ለሴቶች እና ህፃናት የሚያደረጉትን እገዛ ሲያስተባብር ቆይቷል፡፡ የመንግስት ሰራተኞች የማህበራዊ መድን የማስተዳደር የረዥም ጊዜ ልምድ አለ፡፡ ከ2011 ጀምሮ የግል ዘርፍ የማህበራዊ የመድን ዋስትና (መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ ሳይጨምር) ለማስተዳደር የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ይሁን እንጂ ባጠቃላይ የማህበራዊ ጥበቃ ስራ የተበታተነና ያልተቀናጀ ከመሆኑም በላይ በተለይ በወረዳ ደረጃ ይህንን ስርዓት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ያቅም ውስንነት አለ ፡፡ ለምሳሌ የግብርናው ዘርፍ 60,000 የልማት ሰራተኞች እና 15,000 የገበሬ ማሰልጠኛ መዕከላት አሉት፡፡ የጤናው ዘርፍ 38,000 የሚጠጉ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች አሉት፡፡ የሰራተኛና ማህበራዊ ዘርፍ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የማህበራዊ ሠራተኞች በየወረዳው የሉትም፡፡

**2.6.5. ዘላቂነት**

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው የማህበራዊ ጥበቃ የገንዘብ ድጋፍ የሚመጣው ከውጪ ነው፡፡ መንግስት ከጊዜ ወደ ጊዜ ለማህበራዊ ጥበቃ ከራሱ በጀት በመመደብ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይሄዳል፡፡ የማህበራዊ ጥበቃን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና ፖለቲካ ፋየዳዎች የህዝብ ግንዛቤን ለመጨመር ለሚደረጉ ጥረቶች በጀት ይመድባል፡፡

**ለማጠቃለል** ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ከፍተኛ እድገት የታየ ቢሆንም፤ ተቋማዊ ማዕቀፎች፣ አቅሞች እና የትግበራ ስልቶች ለድሃና ተጋላጭ ህዝቦች ትርጉም ባለው መልኩ ውጤት ለማምጣት በቂና ጠንካራ አይደሉም፡፡ በማህበራዊ ጥበቃ ረገድ የዜጎችን ሕገመንግስታዊ መብቶች ይበልጥ ተግባራዊ ለማድረግ እነዚህን ማዕቀፎች መገንባት ያስፈልጋል፡፡

### ክፍል ሦስት፡- ስትራቴጂካዊ ማዕቀፍ

በክፍል ሁለት እንደታየው፣ በማህበራዊ ጥበቃ የዜጎችን መብቶች ለማስከበር እና ለማረጋገጥ በአምስቱም የትኩረት አቅጣጫዎች በርካታ ባለድርሻ አካላት ይሳተፋሉ፡፡ ይህ ክፍል ቁልፍ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮችን ይኸውም ውጤታማ እና የተቀናጀ የማህበራዊ ጥበቃን ለማድረስ አስተዋጽኦ አላቸው የተባሉትን ያብራራል፡፡ እነሱም፡-

- ሽፋን እና ልየታ /coverage and targeting/ (ገፊና ሳቢ /push pull/ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት እና ተደራራቢ ጥቅምን ማስቀረት፤
- ሁሉን አቀፍ እና የወደፊት ፍላጎትን ያካተተ ድጋፍ /comprehensive and evolving support/ ፤
- ከፕሮግራም ድጋፍ መውጣት/graduation/፤
- ተጠያቂነት እና ተግባቦት መፍጠር /accountability and communication/፤
- የፆታ፣ የዕድሜ፣ የአካል ጉዳት እና ኤች አይቪ ተጎጂዎችን ማካተት/main streaming/፤

#### 3.1. ሽፋን እና ልየታ

የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ቁልፍ ዓላማው አብዛኛው ለድህነት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የፕሮግራም ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ የሚካተቱት የህብረተሰብ ክፍሎችን ከዚህ በላይ በክፍል 2..2 በአንክሮ እንደተገለጸው ለተደራራቢ የድህነት መገለጫዎች የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ መገንዘብ ያለብን (1) ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከአንድ የትኩረት አቅጣጫ በላይ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ (2) አንዳንዶች ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተብለው የተለዩት ሰዎች ከሚሰጠው ድጋፍ ለተወሰነ ጊዜ ተጠቅመው ወደተለያዩ ደረጃዎች ይሸጋገራሉ፡፡

ብሄራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ የህብረተሰብ ክፍሎችን በጥቅሉ አስቀምጧል፡፡ በትክክል ማን ማን ተጠቃሚ መሆን እንዳለበት የሚወሰነው በተዘረጋው የልየታ ስልት ነው፡፡ የማህበራዊ ጥበቃ ልየታ መርሆችን የሚከተሉት ናቸው፡፡

(1) **በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መልክአ ምድራዊ ሀብት ክፍፍል** - ማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች ቀስ በቀስ በመላ ሀገሪቱ በማስፋፋት ደሃና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በየትኛውም ባሉበት ቦታ ሆነው ተደራሽ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ ውጤታማ የመልክአ ምድራዊ ልየታ በማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች ያልተሸፈኑ አካባቢዎችን በመለየት ያስቀምጣል፤ ያሉትንም አገልግሎቶች ደረጃቸውን ያሳውቃል፡፡ ለማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት የመንግሰት በጀት ይመደባል፤ የግል ዘርፍ እና ሲቪል ማህበራት ወደ ስርዓቱ እንዲገቡ ይበረታታሉ፡፡

**(2) የልየታ ስህተቶችን መቀነስ /ያለአግባብ ማካተት ና ማስወጣት**

ለማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓቱ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ልምድ ላይ በመገንባት የልየታ ስህተቶችን /ያለአግባብ ማካተትና ማስወጣት/ ይቀንሳል፡፡ እነዚህም የማህበረሰብ ልየታ ዘዴን፣ የቅሬታ ማቅረብ እና መፍታት ስርዓትን መጠቀም የቀበሌ እና

የቤተሰብ ደህነት ጠቋሚ መረጃ መጠቀም ሲሆኑ፤ በተጨማሪ ገፊና ሳቢ ሁኔታዎችን እና የተደጋገሚ ተጠቃሚነትን የመከላከል ስራን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህንም ለማስረዳት ያህል፡-

- **ገፊና ሳቢ ሁኔታዎች፡** በአንድ በኩል ድህነት እና ተጋላጭነት ማህበረሰቡ ከመኖሪያ አካባቢው ጥሎ እንዲሄዱ ይገፋፋል/ገፊ ሁኔታዎች/፡፡ በሌላ በኩል ሕዝቦች አገልግሎቶች ተደራሽነት ከፍ ወዳለባቸው አካባቢዎች ሊሳቡ ይችላሉ /ሳቢ ሁኔታዎች/፡፡ ሁለቱም የልየታ ስርዓት ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

- **ተደጋጋሚ ጥቅም ማግኘት-** ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ጥቅማ ጥቅሞችን ከብዙ ምንጮች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ክስተት ነው፡፡ይኸውም ሕጋዊ ወይም ህገወጥ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ መዋጮ ላይ ያልተመሰረተ ማህበራዊ ጡረታ መዋጮ ላይ ከተመሰረተው ማህበራዊ ጡረታ ከፍ ካለ፣ የኋለኛው ልዩነቱን ለመጠየቅ ቢችል ወይም ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ጡረታ መቀየር ቢችል የሚሉት ፡፡ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓቱ መተግበር ሲጀምር ለፈጻሚዎች ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ጉዳዮች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

(ሐ) **የልየታ ስርዓትን ዕሴት ከፍ ማድረግና ወጪውን መቀነስ፣**

የመለየት ተግባራት መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለመተንተን፣ ለመተግበር እና ለመከታታል ወጪዎች አሏቸው፡፡ ውስብስብ የሆኑ የልየታ ስርዓቶች ስህተቶችን ሊቀንሱ ይችላሉ ነገር ግን ወጪያቸው ከፍተኛ ስለሆነ፤ እነዚህን ማመዛዘን ያስፈልጋል፡፡

የማህበረሰቡን ተሳትፎ መሰረት ያደረጉ የልየታ ስርዓቶች ድህነትና ተጋላጭነት የአካባቢው ሰው ስለሚረዳ፤ ስርዓቱንም የራሱ አድርጎ ስለሚይዘው መረጃ ላይ ከተመሰረተው የልየታ ስርዓት (ለምሳሌ ራስን መቻል/አለመቻል ትንተና) የተሻለ ነው፡፡ የሥርዓቱ መኖር ራሱ ለማህበረሰቡ ኩራት ነው፡፡ ቅሬታዎችም ሲነሱ በቀላሉ ለመፍታት ያስችላል፡፡

የማህበረሰብ አቀፍ ልየታ ዘዴን ለማጠናከር እና ግልፅነትን ለመጨመር አራተኛው ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም 'የቀበሌ ምግብ ዋስትና መለኪያን' እና 'የቤተሰብ ድህነት መለኪያን' ከማህበረሰብ ልየታ ጋር በማቀናጀት 'በውክልና ልየታ' (ፕሮክሲ ሚን ቴስት) ዘዴ አካቷል[30]፡፡

'ፕሮክሲ ሚን ቴስት'ዘዴ ለማህበረሰብ ልየታ ተጨማሪ ዘዴ ሲሆን፤ የልየታ ግድፈቶችን እንደሚቀንስ ይጠበቃል፡፡ ተፈጻሚ የሚሆነው አንድ ቤተሰብ በማህበረሰብ ልየታ ሂደት ሲጠቆም ነው[31]፡፡ እነዚህ ልምዶች ለብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ልየታ ስርዓት ትምህረት ይሆናሉ[32]፡፡ የአዲሱ ስርዓት ወጪ ከፍተኛ ይሆናል ተብሎ ቢገመትም፤ የልየታ ግድፈቶችን ስለሚቀንስ መንግስት ላይ የሚስከትለው የረጅም እና መካከልኛ ጊዜ ወጪ አነስተኛ ይሆናል፡፡

(4) **ምስጢራዊነትና መረጃ የማግኘት መብት፡-** በአንድ በኩል የመረጃ መጠበቅ እና ምስጢራዊነት ጉዳዮች በጥንቃቄ ሲያዙ ስለግለሰብ ወደ ህዝብ እንዲደርሱ ለሚደረጉ መረጃዎች ላይ ገደብ ሊጣል ይችላል፡፡በሌላ በኩል በአዋጅ ቁ.590/2000 መሰረት የዜጎች መረጃ የማግኘት መብት መከበር አለባቸው፡፡ አዋጁ ለብዙሃን መገናኛ እና ለግለሰቦች መረጃ የማግኘት መብትን ደንግጓል፡፡

### 3.2 ሁሉን አቀፍ እና የወደፊት ፍላጎትን ያካተተ

በማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች መካከል ትስስር በመፍጠር ያለውን አቅም ሙሉ ለሙሉ ሥራ ላይ ማዋል አልቻለም፡፡ ወደፊት የእነዚህን ትስስር በማጠናከር የሚደረገውን ድጋፍ ውጤታማነት መጨመር ይቻላል፡፡ ጠንካራ ትስስር ተጠቃሚዎችን ከአንዱ የድጋፍ ዓይነት ወደ ተሻለው የድጋፍ ዓይነት (ለምሳሌ ከ ማህበራው ድጋፍ ወደ የስራ እድል ፈጠራና ኑሮ ሁኔታ ማሻሻያ) ለመሸጋገር ያስችላቸዋል፡፡ አልፎም ወደ ገበያ ተኮር እና መድህን አገልግሎት ይሸጋገራሉ፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ከእርዳታ የወጡ ቤተሰቦች ወደ ድህነትና ተጋላጭነት የመመለስ እድላቸው አናሳ ይሆናል (ሰንጠረዥ 3.3 ይመልከቷል)፡፡

በስፋት የሚሰማሩት የማህበራዊ ሰራተኞችና የበጎ ፈቃደኞች ለከፋ ችግር ተጋላጭ ከሆኑ ሰዎች ጋር በመስራት እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ያግዛሉ፡፡

ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የሚያስፈልገው ተገቢ አገልግሎት በሁሉም የትኩረት አቅጣጫዎች እንዲቀረጽ ያደርጋሉ፡፡ በማህበራዊ ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራሞች እና በኑሮ ሁኔታ ማሻሻያ ድጋፍ መካከል ትስስር ይጠናከራል፡፡ ይህም ድጋፍ የሚደረግላቸው ቤተሰቦች ከማህበራዊ እርዳታዎች እንዲወጡ አቅማቸውን ይበልጥ የሚያጎለብት ነው፡፡ ቤተሰቦች ይበልጥ ምርታማ የሚሆኑበትን አቅጣጫ ሲይዙ ለከፍተኛ ስጋት እና ለአደጋ የመጋለጣቸው ሁኔታ ስለሚጨምር የተገኘው ትርፍ በቀላሉ ሊጠፋ ይችላል፡፡ ስለዚህ የጤናና አነስተኛ መድን ዋስትና አገልገሎቶች ጋር እንዲተሳሰሩ ይደረጋል ፡፡

### 3.3 ከፕሮግራም ድጋፍ መውጣት/Graduation/

ከፕሮግራም ድጋፍ መውጣት ማለት ተጋላጭ ቤተሰቦችን ከድጋፍ ተቀባይነት ወደ ሥራ ፈላጊነት፣ ሥራ ፈጣሪነት (ወይም ሁለቱንም) የማሸጋገር ሂደት ነው፡፡ በስዕል 1 እንደሚታየው ለከፋ ድህነት ተጋላጭ የሆኑ ቤተሰቦች ለማህበራዊ ድጋፍ (በዋናነት ጥሬ ገንዘብ) የዕለት ፍጆታ ፍላጎታቸውን እንዲያሚሉ ይደረጋል፡፡ እንዲቆጥቡ ይበረታታሉ፤ የንግድ ክህሎት ሥልጠና ይሠጣቸዋል፡፡ በተጨማሪ በዋነኛነት እንስሳት በማርባት ወይም በማድለብ አነስተኛ ንግድ ፈጠራ መጀመር የሚያስችላቸውን የጥሪት ማስተላለፍ ድጋፍ ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚያም የብድር እና ማይክሮ-ኢንሹራንስን ጨምሮ የኑሮ ሁኔታን ለማሻሻል የሚያግዙ የገንዘብ ድጋፎች ያገኛሉ፡፡

ይህን ሁኔታ በስዕል ለመግለጽ ያህል፤ ስዕል 1 በግል ሥራ በመሰማራት ከፕሮግራም ድጋፍ የመውጣት ጎዳና ሲሆን ስዕል 2 የሚያተኩረው የክህሎት ሥልጠናን ከሥራ ጋር በመዛመድ (ምሳሌ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ አናጺነት) በሚፈጠረው የስራ ዕድል ተጠቅሞ ከፕሮግራም ድጋፍ የመውጣት ጎዳን ያሳያል ፡፡

ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ምሥጋና ይግባውና ኢትዮጵያ ከማህበራዊ ድጋፍ የመውጣት ሀሳብን በማራመድ ልምድ አግኝታለች፡፡ነገር ግን አሁንም ከድጋፍ የሚወጡት ሰዎች ብዛት ግን የታሰበውን ያህል አይደለም፡፡ ከማህበራዊ ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራሞች መውጣት ተጠቃሚዎችን የጥገኝነት አስተሳሰብ እንዳያዳብሩ ያበረታታል፡፡ ይህም ፕሮግራሙ ድጋፉን በጣም ለሚፈልጉት ወይም ያለ ፕሮገራሙ መኖር የማይቾሉት ላይ እንዲያተኩር ያደርጋል፡፡ የማህበራዊ ጥበቃ ስትራቴጂው ይህንን መርህ ወደፊት በማራመድ ይበልጥ ሥልታዊ/ፈጠራዊ እነዲሆን ያደርገዋል፡፡

*ስዕል1፡ የራስን ሥራ በመሥራት ከዕርዳታ መውጣት32*




*ስዕል 2፡ የሥራ ዕድል በማቅረብ አማካይነት ከዕርዳታ መውጣት፡-*



ከድጋፍ የመውጣት ሂደትን ለማፋጠን ትስስሩን በብዙ ደረጃዎች ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ በፌደራል እና በክልል ደረጃ አዲስ ፕሮግራሞች ይቀረጻሉ፤ ሥራ ላይ ያሉትም ከሌሎች ጋር ይበልጥ እንዲሳለጡ ተደርገው ይሻሻሉ፡፡ ድሃና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን/ቤተሰቦችን/ በመለየት ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች በብዛት ባሉበት ቦታ፣ መለያ መስፈርቶች እና ሂደቶች (በሙሉ ወይም በከፊል) እንዲቀናጁ ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ ማህበራዊ ሴፍትኔት እና ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድን ዋስትና የጋራ መስፈርት እና ሂደት እንዲኖራቸው ጥረቶች ያደርጋሉ፡፡ ይህም ደሃና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ ቤተሰቦችን ለመለየት ያስችላል፡፡

በወረዳ፤ በቀበሌ እና ማህበረሰብ ደረጃዎች በተለይም በጽ/ቤቶችና በኮሚቴዎች መካከል ተግባራዊ መረጃዎችን መለዋወጥ ስርአት መዘርጋት የድጋፉን ውጤታማነትና ብቃቱን ለማሻሻል ይረዳል፡፡ የተለያዩ ማህበራዊ ጥበቃ ፕሮገራሞቸ የሚጠቀሙትን በአንድ ወጥ ምዝገባ /single registry/ ስር ማድረጉ የባለድርሻ አካላት የጋራ ጥረታቸውን ውጤታማ በሆነ መልኩ ማሻሻል እንዲችሉ ያደርጋል፡፡

### 3.4. ተጠያቂነት እና ተግባቦት (ኮሙዩኒኬሽን)

መንግስት በተለያዩ ደረጃዎች የማህበራዊ ጥበቃ ተጠያቂነት ሥርዓትን ይዘረጋል፡፡ ይህም የሚከተሉትን ለማረጋገጥ ይረዳል፡-

(1) የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራም ተሳታፊዎች እና ተሳታፊ ያልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የፕሮግራሙን አላማዎች እና መስፈርቶች ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ተጠቃሚዎችን በመለየት እና ፕሮግራሙን በማስተዳደር ተገቢውን ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ፤

(2) ሠማጉሚ በማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት እንደ መሪ መስራያቤትነቱ የዜጎችን ቻርተር ያሳውቃል፡፡ይህም ቻርተር በማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት ሰጭዎች እና በዜጎች መካከል ውል ይመሰርታል፤ ተግባር እና ኃላፊነቶች ያስቀምጥ እና በተገቢው ቋንቋዎች እና ሁኔታዎች ያስተዋውቃል፡፡

(3) ተጠቃሚዎች የደንበኛ ካርዶች ይይዛሉ፡፡ ስለዚህም ሊያገኟቸው ስለሚገባቸው አገልግሎቶች ሙሉ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

(4) ዋና ዋና ፕሮግራሞች ሁሉ ከልየታ ስርዓት ገለልተኛ የሆነ ይግባኝ እና ቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት ይኖራቸዋል፡፡ የፕሮገራም ተሳታፊ እና ተሳታፊ ያልሆኑ ሰለዚህ ስርዓት በቂ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

(5) ቅሬታዎች ክትትል ይደረግላቸዋል፡፡ ግብረ መልስ ለቅሬታ አቅራቢዎች ይሰጣቸዋል፡፡ ለቅሬታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲኖር ያደረጋል ፡፡

(6) በማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓቱ ዙሪያ ድክመቶች ላይ መረጃ (ከተጠቃሚዎች እና ተጠቃሚ ካልሆኑት) ይሰበሰባል፣ ይተነተናል፡፡ ይህም ፕሮግራሞቹን በመቅረጽና በመተግበር ረገድ ተገቢውን መሻሻሎች እንዲያደርጉ ለውሳኔ ሰጭዎች የሚያግዝ መረጃ ይሆናል፡፡

እነዚህ ስልቶች በልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም እና መሠረታዊ አገልግሎቶች ጥበቃ ፕሮግራም በሥራ ላይ ናቸው፡፡

ውጤታማ ተግባቦት (ኮሚዩኒኬሽን) ለተጠያቂነት ዋነኛው የማዕዘን ድንጋይ ነው፡፡ የመረጃ ተደራሽነትን ያረጋግጣል፡፡ ትምህርታዊ መዝናናትን በመጠቀም የባህሪ ለውጥ ለማምጣት ይረዳል (ለምሳሌ የጨቅላ ህፃናትን አመጋገብ ልማድ በማሻሻል ወይም የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን በማሳደግ)፡፡ በአጠቃላይ ህዝቡ ስለ ማህበራዊ ጥበቃ ግንዛቤ እና ድጋፍ በማሰባሰብ ተግባቦት (ኮሚዩኒኬሽን) አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ስትራቴጂ የገጽ-ለገጽ ተግባቦት መጠቀም ብቻ ሳይሆን በከተማ እና በገጠር አካባቢዎች ለበርካታ አድማጭ እና ተመልካች ለመድረስ የቴሌቪዥን፣ የራዲዮ እና የተንቀሳቀሽ ስልክ ሰርፆ መግባት ከግምት ውስጥ ይገባል (በአሁን ወቅት በትንንሽ ከተሞች 60 በመቶ እና 24 በመቶ በገጠር አካባቢዎች አንድ አባል አንድ ተንቀሳቀሽ ስልክ አለው ተብሎ ይገመታል[34] )

ብሄራዊ አንድ ወጥ የምዝገባ ስርዓት መዘርጋት ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡ የማህበራዊ ሠራተኞች ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ፍላጎት ተገቢ የሆኑና የተቀናጁ ድጋፎች ለማቅረብ የሚያስችል የገንዘብ፣ የቴክኒክና ማህበራዊ ድጋፍ ጥያቄ ለማቅረብ ያስችላቸዋል፡፡ በቀበሌ ደረጃ ያሉ ባለድርሻ አካላት ለአንድ ቤተሰብ በተመሳሳይ ፕሮግራም ያልታቀደ ተደጋጋሚ ጥቅሞች እንዳይሰጡ ለመለየት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም የሚሰጡ ድጋፎች የቤተሰብ ሁኔታን ለውጥ ያገናዘቡ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ ባለድርሻ አካላት ተጠቃሚዎች ከሚደረግላቸው የማህበራዊ ድጋፍ የሚወጡትን በቀላሉ በመለየት አስፈላጊውን ጥሪት፣ ሥልጠና በመሥጠት እና ለሥራ ዕድል ድጋፍ ማትጊያ በመስጠት ከማህበራዊ ድጋፍ የሚወጡበትን ማፋጠን ይችላሉ፡፡በመጨረሻ ብሄራዊ አንደ ወጥ ምዝገባ ከእነዛ እስከ ዛሬ ያልወጡት (ለመውጣት የማይችሉትን) እና ረዥም/መካከለኛ ጊዜ ማህበራዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን በግልጽ ለመለየት ይረዳቸዋል፡፡

### 3.5 በፆታ፣ እድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት እና ኤች አይቪ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ትኩረት ሰጥቶ ማካተት

በማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ውስጥ ተጠቃሚዎችን በምናካትትበት ወቅት የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለብን፡፡

- ድህነትን እና ተጋላጭነት በፆታ፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳተኝነት እና በሌሎች ጉዳዮች በቤተሰቦች መካከል እንዴት እንደሚለይ (ምሳሌ በአባወራ እናበ እማወዋራ በሚመራ ቤተሰብ መካከል[35])፤
- የማህበራዊ ጥበቃ ድጋፍ የተለያዩ ቡድኖች ያላቸውን ሚና፣ ኃላፊነቶችና ተግዳሮቶች ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡

ውጤታማ ማካተትን ለማምጣት ድጋፍ በሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች በሁሉም ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ መረጃ በፆታ፤ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳተኝነት፤ በጤና እና በኑሮ ሁኔታ አቅጣጫዎች እና በሌሎች ማህበራዊ ደረጃዎች በዝርዝር መደራጀት አለበት፡፡ ተጠቃሚዎች ስለሚደረግላቸው የማህበራዊ ጥበቃ ሁኔታዎች በተገቢው መንገድ መረጃ ያገኙ መሆኑን ለማረጋገጥ የተለየ ጥረት የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ይህም የሚገባቸው ድጋፍ ላይ ውሳኔ የመሥጠት ሂደት ውስጥ ተሳትፎአቸውን ከፍ ያደርገዋል፡፡ ውጤታማ ማካተት በሁኔታና በፕሮግራም ዓይነት ስለሚለያይ፣ ለማረጋገጥ የሚከተሉት ተግባራዊ እርምጃዎች ይወስዳሉ፡፡

- ማህበራዊ ድጋፎችን በይዘት ወይም በቅርጽ የተለያዩ ቡድኖችን ተጨባጭ ሁኔታ/ፍላጎቶች እንዲያንጸባርቁ ማድረግ፤
- አገልግሎቱ በሚሰጥበት ቦታና ሰዓት ላይ ትኩረት በመስጠት አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ፤
- ድጋፉን ለቤተሰቡ መሪ ከመስጠት ይልቅ ይበልጥ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ በቀጥታ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ከኤች አይቪኤድስ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ወይም ለተጋላጭ አረጋውያን መስጠት፡፡

- ውሳኔ ሰጭ ኮሚቴዎች ሥርአተፆታ እኩልነት፣የአካል ጉዳተኞችን ያካተተ እና ሁሉንም የእድሜ እርከኖች አካቶ እንዲዋቀር ማድረግ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ልዩ ንዑስ ኮሚቴዎችን የተለዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ትኩረት በማድረግ ማቋቋም፡፡

ዝርዝር ጉዳዮች እንደ ፕሮግራሙ/ድጋፉ ሁኔታ ስለሚለያዩ፣ ዝርዝር ምሳሌዎችን ለእያንዳንዱ ፖሊሲ ትኩረት አቅጣጫ ላይ ከዚህ በታች በክፍል 4 ቀርቧል፡፡ ተጨባጭ ሁኔታዎችን መሰረት ያደረገ የማካተት የድርጊት መርኃ ግብር በእያንዳንዱ ክልል እና ወረዳ በሚመለከታቸው ቢሮዎች እና ጽ/ቤቶች የሚቀረጽ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት፡ እስትራቴጂዎችና የማስፈፀሚያ መሳሪያዎች

ቀደም ሲል የቀረቡት አምስት የትኩረት አቅጣጫዎች በኢትዮጵያ ማህበራዊ ጥበቃን ለማስፈን መሰረታዊ መዘውር ናቸው፡፡ በዚህ የእስትራቴጂ ሰነድ እንደተብራራው እነዚህ የትኩረት አቅጣጫዎች ለየብቻቸው ተነጣጥለው የሚታዩ አይደለም፡፡ በአንድ የትኩረት አቅጫጫ ድጋፍ የሚያስፈልገው የህብረተሰብ ክፍል በሌላው የትኩረት አቅጣጫ የሚደረግ ድጋፍ ሊያስፈልገው ይችላል፡፡ ለምሳሌ በትኩረት አቅጣጫ 1 በቅድመ ሁኔታ እና ያለቅድመ ሁኔታ ድጋፍ የሚያስፈልገው የህብረተሰብ ክፍል የህግ ድጋፍ፣ ከጥቃት እና ከብዝበዛ የመጠበቅ ድጋፍ ሊፈልግ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ በትኩረት አቅጣጫ 2 የኑሮ ሁኔታ የማሻሻል ተግባራት ሊያጋጥም የሚችለውን ስጋት ለመቀነስ የማህበራዊ መድን ዋስትና ተደራሽነት (ትኩረት አቅጠጫ 3) ያስፈልገዋል፡፡ ይህ ግንዛቤ በተለይ የድርጊት መርኃ ግብር በሚቀረፅበት ጊዜ እና በህብረተሰቡ ደረጃ ለአስፈፃሚዎች አስፈላጊ ነው፡፡ በእያንዳንዱ የትኩረት አቅጣጫ ቢያንስ ሁለት ቁልፍ የማስፈፀሚያ መሣሪያዎች ከዚህ በታች በሰንጠረዥ 5 እና በክፍል 4-2 እስከ 4-6 ቀርበዋል፡፡

### 4.1. ራዕይ፣ ተልእኮና የፖሊስ ዓላማዎች

ይህ ብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ እስትራቴጂ የተቀረፀው በብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ የተገለጹትን ራዕይ፤ ተልዕኮና ዓላማዎች ስራ ላይ ለማዋል ነው፡፡ አስፈጻሚዎች ሁለቱን ሰነዶች በአንድ ላይ እንደአስፈላጊነቱ እንዲጠቀሙ ይመከራሉ፡፡ እንደአስፈላጊነቱ የድርጊት ፕሮግራሞች፤ መመሪያዎች ማኑዋሎች ሊቀረጹ ይችላሉ፡፡

**ሰንጠረዥ 5፡ ለትኩረት አቅጣጫዎች ቁልፍ ማስፈጸሚያ መሳሪያዎች ሆነው የተለዩ፤**

| **ትኩረት አቅጣጫ1** ልማታዊ ሴፍቲኔትን ያስፋፋል፤ | **ትኩረት አቅጣጫ 2፡** የሥራ ዕድልን ያስፋፋል፤ የኑሮ የኑሮ ሁኔታ ደረጃን ያሻሽላል፡፡ | **ትኩረት አቅጣጫ 3፡**ማህበራዊ መድን ዋስትናን ያስፋፋል፡፡ | **ትኩረት አቅጣጫ 4፡** ለመሰረታዊ አገልግሎቶች ለጤና፤ ትምህርትና ሌሎች ተደራሽነትን ያሳድጋል፡፡ | **ትኩረት መስክ 5፡** በደል፣ ጥቃት፣ ማግለልና ብዝበዛን ለማስወገድ የህግ ጥበቃና ድጋፍ መስጠት፤ |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. ያለሁኔታ ድጋፍ ማድረግ፤ | ሀ/ በእርሻ ላይና ከዕርሻ ውጭ የኑሮ መተዳደሪያ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤ | ሀ/አስገዳጅ ማህበራዊ ዋስትና፤ | ሀ/ ማህበራዊ ድጋፍ ለሰው ሀብት ካፒታል ልማት፤፡ | ሀ/ባደልናብዝበዛን ለመከላከልተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) |
| ለ/በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ማህበራዊ ድጋፍ | ለ/የስራ አገልግሎትና ደረጃዎች፤ | ለ/ ከአየር ለውጥ ጋር የተገናኘ መድን ዋስትና ፤ | ለ/ የጤና መድን ዋስትና በነፃ ወይም በድጎማ በመስጠት፤ | ለ/ከቤተሰብ ውጭ ድጋፍና እንክብካቤ ለተለያቸው ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ/ |
| ሐ/ የህዝብ ስራዎች፤ | ሐ/ የገንዘብ ድጋፍ አገልግሎቶች መስጠት | ሐ/ የህይወት መድን ዋስትና፤ | ሐ/ የማህበራዊ ስራ ሥርዓት ማቋቋም፤ | ሐ/ የፖሊሲና የሕግ ሽፋን፤ |
| መ/ የአደጋ ወቅት ምላሽ ስልቶችን ማሳደግ፤ | | መ/ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድን ዋስትና፤ | መ/ ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳት ችግር ላለባቸው ተደራሽ ማድረግ.. የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቻው አገልግሎት መስጠት፤ | መ/ ብዝበዛ የተፈፀመባቸው ጥቃት ለደረሰባቸው ለተገለሉና ብዝበዛ ለተፈፀመባቸው ተጎጂዎች ች ድጋፍ መስጠት፤ |
| | | | ሠ/ የትምህርት ቤት ምገባ | ሠ./ በማዕከላትና ለዕደላ አመች በሆነ መስመር ላይ መስጠት፤ |
| | | | | ረ/ የልዩ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጭዎች ኔትወርክ ማቋቋም፤ |

### 4.2. የትኩረት አቅጣጫ 1፡ ልማታዊ ሴፍቲኔት ማስፋፋት

#### 4.2.1. ዓላማዎች

በብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ እንደተጠቀሰው የልማታዊ ሴፍቴኔት ፕሮግራም ስትራቴጂካዊ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጮች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ማህበራዊ ድጋፍ ማስፋፋት እንዲሁም እነዚህን ዜጎች ወደ ፍፁም ድህነት እንዳይወድቁ ለመከላከል፤
- በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉትን ሕፃናት፣ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ከድህነት ለማውጣት ድጋፍና እንክብካቤ መስጠት፤
- ድጋፍ እና እንክብካቤ ለሌላቸው አረጋውያን የማህበራዊ ሴፍቴኔት ሥርዓት ማቋቋም፤
- የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የማህበረሰቡን ጥሪት ለማሳደግ የማሕበረሰብ ጉልበት ስራ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት ናቸው፡፡

በተጨማሪም በዚህ የትኩረት አቅጣጫ የሚደረጉ ድጋፎች መሠረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ያረጋግጣሉ፡፡ ለምሳሌ ትምህርት እና ጤና በእጅ ያሉ ጥሪቶች እንዳይሚጠጡ መከላከል እና የምግብ እና ሌሎች አገልግሎቶች ፍላጎትን በማጠናከር ገበያን ማነቃቃት፡፡

#### 4.2.2. ቁልፍ የማስፈፀሚያ መሳሪያዎችና ድጋፎች

የብሔራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ ለተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች አስቀድመው የሚታወቁ፣ ወቅታዊና በቂ የማህበራዊ ድጋፍ ለማስፋፋት ቁርጠኛ አቋም ወስዷል፡፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ለሚሟላት አራት ቁልፍ የማስፈፀሚያ መሣሪያዎች ቀርበዋል፡-

- ያለ ቅድመ ሁኔታ ማህበራዊ ድጋፍ ማድረግ፤
- በቅድመ ሁኔታ ድጋፍ ማድረግ (ከሥራ ውጪ ሁኔታዎች)፤
- የማህበረሰብ ጉልበት ሥራዎች፤
- ማህበራዊ ሴፍቲኔት እና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቶች ለአደጋ ምላሽ ፤

እነዚህ ፕሮግራሞች ብሄራዊና አንደ ወጥ የተጠቃሚዎች ምዝገባ ስርዓትን በመጠቀም በከፍተኛ ደረጃ ይቀናጃሉ፡፡ ከዚህ በታች ባለው ክፍል በእያንዳንዱ የማስፈፀሚያ መሳሪያ ሥር የተወሰኑ ጠቋሚ ተግባሮች ቀርበዋል፡፡

##### 4.2.2.1. ያለ ቅድመ ሁኔታ ማህበራዊ ድጋፎችን ማድረግ

በዚህ የማስፈፀሚያ መሳሪያ፡-

- ለድሃና ሥራ ለመስራት ጉልበት እጥረት ላለባቸው ቤተሰቦች በሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች ማህበራዊ ድጋፍን ማስፋፋት ሥራ መሥራት የማይችሉ ቤተሰቦች ሲባል ምንም ሥራ የመሥራት አቅም የሌላቸውን ብቻ ሳይሆን፣ የሕፃናት እና ሌሎች ጥገኞችን ተንከባካቢዎች በማህበረሰብ ስራ ቢሳተፉ፣ እነዚህ ጥገኞች አደጋ ላይ ሊወድቁ

ስለሚችሉ፤ (በአንዳንድ ክልሎች ስራ ላይ ውሎ ከነበረው የሙከራ ማህበራዊ ገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም መልካም ተሞክሮ አለ)፡፡[36]

- ያለመዋጮ ጡረታን ስራ ላይ ማዋል፤ የዚህ ጡረታ መውጫ ዕድሜ አሁን እየተሠራበት ካለው የመደበኛ የጡረታ መውጫ የእድሜ ጣራ እኩል ወይም በላይ ይሆናል፡፡ ትክክለኛው ዕድሜ በወቅቱ በሚኖረው የገንዘብ አቅም የሚወሰን ይሆናል፡፡ ከስትራቴጂው ቀጥሎ የሚዘጋጁት የድርጊት መርኃግብር ወይም የኢንቨስትመንት ማዕቀፍ ላይ የሚብራራ ይሆናል፡፡
- ለተለያዩ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች እገዛ ማድረግ፤ ለምሳሌ ለታዳጊ ሕፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞቸንና ለአረጋውያን፤
- ጉልበት ውሱንነት ያለባቸው ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ዓመቱን ሙሉ የሚደርስባቸውን ችግር ለመቅረፍ ለአሥራ ሁለት ወራት ድጋፍ መስጠት/ማድረግ፤
- የሚሰጠው ድጋፍ እንደ ገበያው ሁኔታ ከገንዘብ ወደ ምግብ ወይም ከምግብ ወደ ገንዘብ የሚቀየር ይሆናል፡፡ ገበያው ምግብ በበቂ ሁኔታ እና የመግዛት አቅም ባገናዘበ ሁኔታ ማቅረብ ከቻለ፣ ገንዘብ ይሰጣል፡፡ ካልሆነ ምግብ ይሰጣል፡፡

#### 4.2.2.2. በቅድመ ሁኔታ ማህበራዊ ድጋፎች ማድረግ

በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም 80 በመቶ ተጠቃሚዎች ለማህበረሰብ ስራ ጉልበት የመስጠት ቅድመ ሁኔታ ሲያሟሉ ይከፈላቸዋል፡፡ በማህበራዊ ጥበቃም ማህበረሰብ ስራ ጉልበት መስጠት ድጋፍ ማግኘት ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በስትራቴጂው ዘመን ሌሎች በቅድመ በሁኔታ ላይ የተመሰረቱ አማራጮች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

- የሰው ሃብት ልማት፡- የተመጣጠነ ምግብ፣ ትምህርት፣ የመከላከል ጤና እንክብካቤ፣ ትምህርት ቤት መከታተል፣ የጎልማሶች መሠረት ትምህርት (የጎልማሳ ትምህርት) ወይም የወጣቶች ክህሎት ማሳደግ፤
- "ለዘብ (ሶፍት)ላሉ ቅድመ ሁኔታዎች ቅድሚያ መስጠት፡- ባለፉት 20 ዓመታት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት የተሻሻለ ቢሆንም፤ በብዙ አካባቢዎች የአገልግሎት ጥራት ተግዳሮት እንደሆነ ነው፡፡ ስለሆነም "ከማክረር" ይልቅ ለዘብ ያሉ ቅድመ ሁኔታዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡ ይኸውም የቅድመ ሁኔታን መሟላት ይበረታታል፣ ክትትልም ይደረጋል፡፡ የቅድመ ሁኔታን ሳይሟላ ሲቀር ምክንያቱን መረዳት እና መፍትሄ መስጠት እንጂ ወደ ቅጣት አይገባም፡፡
- ከግሉ ዘርፍ፣ ከመያዶች/ከሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ጋር አጋርነት መፍጠር፡- በረዥም ጊዜ ውስጥ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ መንግስት ሙሉ ኃላፊነትን ይወስዳል፡፡ ከአጭር እስከ መካከለኛ ጊዜ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ከሲቪል ማህበራት እና ከግል ዘርፍ ጋር አጋርነት የሚጎለብት ይሆናል፡፡
- ማስረጃን መሠረት ያደረገ ድጋፍ- የእያንዳንዱ አማራጭ የሚያስከፍለው ዋጋ እና የሚያስገኘው ጥቅም ይተነተናል፡፡

#### 4.2.2.3. የማህበረሰብ ጉልበት ሥራዎች፡- መጠነኛ የሥራ ዋስትና መስጠት

እስካሁን ድረስ  የማህበረሰብ ሥራዎች መስራት ድጋፍ ለማግኘት እንደ ቅድመሁኔታ ይወሰዱ ነበር፡፡  በዚህ ስትራቴጂ ግን እንደ መጠነኛ የሥራ ዋስትና ማረጋገጫና ማስፈጸሚያ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ የልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ተሞክሮ በተለይ በገጠር አካባቢዎች የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ይህም ማለት፡-

- የማህበረሰብ ሥራዎች ተግባራዊ መሆን በሚችሉበትና ክፍያዎችም በጣም አስፈላጊ በሚሆኑበት ጊዜ መታቀድ ይገባቸዋል፡፡ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ወሣኝ በሆነ የረሃብ ወቅት ተግባራዊ መደረግ ያለበት ሲሆን ከፍተኛ ዝናብ በሚኖርበትና የግብርና እንቅስቃሴ ወቅት ባይሆን ይመረጣል፡፡ የማህበረሰብ ሥራ ማከናዎኛ ጊዜያት በሃገራችን የወቅት መለያየት ማገናዘብ ይኖርበታል፡፡
- የማህበረሰብ ስራዎች የክፍያ ተመን በሚቀመጥበት ጊዜ ፍጆታን ለማሟላት በቂ መሆኑን ማረጋገጥ ይስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ተጠቃሚዎች ከድጋፍ የሚወጡበት መንገድ የሚያበረታታ እና  አቅምን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡ በገበያ ላይ ያለውን የደሞዝ መጠን ያገናዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ፕሮግራም ያለውን ክፍያ ያገናዘበ መሆን ይኖረበታል፡፡
- የፕሮግራሙን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የማህበረሰብ ሥራ ክፍያ በቤተሰብ አባላት ብዛት ይወሰናል፡፡  የሚደረገው ድጋፍ ወጭ ቆጣቢ ስለመሆኑ ተከታታይ ትንተና ይደረግበታል፡፡
- ከልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም፣ ከመሬት/MERET/ ፕሮጀክት እና ሌሎች በደጋማ አካባቢ የሚተገበሩ የማህበረሰብ ሥራዎች የተገኘው ልምድ እንዳለ ሆኖ፣ ማህበራዊ ጥበቃ ፕሮገራሙ ሲተገበር  በቆላ እና በከተማ አካባቢዎች ያሉትን የተለያዩ ዕውነታዎች ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡
- በፕሮግራሙ እና በሌሎች ብዙ ህዝብ ሚያሳትፉ ሥራዎችን በመቅረፅ /በማስተዳደር እና በማሳተፍ ልምድ ካላቸው ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅት ይኖራል ለምሳሌ የእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር፣ ብሔራዊ አደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን፣ የሁሉን አቀፍ የገጠር መንገዶች ተደራሽነት ፕሮግራም፣ የውሃ ሃብትእና ኢነርጂ ሚኒስቴር (በውሃ ላይ)፣ የከተማ ልማት ቤቶች ሚኒስቴር (በከተማ ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም)፡፡
- በዚህ ስትራቴጂ የማህበረሰብ ስራዎች፡-  ከዚህ የሚከተሉት ገጽታዎች ይኖሯቸዋል፡፡
    - የማህበረሰብ ሥራዎች ለከፋ ችግር ተጋላጭ በሆኑ ቤተሰቦች የግል መሬት ላይ ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡
    - በሥነ-ምግብ ተኮር ስራዎች የበለጠ ማራመድ (ለምሳሌ፤- የተለያዩ የተመጣጠኑ ምግቦች በሚያስገኙት ስራ ላይ፤ በንጥረ ነገር የበለፀጉ ሰብሎችን ለማምረት ማስቻል፤ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተደራሽነትን ለሚያስገኙ )
    - በዚህ ስትራቴጂ በትኩረት አቅጣጫ 4 የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የማህበረሰብ ሥራዎች የማህበራዊ አገልግሎትን ተደራሽነት ማረጋገጥ፡፡ ለምሳሌ ተጠቃሚዎች እንደ ማህበረሰብ መምህራን፣ (በከተማ እና ገጠር)፤ በክሊኒኮች /በትምህርት ቤቶች/በቅድመ ትምህርት ማዕከላት ስራ ተጠቃሚዎች እንዲሳተፉ ማድረግ (በተለይ በከተማ አካባቢዎች)፡፡

#### 4.2.2.4. ለአደጋ ምላሽ ሴፍቲ ኔት እና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቶችን ማስፋት

በአደጋ ለተጠቁ ተጋላጭ ሰዎች ውጤታማ እና ቀጣይነት ያለው ድጋፍ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲን ማዕከል ባደረገ መልኩ ይጠናከራሉ፡፡ ይህም ሂደት የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ይጨምራል፡-

- የመጠባበቂያ በጀት እና ለመለስተኛ ክስተቶች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ስልት መዘርጋት፡፡ ይህም ለተረጂዎች የዕርዳታውን መጠን መጨመርና ለሌሎች ተጋላጭ ቤተሰቦች ዕርዳታውን ለማስፋት ጭምር ማለት ነው፡፡
- የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ የተፈጥሮ አደጋዎችን ጨምሮ ከፍተኛ ቀውስ በሚፈጠርበት ጊዜ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ውጤታማ የሆነ ስልት መቀየስ፤
- ማህበራዊ ሴፍቲኔት እና ሰብዓዊ ድጋፍ ሰጪዎች በጋራ ማቀድ እና የተቀናጀ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መሣሪያዎችን መጠቀም፤
- በምግብ እጥረት የተጎዱ ሕፃናት/ ነፍሰጡር እና አጥቢ እናቶች በሴፍቲኔት ፕሮግራሞች ውስጥ በጊዜያዊነት እንዲካተቱ በማድረግ ድንገተኛ የምግብ እጥረት ሁኔታዎችን መከላከል ፤
- በሴፍቲኔት እና በሰብዓዊ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል በአደጋው ሁኔታ ላይ ተከታታይ ግንኙት እና መረጃ መለዋወጥ፡፡
- እነዚህ ሊስፋፉ የሚችሉ የሴፍቲ ኔት ድጋፎች ያለ ቅድመ ሁኔታ ወይም በቅድመ ሁኔታ ሊተገበሩ ይችላሉ፡፡ የፕሮግራሙ ቀረጻ ከመጠባበቂያ ፈንድ ከልማታዊ ሴፍቲ ኔት እና ከ አርብቶ አደር ማህበረሰብ ልማት ፕሮግራም በተገኙ የመጠባበቂያ ፈንድ እና ሌሎች የአደጋ ክስተት መቋቋሚያ ስልቶች ተሞክሮዎችን ያካትታል፡፡

### 4.3. የትኩረት አቅጣጫ 2፡ የሥራ ዕድልን ማስፋፋትና የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል

#### 4.3.1. ዓላማዎች

የትኩረት እቅጣጫ 2 የሚከተሉት ስትራቴጂካዊ ዓላማዎች አሉት፡-

- የሰው ሃብት ልማት ለመገንባትና የኑሮ ሁኔታን ለማሻሻል የኢኮኖሚና ማህበራዊ እርምጃዎች መውሰድ፤
- በከተማ እና በገጠር አካባቢዎች ለተጋላጭ እና ሥራ አጦች የሥራና የገቢ ማስገኛ ዕድሎችን ማስፋፋት፤
- በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ያገጠሙ የትስስር ችግሮችን በማስወገድ፤ የማህበራዊ ድጋፍ ተጠቃሚዎችን ከ ስራ ዕድልና ኑሮ ማሻሻያ ጋር ማስተሳሰር;
- ለከፋ ችግር ተጋላጮች የሚያጋጥማቸውን ወደ ገበያ የመግባት እንቅፋቶችን ለማስወገድ የሥራ ገበያ መረጃን፤ ተገቢ የገንዘብ አቅርቦት አገልግሎትን እና የንግድ ሥራ ዕቅድ ዝግጅትን ጨምሮ የክህሎት ሥልጠና በመስጠት
- የሚሰጠው ድጋፍ በተጋላጭ ቤተሰቦች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ፤ ለተለያዩ በከተማና በገጠር ሁኔታዎች፤ በቆላ እና በደጋ እንዲሁም በተለያዩ የኑሮ መሠረቶች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ከግብርና ውጭ የገቢ ማመንጫ ስራዎች ማስተዋወቅ እና ማስፋፋት ሥራ እና ኑሮ ሁኔታን ለማሻሻል ከሚሰጠው ድጋፍ ሁሉም የዕድሜ እርከኖች፤ ሴቶች እና  ወንዶች መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ፤

- ፈቃደኛ የሆኑ የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን በሥራና በኑሮ ሁኔታ መሻሻል ድጋፍ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ፤
- የህፃናት የጉልበት ብዝበዛን ለመከላከል እና እንዳይከሰት ለማድረግ መከላከያ ማስቀመጥ ናቸው፡፡

### 4.3.2. ቁልፍ የማስፈጸሚያ መሳሪያዎች እና የሚደረጉ ድጋፎች፤

የዚህን የትኩረት አቅጣጫ ዓላማዎች እውን ለማድረግ ሦስት መሰረታዊ የማስፈጸሚያ መሳሪያዎች ቀርበዋል፡-

- በገጠር አካባቢዎች ለሚገኙ በግብርና ሥራ ከግብርና ስራ ውጭ ለተሰማሩ ድሃ እና ተጋላጭ ቤተሰቦች የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤ በከተማ አካባቢ ለሚኖሩ ድሃ እና ተጋላጭ ቤተሰቦች ተመሳሳይ ድጋፍ መስጠት
- ለገጠር እና ለከተማ ሕዝብ የሥራ ዕድል አገልግሎቶችን እና ደረጃዎችን ማውጣት፤
- ለድሃ ቤተሰቦች የፋይናንስ አገልግሎቶች መስጠት፤
- የክህሎት ሥልጠና ጥራት እና አግባብነትን ከቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ተቋማትና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር ማሻሻል፤
- የሥራ ዕድልና የኑሮ ማሻሻል ድጋፍ ለከተማ እና ለገጠር ተጨባጭ ሁኔታ እንዲሁም ለቆላ እና ለደጋ (ለዝቅተኛና ለከፍኛ ቦታዎች) እና ለተለያዩ የኑሮ መተዳደሪያ (ቀጠናዎች) ተስማሚ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

#### 4.3.2.1. በገጠር እና በከተማ አካባቢዎች ለሚገኙ በግብርና ሥራ እና ከግብርና ስራ ውጭ ለተሰማሩ ድሃ ቤተሰቦች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፡-

እርሻና የእንስሳት እርባታ ለበርካታ ድሃ ቤተሰቦች ወሳኝ የኑሮ መሠረት ዋነኛ አካል መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ በእርሻ፣ በእንስሳት እርባታ እና በተፈጥሮ ሀብት ልማት ምክርና ድጋፍ የሚሰጡ ቢያንስ 3 የልማት ሰራተኞች አሉ፡፡ እንዲሁም ግብዓትና ምርት ገበያ ጋር በተያያዘ ምክር የሚሰጥ አንድ የህብረት ሥራ ባለሙያ በየሦስት ቀበሌ ይገኛል፡፡ እነዚህ ተጠሪዎች (ወኪሎች) በእርሻ ሥራ ላይ የተሻለ ክህሎት ስላላቸው የሚያተኩሩት በእርሻ ላይ ነው፡፡ ከእርሻ ውጭ ያሉ ስራዎች ትኩረት አይሰጣቸውም፡፡

- ስለሆነም በዚህ ስትራቴጂ የገጠር/አርብቶ አደር የልማት ሰራተኞች ከእርሻ ስራ ውጭ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ላይ ጭምር ምክር እንዲሰጡ በሚያስችላቸው የቴክኒክ ስልጠና እንዲታጠቁ ይደረጋል፡፡ በአንድ አካባቢ ከፍተኛ ከእርሻ ውጭ የስራ እንቅስቃሴ ካለ፤ በዚሁ ሙያ የሰለጠነ የልማት ሰራተኛ ሊመደብ ይችላል፡፡
- በትጉህ የስራ ዕድሜ ክልል ያሉ ድሃ እና ተጋላጭ ሰዎች ተገቢ የኑሮ ማሻሻል ስራ ላይ የመሳተፍ አቅማቸውን የሚገነቡ ማኅበራዊ አገልገሎቶችን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤
- በገጠርም ሆነ በከተማ አካባቢዎች በአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች (አ.መ.ኢ) ኤጀንሲ አማካኝነት የተጀመሩ የአንድ መስኮት ግብይት አገልግሎትን ማጠናከር እና ማስፋት፤
- በገጠር እና በከተማ የሚካሄዱ ከእርሻ ሥራ ውጪ የሆኑ እንቅስቃሴዎች የሚያጋጥማቸውን የከፋ ማነቆ የተመለከቱ ችግሮች ለመለየት ጥናት ማከናወንና መረጃውን ለቴክኒክ እና የሙያ ትምህርት ተቋማት፤ ኮሌጆች ማካፈል፤ ይህም

የተደራሲዎቻቸውን ፍላጎት የሚያሟሉ የሥልጠና ፕሮግራሞችን እንዲነድፉና የተነደፈውንም እንዲከልሱ ይረዳል፡፡ ለምሳሌ የአካል ጉዳተኞች ለየት ያለ ችሎታ ተለይቶ እንዲታወቅና እንዲዳብር ማገዝን ይጨምራል፡፡

- በግሉ መስክ የተሰማሩ አግባብነት እና ብቃት ያላቸው ድርጅቶች/የሲቪል ማኅበራት ተጋላጭና ልዩነት ለሚደረግባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የንግድ ሥራ ድጋፍ እንዲያደርጉ ማበረታታት፤

**4.3.2.2. ለገጠር እና ለከተማ ሕዝብ የሚሆኑ የሥራ ዕድል አገልግሎቶች እና ደረጃዎችን በተመለከተ**

የሥራ ዕድል ማግኘት ኢትዮጵያ ውስጥ በድህነት ለሚገኙ ሰዎች አብይ ጉዳይ ነው፡፡ ስትራቴጂው ይህን ፍላጎት እንደሚከተለው ያሟላል፡፡

- መሬት አልባ ሥራ አጥ ሰዎች (በተለይም ወጣቶች) በየአካባቢው ከሚገኙ የሥራ ወኪሎች እና ሥራ አፈላላጊ ጽ/ቤቶች በመቅረብ እንዲመዘገቡ ግንዛቤ መፍጠር፤
- በገጠርም ሆነ በከተማ የሥራ ወኪሎች እና የሥራ አፈላላጊ ጽ/ቤቶችን መክፈትና ያሉትንማጠናከር፤
- ሥራ ፈላጊዎች ሥራ ማግኘታቸውን እና የሚያገኙትን ሥራ ፍሬያማነት መከታተል ፤
- የሥራ ዕድልንና የኑሮ ሁኔታ መረጃ መሰብሰብ፣ ማጠናቀር እና መተንተን፤ ውጤቱም የሥራ ዕድልንና የኑሮ ሁኔታ ፕሮጀክቶች ለመቅረጽ ይረዳል፤
- ከመኖሪያ አካባቢያቸው እርቀው ለሚሰሩ ሠራኞች የቁጠባና የሀዋላ አገልግሎት ለማመቻቸት የሚያስችል የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነትን ማመቻቸት፤
- አሠሪዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ ይበልጥ ግልፅ እና ተባባሪ እንዲሆኑ መጠየቅ ሲሆኑ፤ ይህ የሚከተሉትን ያካትታል፡-
    1. አመቺ በሆነው ቦታ ላይ የሥራ ዕድሎችን ለዕይታ ማቅረብ (ለምሳሌ የገበሬ/የአርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት፤ ሕዝብ በብዛት በሚሳተፍባቸው የሕዝብ የሥራ ቦታዎች፣ በትምህርት ቤቶችና በጤና ተቋማት)፤
    2. የሥራ ፈላጊዎችን ዝርዝር በመዝገብ መያዝ፤
    3. ተገቢውን የቅድመ ሥራ/አገልግሎት ሥልጠና እንደ አስፈላጊነቱ ማዘጋጀት፤
    4. ቢያንስ ዝቅተኛውን የሥራ የደህንነት ደረጃ ማሟላት (ሥራ ፈላጊዎችን ከብዝበዛ፣ ከአካላዊ ጉዳት፣ ከመድሎና ማግለል ለመጠበቅ እና የሕፃናት የጉልበት ብዝበዛን ለማስወገድ)
- ወቅታዊ የገጠር የሥራ ፈላጊዎችን የከተማ ሥራ አጦችን በሚሸፍን መልኩ ተደራሽነትን ማስፋት፤
- የሥራ ዕድል መረጃ ለገጠርና ለከተማ አካባቢዎች ሁኔታ የሚያንፀባርቅ ወይም ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል፡፡ አካል ጉዳተኞችና ከኤችአይቪ ጋር የሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚያጋጥማቸው ተግዳሮቶች ተለይተው ቅድሚያ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡
- የገጠርና የከተማ ትስስር በሚከተሉት መንገዶች መፍጠር፡-

1. የገጠር ሰዎች በከተማ፣ የከተማ ሰዎችም በገጠር ሥራ እንዲያገኙ ማስቻል፤ እና
2. በአነስተኛ ከተሞች የሚገኙ ድርጅቶች የገጠር ሰዎች ምን እንደሚያስፈልጋቸው እንዲለዩ ማበረታታትና በዚሁ መሠረት ምርት እንዲመረት ማድረግ፤

- የሥራ ዕድሎችን በማስፋት ረገድ ያሉትን ማዕከላትና ተቋማዊ መዋቅሮች መጠቀም፤ ለምሳሌ፡-

1. የአርሶ/አርብቶ አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከላት (F/PTCs) በየወረዳ ሠራተኛና ማህበራዊ ጽ/ቤት እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ኤጀንሲዎች ድጋፍ የሚደረግላቸው የሥራ ዕድል ማዕከላት ይሆናሉ[37] ፡፡

2. የአሠሪዎች እና የሠራተኞች ማህበራት፣ የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎችና ማሰልጠኛ ተቋማት የሥራ ግብይት ተቋማት ሆነው የማገልገል አቅም አላቸው፡፡

- የሥራ ስምሪት ቁጥጥርን ተቋማዊ የማድረግ እና የማጠናከር ስራ መስራት፡፡

#### 4.3.2.3 የፋይናንስ አገልግሎቶች ለድሃ ቤተሰቦች

በድህነት ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች የፋይናንስ አገልግሎቶችን የመጠቀም ሁኔታ በአሁኑ ወቅት በእጅጉ ዝቅተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ከ 12 በመቶ የሚያንሱ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የማህበረሰብ ሥራ ተሳታፊ ቤተሰቦች ብድር ወስደዋል፡፡ ይህ በከፊል የተደራሽነት ችግር ሲሆን በከፊል ደግሞ የግንዛቤ ችግር ነው፡፡ ተደራሽነቱ በአንፃራዊነት መልካም በሆነባቸው አካባቢዎች እንኳ ፍላጎቱ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በድሃ ቤተሰቦች ዘንድ ያለውን የፋይናንስ አገልግሎቶች አቅርቦትና ፍላጎት ማነቆ ለመፍታት የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

- የየቤተሰቦቹን ክህሎትና በራስ መተማመን ለማሳደግ መሰረታዊ የፋይናንስ ሥልጠናዎችን ማስፋፋት፤
  1. ብድር ከመውሰድ አኳያ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ሴቶች በአሁኑ ወቅት ያነሰ ዝንባሌ ያላቸው እንደመሆኑ መጠን የተለየ ትኩረት የሚሰጣቸው ሲሆን የሥልጠና ስልቶችም የሴቶችን ተሳትፎ ያበረታታሉ፤
  2. ሴቶች ሊገኙ በሚችሉባቸው የቀን ክፍለ ጊዜያት አጫጭር ስልጠናዎች በየመንደሩ ይካሄዳሉ፤
  3. በመስኩ የተረጋገጠ ተሞክሮ ካሏቸው የግሉ ዘርፍ፣ አነስተኛ የብድር ዕና ቁጠባ ተቋማት እና የሲቪል ማህበራት ጋር በጥምረት መስራት፤
- ለቁጠባ እና መዋእለ ንዋይ አትኩሮት መስጠት፤ (1) የገጠር ቁጠባና ብድር ድርጅቶች ለመዋዕለ ንዋይ በይበልጥ እንዲያበድሩ ያስችላቸዋል፡፡ (2) በቤተሰብ ደረጃ የሚያጋጥም የአደጋ ስጋት መከላከል (3) ጥቃቅን ተቋማት እንዲጀመሩ ወይም እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- የቁጠባ ቡድኖችን ማቋቋምና ማጠናከር፡ (ለምሳሌ የመንደር ቁጠባ እና ብድር ማህበራት ወይም የመንደር ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ማህበራት) መመስረት እና ማጠናከር፡፡ እነዚህን ቡድኖች የመደገፍ ተግባር በመስኩ ልምድ ካላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በሚኖር ትብብር አማካኝነት የሚሰጡ ስልጠና፣ ምክር እና አመራር የሚያካትት ነው፡፡
- **እርቀው በሚገኙ አካባቢዎች የሃዋላ አገልግሎትን ማመቻቸት**፡- ሰራተኞች ራቅ ወዳሉ ስፍራዎች ስራ ፍለጋ ሲጓዙ ከሚያገኙት ገቢ የተወሰነውን ትተውት ለመጡት ቤተሰባቸው ያስተላልፉ ዘንድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገር ግን የገንዘብ ማስተላለፊያ አቅርቦቶች በሌሉበት ሁኔታ ሰራተኞች ለዝርፍያ ከመጋለጣቸው ባሻገር አላስፈላጊ ገንዘብ አጠቃቀም (አባካኝነት) የማዳበር ዝንባሌ ያሳድራሉ፡፡ ከባህላዊ የገንዘብ ማስተላለፍ ስልቶች በተጨማሪ ብቅ ብቅ እያሉ የሚገኙት የኢ-ባንኪንግ፣ የተንቀሳቃሽ ስልክ ባንኪንግ፣ ወኪሎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

- **ገንዘብ በሃዋላ የሚደርሳቸው ሰዎች እንዲቆጥቡ እና በሥራ ላይ እንዲያውሉ ማበረታት**፡- በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር ከሚኖሩ ዘመዶቻቸው የተላከላቸውን ገንዘብ የሚቀበሉ የገጠር እና የከተማ ቤተሰቦች[38] ገንዘባቸውን ፍሬያማ በሆነ መልኩ ማለትም ለቁጠባ እና በሥራ ላይ ለማዋል እንዲጠቀሙባቸው አስፈላጊው ቴክኒካዊ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡
- **የቁጥጥር ተግባር የሚካሄድበት ስርዓት** ፡- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ ብሄራዊ ባንክ፣ የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የከተማ ምግብ ዋስትና እና ሥራ ፈጠራ ኤጀንሲ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት በድሃና ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ ላተኮሩ የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚያገለግለውን የቁጥጥር ሥርአት ለማሻሻል በጋራ ይሰራሉ፡፡

### 4.3.2.4 የክህሎት ስልጠናን ጥራት እና አግባብነትን ከቴክኒክ ሞያ ስልጠና ተቋማት እና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር ማሻሻል፡-

መንግስት በኢትዮጵያ ለድህነት ቅነሳ እንዲሁም ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት የሚችል ተወዳዳሪ፣ ተነሳሽነት ያለው ከሁኔታዎች ጋር ሊላመድ የሚችል እና ፈጠራን የተላበሰ ሰራተኛ ሃይል የመፍጠር አጠቃላይ አላማ ያለው የቴክኒክ እና ሞያ ትምህርት እና ስልጠና ስትራቴጂ በሥራ ላይ አውሏል፡፡ የሥትራቴጂው ዝርዝር አላማዎች፡-

1. በየደረጃው ያሉትን የቴክኒክ እና ሞያ ትምህርት ተቋማትን (መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ) ጥራት፣ ማጎልበት እና በሰራተኛ ሃይል ለገበያው ፍላጎት ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉ ማድረግ፡፡
2. ሴቶችንና የገጠር ኗሪዎችን በክህሎት ማብቃት፤
3. የቴክኒክ ሞያ ትምህርት ተቋማት ለሴቶች እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ያላቸውን እኩል ተደራሽነት ማረጋገጥ፤
4. የሥራ ፈጣሪነት ባህልን ማጠናከር እና በተለይም በማደግ ላይ በሚገኙ ክልሎች መደገፍ ፡፡ እነዚህ ከማህበራዊ ጥበቃ እስትራቴጂ ስራንና ኑሮ ማሻሻልን ከሚመለከተው ክፍል ጋር አብረው የሚሄዱ ናቸው፡፡

ስለዚህ የማኅበራዊ ጥበቃ ስርዓቱ ከቴክኒክ እና ሞያ ትምህርት ዘርፍ በጋራ በመስራት ፖሊሲው ለይቶ ያስቀመጣቸውን ይበልጥ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ጥራት እና አግባብነት ያለው ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡
ለዚህም ሲባል **ጥምር የቴክኒክ ኮሚቴ ይመሰረታል/ይጠናከራል**፤ ኮሚቴው ወይም ግብረ ኃይሉ፡-

- ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑና ከተጠቃሚነት ለራቁ/ለተገለሉ የህብረተሰብ ክፍል የሚሆን ተጨማሪ ሃብት ማሰባሰብ እና ለችግሩ መድረስ፤
- በገጠር እና እርቀው በሚገኙ አካባቢዎች (በእርሻ እና ከእርሻ ስራ ውጭ የተሰማሩትን አጠቃሎ) ያለውን የክህሎት ፍላጎት ከማሟላት አኳያ የቴክኒክ ሞያ ትምህርት እና ማሰልጠኛዎች የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ እውቀትን እና ምርጥ አለማቀፋዊ ተሞክሮዎችን ሊያመነጩ የሚችሉ ጥናቶችን ማስጠናት፡፡
- በየጊዜው የሚቀያየረው እና የሚያድገው የሰራተኛ ሃይል ገበያው የሚጠይቀውን ለመሟላት የሚችል፤ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ከፍተኛ ጥራት ያለው የቴክኒክ ሞያ ትምህርት እና ስልጠና መነደፉን ማረጋገጥ፤
- የስራ ገበያን ለማጠናከር እንዲቻል አግባብነት ካሉት ቢሮዎች ጋር አብሮ መስራት፤

- ባሁኑ ወቅት በክልሎች መካከል ያለውን ክፍተት ለማስወገድ ከሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የማህበራዊ ሠራተኞች ደረጃዎችን ማዘጋጀት/ማሻሻል (በተጨማሪም 4.5.2.7ን ከስር ይመልከቱ)

#### 4.3.2.5 እንደአስፈላጊነቱ የሚዘጋጅ የሥራ ዕድል እና የኑሮ ሁኔታ ድጋፍ

በመሰረቱ የኑሮ ሁኔታ በከተማ እና በገጠር ከሚለያይባቸው ምክንያቶች ርቀት፣ ለመሰረት ልማት እና ለመረጃ በሚኖር ቅርበት ይገኙበታል፡፡ በተመሳሳይ በቆላ እና ደጋ (የዝቅተኛ እና የከፍተማ ቦታዎች) በዋነኛነት በግብርና ሥነ ምህዳር እና በማህበራዊ አውታሮች ምክንያት ልዩነት አላቸው፡፡ ይህ መለያት ለተጋላጩ እና ለተገለለው የሕብረተሰብ ክፍል እና ግለሰቦች የሚሰጠው የኑሮ ማሻሻያ ይህን ልዩነት የሚያንጸበርቅ መሆን ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ ለዚህም የማህበራዊ ጥበቃ ሥርአቱ፡-

- ከማህበረሰብ አዉታሮች (መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ)፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪል ማህበራት ጋር በመሆን በዚህ የተለያየ ስርአት ውስጥ ምርጥ ተሞክሮዎችን መለየትና ማስፋፋት፤
- ሴፍቲኔትና ኑሮ ማሻሻያ ጥረቶችን በማቀናጀት ቤተሰቦችን እና ግለሰቦችን ወደዘላቂ መተዳደሪያ እንዲሸጋገሩ መርዳት፤
- እራቅ ባሉ አካባቢዎች ለሚኖሩ ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተስማሚ የኑሮ ማሻሻያ ድጋፎች ከልዩ አስተያየት ጋር (ለምሳሌ ለየት ያለ መመረቂያ፣ መመዘኛና ጊዜ) መንደፍ ወይም ማሻሻል፡፡

## 4.4 የትኩረት አቅጣጫ 3፡ ማኅበራዊ ዋስትናን ማስፋፋት

### 4.4.1. ዓላማዎች

ምንም እንኳን አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት ቢስፋፉ እና በምግብ ዋስትና ፕሮግራም አማካኝነት የተለየ ጥረት ቢደረግም፤ የገጠሩ ህዝብ በአብዛኛው ገንዘብ ተበድሮ በስራ ላይ ማዋል የሚያስከትለውን ኃላፊነት እና ስጋት ይሸሻል[39] ፡፡ ከዚህ አንጻር የስትራቴጂው የማህበራዊ መድን አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የተለያዩ ክስተቶች በህይወት እና በኑሮ ሁኔታ ላይ የሚያስከትሉትን አሉታዊ ውጤቶች ለመከላከል እና ለመቀነስ የሚያስችል የማህበራዊ መድን ስርዓቶችን ማስፋፋት እና ማበረታት፤
- መደበኛ ያልሆኑ የማህበራዊ ጥበቃ ስልቶችን መደገፍ እና ከመደበኛ ስርዓት ጋር የሚኖራቸውን ትስስር ማመቻቸት፡፡

ይህም ቤተሰቦች አስጊ ሁኔታዎችን ባግባቡ እንዲቆጣጠሩ ማስቻል፤ ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኙ የስራ ፈጠራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በይበልጥ እንዲሳተፉ እና የኑሮ ሁኔታን እንዲያሻሽሉ ያበለታታል፡፡ ስጋትን የመቆጣጠር ጉዳይ ከተሰጠው ትኩረት አኳያ ማህበራዊ ዋስትና ከአምስቱ የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል ሰፊውን የአትኩሮት ክፍል ይሸፍናል፡፡

#### 4.4.2 ቁልፍ ማስፈጸሚያ መሳሪያዎችና የሚደረጉ ድጋፎች

የዚህን ትኩረት አቅጣጫ አላማዎች ለማስፈፀም የሚያስፈልጉት የትግበራ መሳሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- አስገዳጅ ማህበራዊ መድን (የጤና መድንን ጨምሮ)፤
- ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድን፤
- የሕይወት መድን፤
- ከአደጋ መከሰት ዕድል /ጠቋሚ/ ጋር የተያያዘ የሰብል/የቀንድ ከብቶች መድን፤
- ፈጠራንና ተስማሚ ቴክኖሎጂ ማስፋፋት፤

በክፍል ሶስት እንደሰፈረዉ ከእነዚህ የትግበራ መሳሪያዎች መካከል አንዳንዶቹ በስራ ላይ ውለዋል ወይም በሙከራ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡

##### 4.4.2.1 አስገዳጅ ማህበራዊ መድን

በአሁኑ ወቅት የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ሰራተኞች ማህበራዊ መድን አገልግሎት አንድ ላይ ሲደመሩ 1.8 ሚሊዮን ሰራተኞችን ይሸፍናሉ፡፡ በሁለቱም ዘርፎች የስራ እድል እያደገ ሲሄድ ለመድን የሚደረገው መዋጮ ይጨምራል፡፡ እነዚህ እየተጣናከሩ ይሄዳሉ፤ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ከማሟላት አኳያ ይበልጥ ፈጠራ የታከሉባቸው ሆነው መቀጠላቸው አይቀርም፡፡ ሰዎች ከግል ወደ መንግስት ከመንግስት ወደ ግል ሥራ የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎችእና በመሳሰሉ የጋራ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ትብብር ይኖራል፡፡

##### 4.4.2.2. አስገዳጅ የጤና መድን ዋስትና

የማህበራዊ የጤና መድን ለመንግስት እና ለግል ዘርፍ መደበኛ ሰራተኞች እንዲሁም ለጡረተኞችና እና በስራቸው ለሚተዳደሩ ሰዎች መሰረታዊ የጤና መድን የሚሰጥ ለየት ያለ አስገዳጅ ማዕቀፍ ነው፡፡ የገንዘብ ምንጩም የአሰሪና ሰራተኛ መዋጮ ሲሆን በኢትዮጵያ የጤና መድን ኤጀንሲ አማካኝነት ይተዳደራል፡፡

##### 4.4.2.3. ማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድን

በርካታ ኢትዮጵያውያን ከፍላጎት እና አቅርቦት አኳያ ባለው ማነቆ ምክንያት፤ የጤናንና የሌሎች እክሎችን ጉዳት ለመቀነስ ከሚያስችሉ የማኅበራዊ መድን ማዕቀፎች ሆነ የቀንድ ከብቶችን ምርትና ምርታማነት የሚያሣድጉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመቀጠል ፈቃደኝነቱ ይጎድላቸዋል፡፡

የህይወት፣ የጤና የሰብል ጥፋትን ያቃለሉ አንገብጋቢ የመድን ሽፋን የሚሹ ስጋቶቻቸውን የሚሸፍኑ አግባብነት ያላቸው የመድን አቅርቦቶች በድህነት ውስጥ ለሚገኙ ቤተሰቦች ከፍ ባለ መጠን ተደራሽነት ይሆንላቸው ዘንድ የማኅበራዊ ጥበቃው ዘርፍ ድጋፍ ያደረግላቸዋል፡፡ ስትራቴጂው በሥራ ላይ ያሉትን የመንግስት ሕጋዊና ተቋማዊ መዋቅሮች የሚያጠናክር ሲሆን አስፈላጊ ከሆነም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በሚኖር ትብብር አማካኝነት በድህነት ውስጥ የሚገኙ ማኅበረሰቦች የመድን አገልግሎትን ማግኘት እንዲችሉ በሂደት ላይ ያሉ አዳዲስ ሀሳቦች ቀጣይነት ላይ ተነሳሽነት ይወስዳል፡፡

መንግስት በገጠርም ሆነ በከተማ ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድን እንዲኖር ሥርአት ዘርግቷል፡፡ የሙከራ ትግበራዎች የተከናወኑ ሲሆን በአዋቂ ዕድሜ ክልል ከሚገኘው ሕዝብ ብዛት ውስጥ 40 በመቶውን (35 ሚሊዮን ሕዝብ) በ2014/15 እ.ኤ.አ እንዲደርስ የሚያስችል ማዕቀፍ እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡

#### 4.4.2.4. የህይወት መድን

- ዕድሮች በሞት የተለዩ ሰዎችን ቤተሰቦች እና ጓደኞች የቀብር ማስፈፀሚያ ወጪን መሸፈንና ስነ ልቦናዊ ድጋፍ የመስጠት ባህላዊ ሚናቸውን እንዲቀጥሉበት መደገፍ፤
- ዕድሮች ሚናቸውን እንዲያሰፉና የህይወት መድን ሽፋንና ሌሎች የክፉ ቀን መጠባበቂያዎችን ለአባሎቻቸው እንዲሰጡ ማገዝ፤፡
- ዕድሮችንና ሌሎች ማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀቶችን ከመደበኛው የመድን ዘርፍ ጋር ማያያዝ፤ እንደ አገናኝ እንዲያገለግሉ ማብቃት፤ ወይም ዕድሮች ጥምረት በመፍጥር ራሳቸውን እንደ መድን ሕብረት ሥራ ማህበራት/ ኩባንያዎች የሚደራጅበት እንዲችሉ ማገዝ፡፡

#### 4.4.2.5. ከአደጋ መከሰት ዕድል /ከጠቋሚ/ መረጃ ጋር የተያያዘ የሰብል/የቀንድ ከብቶች መድን

በክፍል 3 እንደሰፈረው የአየር ፀባይ ለውጥ በምርትና ምርታማነት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ለመቀነስ በርካታ ተጨባጭ ጅማሬዎች በሙከራ ላይ ናቸው፡፡ ከእነዚህ የሙከራ ትግበራዎች የተገኘውን ልምድ እና እንደየተጨባጭ ሁኔታው የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች (ከፍተኛና ተለዋዋጭ መልክ ያለውን የድርቅ አደጋ ስጋትና የመድን ዘርፍ አቅም ውስንነት ጨምሮ) ከግምት ውስጥ በማስገባት በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ጠቋሚዎች ላይ የተመሰረተ መድንን ማጎልበት የሚኖረው አዋጭነት ይመዘናል፡፡ አዋጭ ሆኖ ከታየም የማኅበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ተለይተው ለታወቁ ተቋማዊ ማነቆዎች ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን ለማጎልበቻ እንቅስቃሴዎችም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

#### 4.4.2.6. በአነስተኛ መድን አማካኝነት ፈጠራንና ተስማሚ ቴክኖሎጂን ማስፋፋት

አነስተኛ ገበሬዎች አይሳካልንም በሚል ፍራቻ ምክንያት ከፈጠራ ሥራና ተስማሚ ቴክኖሎጂ ወስደው ከመጠቀም ራሳቸውን የሚገድቡ በመሆናቸው "ስጋት የሚሸሹ" በሚል ቅጥያ ይጠራሉ፡፡ ምንም እንኳን ከእነዚህን ቴክኖሎጂዎች ለአነስተኛ ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች ተደራሽ የማድረግ ኃላፊነት የእርሻ እና የተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር ፤የእንስሳትና አሳ ሀብት ሚኒስቴር እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብብር ሚኒስቴር ቢሆንም የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍም መእነዚህ ተቋማት ጋር በመስራት ተጋላጭ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል ከፈጠራ ስራ እና ከቴክኖሎጂ ማዕቀፎች ውጭ እንዳይሆኑ ያረጋግጣል፡፡

### 4.4 የትኩረት አቅጣጫ 4፡ ለጤና፣ ለትምህርት እና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ያለውን ፍትሃዊ ተደራሽነት ማሳደግ

4.5

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች እና የጤና ተቋማት በሰው ሃይልም ይሁን በቁሳቁስ ረገድ የአካል ጉዳት እና ሌሎች የትምህርት አቀባበል ችግር ያለባቸውን ሕጻናት ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ የተደራጁ ባለመሆናቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህፃናት ከትምህርት ቤት ውጪ ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የጤና ተቋማት ይበልጥ ለአደጋ ተገላጭ የሆኑትን ተቀብለው ለመንከባከብ በአግባቡ የተደራጁ አይደሉም፡፡ ከፍላጎት አኳያ አብዛኞቹ ተጋላጭ ቤተሰቦች መሰረታዊ

አገልግሎቶችን ለማግኘት የግንዛቤ እና የገንዘብ አቅም ያጥራቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የማህበራዊ ጥበቃ ሚና የድሃ ድሃ የሆኑና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች የሚያጋጥሟቸውን ከተደራሽነት ጋር ለተያያዙ ችግሮች ትኩረት በመስጠት ጉድለቱን መሙላት ይሆናል፡፡

### 4.5.1. ዓላማዎች

የትኩረት አቅጣጫ4 አላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው

- ጥራት ያለው  የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለህፃናት እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው አዋቂዎች እንዲደርስ ማድረግ፤
- በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ህፃናትን ትምህርት የማጠናቀቅ መጠን እንዲጨምር አስተዋፅኦ ማድረግ፤ ትምህርት ማቋረጥን መቀነስ፤
- ቅድመ ትምህርት የህፃናት እንክብካቤዎች በሌሉባቸው አካባቢዎች እንዲኖሩ ማበረታታት፤

### 4.5.2. ቁልፍ የማስፈጸሚያ መሳሪያዎች እና የሚደረጉ ድጋፎች

የዚህን የትኩረት 4 አላማዎች እውን ለማድረግ የሚከተሉት መሰረታዊ የማስፈጸሚያ መሳሪያዎች ቀርበዋል፡-

- ለሰው ሃብት ልማት የሚደረግ ማህበራዊ ድጋፍ፤
- ለጤና አገልግሎት ክፍያ ማስቀረት ሥርዓት እና የጤና መድን ድጎማዎች፤
- ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጡ አገልግሎቶች፤
- ለአረጋውያን የሚሰጡ አገልግሎቶች፤
- የት/ቤት ምገባ ፕሮግራም ፤
- ለሕጻናት ጨቅላ ዕድሜ የሚደረግ እንክብካቤ
- የማህበራዊ ስራ ንዑስ ሥርዐት መመስረት፤

#### 4.5.2.1. ለሰው ሃብት ልማት የሚደረግ ማህበራዊ ድጋፍ፡-

የማህበራዊ ድጋፍ ማስፈፀሚያ መሳሪያዎችን በሚመለከት **በትኩረት አቅጣጫ 1** ሥር በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑት ማህበራዊ አገልግሎቶችም ተደራሽ ከማድረግ አንፃርስ ምን ሚና ሊጫወት ይችላሉ? ከአገልግሎቱ ተደራሽነት አኳያ ይበልጥ ውጤታማ ለመሆን ማህበራዊ ድጋፍ የሰው ሃብት ዓላማዎችን ታሳቢ በማድረግ ይቀረፃሉ፡፡ ለምሳሌ ማህበራዊ ድጋፍ  የጤና፣ የትምህርት እና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ከማግኘት የሚያግዱ ኢኮኖሚያዊ እንቅፋቶችን በማስወገድ በፍላጎት በኩል/demand side/ ያሉትን ማነቆዎች ለመፍታት ይችላሉ፡፡ ማህበራዊ ድጋፎች አመጋገብን ሊያሻሽሉ  ይችላሉ፡፡ ለዚህም የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች የሚሰጠው ድጋፍ ነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶችን፤ ከ2 አመት እድሜ በታች የሚገኙ ህፃናትን እና በ ጉልምስና እድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶችን መድረሱን ያረጋግጣሉ፡፡

ምንም እንኳን የኢትዮጵያን ህፃናት የአመጋገብ ስርዓት ደረጃ የሚታወቅ ቢሆንም፤ ማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ሲቀረፁ ለምግብ እጥረት መንስኤ የሆኑ ምክንያቶችን ለመለየት የተሰሩ ትንታኔዎች መሰረት ማድረግ ይሆናል፡፡ የማህበረሰብ የጉልበት ሥራዎች አሉታዊ የሥነ ምግብ ተፅዕኖዎች እንዳያመጡ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የማህበራዊ ድጋፍ ለማህበራዊ አገልግሎቶቹ ተደራሽነት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉባቸው መንገዶች መካከል የተወሰኑ ምሳሌዎች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ***የልየታ መስፈርት***:- የአመጋገብ ስርዓት ችግር ለማሻሻል እና የቅድመ ወሊድ እንክብካቤ እና የህፃናት ክትባቶች አቀባበል ለመጨመር የልየታ መስፈርቶች ነፍሰጡሮች እና ከሁለት አመት በታች ያሉ ህፃናት የሚገኙባቸው ድሃ ቤተሰቦች ላይ ያተኩራሉ፡፡ የትምህርት ውጤታማነት ለመጨመር እና የህፃናት ጋብቻን በመቀነስ የልየታ መስፈርቱ በጉልምስና ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶችን ያካትታል፡፡
- ***ቅድመ ሁኔታን ተፈፃሚ ማድረግ***:- በህፃናት ጤና፣ በሥነ ምግብ፣ በትምህርት ረገድ ውታማነትን ለመጨመር አዳዲስ ቅድመ ሁኔታዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ለምሳሌ የህፃናት ጤንነት እና የሥነ ምግብ ትምህርትን በሚመለከቱ መድረኮች ላይ መታደም ወይም እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት በመደበኛነት ትምህርታቸውን የመከታተላቸው ጉዳይ ላይ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በተጨማሪም የማህበረሰብ ስራዎች ተፈፃሚነታቸው የሚቀጥል ሲሆን በየቤተሰብ አባላት ላይ ያልታሰቡ አሉታዊ ውጤቶች እንዳያመጡ ቁጥጥር ይደረጋል (ለምሳሌ የሴት ልጆች የሥራ ጫና መጨመር እና ከትምህርታቸውመስተጓጎል)፡፡
- ***ግንዛቤ ማሳደግ*** :- የማህበረሰብ ስራ አካባቢዎች እና የክፍያ ጣቢያዎች ጤናን ወይም ሥነ ምግብን፣ ትምህርትን በተመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በአነስተኛ ወጪ ግንዛቤ ለማስጨበጥ መልካም አጋጣሚዎች ናቸው፡፡

### 4.5.2.2. የጤና አገልግሎት ክፍያ የማስቀረት ሥርዓት እና ለጤና መድን ድጎማዎች መስጠት

ምንም እንኳን አነስተኛ የገንዘብ ድጋፍ ያላቸው እና አፈፃፀማቸውን ከክልል ክልል የተለያየ ቢሆንም፤ አሁን በስራ ላይ ባለው የጤና ስርዓት ችግረኞች ከክፍያ ነፃ የሚሆኑበት አሰራር አለ፡፡ በተመሳሳይ በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ማዕቀፎች ውስጥ ችግረኞች የሚከፍሉት አረቦን ድጎማ የተደረገበት እና ግልፅ የልየታ መስፈርት ያለው ቢሆንም ከሽፋኑ አንፃር ሲታይ ግን አሁንም ልዩነት ያለው ነው፡፡

*ተጋላጭ ሰዎች ሁሉን አቀፍ የማህበራዊ ጥበቃ ድጋፍ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ:-*

- ከክፍያ ነፃ የህክምና አገልግሎት (እንዲሁም እየጨመረ የሚሄድ ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድን አረቦን ድጎማ) የሚስፋፋ ሲሆን መልክአምድራዊ ልየታ በመጠቀም የፌዴራል ሃብት (የተረፈው ዘርፍ/አካባቢ የጎደለውን የመደጎም ስርዓት) ድህነት ለተጫናቸው ወረዳዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ድሃና ተጋላጭ ቤተሰቦች ለመሸፈን የሚያስችል በቂ ገንዘብ የሚያገኙባቸውን ሁኔታ ያረጋግጣል፡፡
- የጤና አገልግሎት ክፍያን የማስቀረት አሰራር/የመድን ድጎማ ግልጽ መስፈርት እና ወጥ የልየታ ሂደቶች እንዲኖራቸው ይደረጋል፤ የማህበራዊ ድጋፍ ፕሮግራሞች ጋር እንዲጣጣም ይደረጋል፡፡ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች (የጤና ጥበቃ፣ የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ፣ የእርሻ እና የተፈጥሮ ሃብት እና የከተማ ልማትና ቤቶች) ፤ በመተባበር የጋራ የልየታ መስፈርቶችን እና ሂደቶችን ይቀርፃሉ፡፡ በዚህ አይነቱ ስርዓት ውስጥ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች ከሁለቱም አገልግሎቶች ማለትም በጤና አገልግሎትም በማህበራዊ ድጋፍ የመጠቀም ሰፋ

ያለ ዕድል ይኖራቸዋል ። ይህም የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑት ቤተሰቦች እና ግለሰቦች የሚሰጣቸውን ድጋፍ ለድንገተኛ የጤና እክሎች ከማውጣት ይታደጋቸዋል፡፡ የጤና አገልግሎት ሰጪዎችም ነፃ የጤና አገልግሎት የሚያገኙ ሰዎች የምግብ ፍላጎታቸውን ለመሸፈን የሚያስችል ድጋፍ እንደሚያገኙ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

- በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ያለው የተጠቃሚዎች አንድ ወጥ ምዝገባ ሁሉም ጽ/ቤቶች ለየፕሮግራሞቻቸው የሚፈልጓቸውን መረጃዎች በሙሉ የሚያጠቃልል ሲሆን ይህም በተጠቃሚ ልየታ፣ ክፍያ እና ክትትል የጋራ የማጣቀሻ ሰነድ ሆኖ ያገለግላል፡፡

#### 4.5.2.3. ለአካል ጉዳተኛ የሚሰጡ አገልግሎቶች

አካል ጉዳተኞች የጤና፣የትምህርት አገልግሎቶች እንዲሁም የሥራ ዕድል ከማግኘት አንፃር ለየት ያሉ እንቅፋቶች ያጋጥማቸዋል፡፡ እነዚህም እንቅፋቶች በአብዛኛው በአካል ጉዳተኛነት ጋር የሚገናኙ ሳይሆኑ በአመዛኙ ከአመለካከት፣ ከአድሎ፣ ከማግለል፣ የአካል ጉዳተኞች ያሏቸውን ህገመንግስታዊ መብቶች በብቁ ካለማወቅ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የአካል ጉዳት ያለባቸው ህፃናት ከቤተሰብ ጋር እና በማህበረሰብ ውስጥ ቢኖሩና እንክብካቤ ቢደረግላቸው፤ በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ይህን ለማስፈጸም፡-

- ማህበራዊ ሰራተኞች፣ የህብረተሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች እና፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ስለአካል ጉዳተኞች መብት ስልጠና በመወስዱ እና አካል ጉዳተኞች ዋና ዋና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጉላቸዋል፡
- ማህበራዊ ሰራተኞች ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ተቀራርበው በመስራት እናቶችና ሕፃናት የአካል ጉዳትን ሊያስቀሩ የሚችሉ መሰረታዊ ጤና አገልግሎቶች እንዲያገኙ ያደረጋሉ፡
- ማህበራዊ ሰራተኞች ከት/ቤቶች፣ ከክሊኒኮች፣ ከወረዳ የትምህርት እና የጤና ጽ/ቤቶች ጋር ተቀራርባብው በመስራት አካል ጉዳተኞች የትምህርት ቤት እና የክሊኒክ አገልገሎት እንዳያገኙ የሚያግዷቸው የማግለል፣ በደል እና የተለያዩ አካባቢያዊ እንቅፋቶች እንዲነሱ ያደርጋሉ፡፡ የተበደሉትንም ወደ የሚመለከተው አካል ይመራሉ፡፡
- የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረቶች የማኅበራዊ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ከአካል ጉዳተኞችና ከማህበረሰቦቻቸው ጋር በቀጣይነት ይሰራሉ፡፡
- የመንግስትና የግል አገልግሎት ሰጪዎች (ለምሳሌ የትራንስፖርት፣ የጤና፣ የባንኮች) ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ የሚሰጥ ስርዓት እንዲዘረጉ ይበረታታሉ[40]፡፡
- ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ልዩ አገልግሎቶች ቀጣይነት ባለው መልኩ ይሰፋፋሉ፡-

  - በህይወት ዘመን ሁሉ ሊኖሩ የሚችሉትን የመንቀሳቀስ ተግዳሮቶች ለመቀነስ የፊዚዮቴራፒክ ህክምና ለአካል ጉዳተኛ ሕጻናት መስጠት
  - የእንቅስቃሴ ድጋፎች፡- ሰው ሰራሽ የአካል ክፍሎች፣ ተሽከርካሪ መቀመጫዎችና የመራመጃ ድጋፎች ይሰጣሉ፡፡ በተደራሽነት በገጠር እና በከተማ መካከል ያለው ልዩነት እንዲጠብ ይደረጋል፡፡ ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው የመራመድ ድጋፎች ለሚፈልጉት ሁሉ እንዲዳረስ ይደረጋል፡፡ በሥራ ድል ምንጭነቱም በሃገር ውስጥ እንዲመረት ይበረታታል፡፡

- ልዩ የትምህርት ፍላጎቶችን በተመለከተ ማየት ለተሳናቸው ህፃናት ብሬል፣ መስማት ለተሳናቸው ደግሞ የምልክት ቋንቋ እንዲጠቀሙ ለማድረግ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

#### 4.5.2.4. ለአረጋውያን የሚሰጡ አገልግሎቶች

የእድሜ ባለፀጎች በተለይም ምንም ዓይነት ጡረታ የሌላቸው የጤና እና የትምህርት አገልግሎቶች እንዲሁም የሥራ እድሎችን ለማግኘት ለየት ያሉ እንቅፋቶች ያጋጥሟቸዋል፡፡ እንቅፋቹም ከዕድሜ መግፋት ጋር (አብዛኛውም ጊዜም የመጀመሪያ አይደሉም) የሚዛመዱ ሳይሆኑ በከፍተኛ ደረጃ ከአድሎ፣ ማግለል፣ የዕድሜ ባለፀጎች ያሏቸውን የህገ መንግስት መብት በበቂ ካለማወቅና ከመሳሰሉት የሕብረተሰቡ አመለካከቶች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ አረጋውያን በማህበረሰብ ህይወት ውስጥ ሊሳተፉ በሚችሉባቸው ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች መካከል እንክብካቤ ቢደረግላቸው የተሻለ ነው፡፡ ይህን ለማስፈጸም፡-

- ማህበራዊ ሰራተኞች፡ የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት አገልግሎት እና ዕድሮች ስለአረጋውያን መብትና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ስልጠና ያገኛሉ፡፡ እነርሱም አረጋውያን አብይ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጉላቸዋል፡፡
- በተለይ የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት አገልግሎት በአካባቢያቸው የሚገኙ የእድሜ ባለፀጎችን የኑሮ ሁኔታ በቅርበት በመከታተል ወደጎዳና እንዳይወጡ እና ወደ ልምና እንዳይሰማሩ ያደርጋል ፡፡
- በስትራቴጂው ትኩረት አቅጣጫ 1 እንደተገለጸው፣ በመዋጮ ላይ ያልተመሰረተ ጡረታ መብት በተወሰነ ዕድሜ ክልል ላሉ አረጋዊያን መፈቀዱ የመግዛት አቅማቸውን ከፍ ስለሚያደርገው በጣም አስፈላጊ አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ፡፡
- ምንም ድጋፍ የሌላቸው የዕድሜ ባለፀጎች በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስር በሚካሄደው ከክፍያ ነጻ የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብት ይሰጣቸዋል፡፡
- ፈቃደኝነቱና ችሎታው ያላቸው አረጋውያን ለመረጃ የሚኖራቸውን አቅም ለማሳደግ እንዲችሉ በተግባራዊ የአዋቂዎች ትምህርት እንዲታደሙ ይደረጋል፡፡
- የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት እና ዕድር የመሳሰሉት ማህበራዊ ተቋማት ከአረጋውያንና ከማህበሮቻቸው ጋር በመተባበር አረጋዊያን በማህበረሰብ ጉዳች ላይ ቀጥታ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያመቻቻሉ፡፡
- የመንግስትና የግል አገልግሎት ሰጪዎች (ለምሳሌ ትራንስፖርት፣ ጤና፣ ባንኮች) ለእድሜ ባለፀጎች ቅድሚያ የሚሰጥ ስርዓት እንዲዘረጉ ይበረታታሉ፡፡

#### 4.5.2.4. የትምህርት ቤት ምገባ

መንግስት ለመጀመሪያ ደረጃ እና ለቅድመ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ህፃናት እንዲመዘገቡ፣ ትምህርት እንዲከታተሉ እና ትምህርት የመቀበል አቅም ለማሳደግ፤ የትምህርት ቤት ምገባን ያስፋፋል፡፡ አገሪቱ ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር የትምህርት ቤት የምገባ ፕሮግራሞች የመተግበር ከፍተኛ ተሞክሮ አላት፡፡ በዚህ ተሞክሮ ላይ በመመርኮዝ በአሁኑ ወቅት በትምህርት ሚኒስቴር ብሄራዊ የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም ትግበራ ስትራቴጂ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ የስትራቴጂው

አላማዎችን፣ የተጠቃሚዎችን የመለየት መስፈርቶችን፣ የምግብ መዘርዝሮችን፣ የምግብ ግዢ መመሪያዎችን፣ የአቅርቦት ሰንሰለትን፣ ዋጋን እና ከትምህርት ምገባ የሚጠበቁ ውጤቶችን በመግለፅ ለይቶ ያስቀምጣል፡፡

በዚህ ስትራቴጂ አግባብ ሶስት ጉዳዮች አስፈላጊ ናቸው፡፡ መጀመሪያ፣ በዘርፎች መሀከል የትብብር ስልት ፣ግልጽ ሚናና ኃላፊነት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ማህበረሰቦችን ትምህርትን፣ ጤናን፣ ግብርናን እንዲሁም በትምህርት ቤት ምገባ እና ሌሎችም የጤና ወይም የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ጋር አጠቃላይ ትስስር ያካትታል፡፡ ሁለተኛ፣ ሀገር አቀፍ የምግብ ግዢ፣ የምግብ ደህንነት እና የምግብ ጥራት ቁጥጥር፣ ሥልጠና፣ የማብሰያና የማከማቻ ሥርዓት፣ ቁጥጥር እና ግምገማ ይዘጋጃል፡፡ በየደረጃው ያሉት ፕሮግራሞችም በተቃና መልኩ ለመተግበር በቂ በጀት የተመደበበት ከፌደራል ጀምሮ እስከ ትምህርት ቤት ድረስ የሚዘረጋ መዋቅር ይኖራል፡፡

ሦስተኛ፣ ውጤታማና የተረጋጋ ፕሮግራም ይኖር ዘንድ ለትምህርት ቤት ምገባ የሚውል አገር አቀፍ በጀት የሚመደብበት ሁኔታ ታሳቢ ይደረጋል፡፡ ከመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ከግሉን ዘርፍ እና ከመንግስትን ጥምር የገንዘብ ምንጮች የሚደገፉበት ስልት የሚቀርጽ ዘርፈ ብዙ ማስተባበሪያ መድረክ ይኖራል፡፡

የማህበራዊ ጥበቃ ስትራቴጂ ለትምህርት ምገባ የሚውል ሃብትን (በገንዘብ እና በአይነት) ሙሉ ኃላፊነት ሊወስዱ በሚችሉ ማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት ጥላ ስር ሆኖ ይበልጥ ዘለቄታ ያለውና የማህበረሰብ አቀፍ የት/ቤት ምገባ ፕሮግራም የመሆን ራዕይ ሰንቋል፡፡

#### 4.5.2.6. በህፃናት ጨቅላ ዕድሜ የሚደረግ እንክብካቤ

በህፃንነት ጨቅላ ዕድሜ እንክብካቤ እና ልማት፣ ከቅድመ ወሊድ ጀምሮ እስከ መጀመሪያ ደረጃ መባቻ (በቅድመ ወሊድ እስከ ስምንተኛው አመት ዕድሜ) ድረስ ያለውን የሰው ልጅ የዕድገት ጊዜ ላይ የሚደረገውን እንክብካቤ ያካትታል፡፡ ይህ እንክብካቤ የሕፃንን የግንዛቤ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ ሂደቶች በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ እና በሃገር ደረጃ የሚደረገውን እንክብካቤ ያስተሳስራል፡፡

ይህ የባለብዙ ዘርፎች ጥምረት እንደመሆኑ መጠን የትምህርት ሚኒስቴር፤ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍላ ህፃናት አጠቃላይ ደህንነት በጨቅላነት ዕድሜያቸው ለማረጋገጥ በጋራ የሚሰሩ ሲሆን፤ ጤናማ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ሃላፊነት የሚሰማቸው በዕውቀት የዳበሩ እና ምርታማ የሆኑ አዋቂዎችን ለማፍራት መሠረት ይጥላሉ፡፡

#### 4.5.2.7. የማህበራዊ ሥራ ሠራዊት ንዑስ ስርዓት

መንግስት በጤናና በትምህርት አገልግሎቶችን ለሁሉም በእኩልነት ለማዳረስ የሚያበረታቱ ተስማሚ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ዘርግቷል፡፡ ሆኖም ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑና ከተጠቃሚነት የተገለሉ ሰዎች የቀረቡትን አገልግሎቶች ለማግኘት አሁንም ድረስ ልዩ ድጋፎች የሚፈልጉበት ሁኔታዎች አሉ፡፡ በቀረቡት አገልግሎቶች ተጠቃሚ

ለመሆን የሰለጠኑ ማህበራዊ ሰራተኞች እና የማህበረሰብ ቡድኖች ድጋፍ ያሻቸዋል፡፡ በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሰረት መንግስት፡-

- በሚገባ የሰለጠነ የማህበራዊ ሰራተኛ ያሰማራል
- የማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶችን ይመሰርታል፣ ያጠናክራል፡፡

ይህን ሞዴል በመፍጠር ሂደት ወስጥ የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የማህበራዊ ስራ ሞዴል ማጎልበት ልምድ ትምህርት ይቀስማል[41] ፡፡ ለዚህም አስፈላጊውን መዋዕለንዋይ በሚከተሉት ላይ ይውላል፡-

- ለማህበራዊ ሰራተኞች የሥራ ምደባ ደረጃ ማውጣት፤ የተሟላ ስርአተ ትምህርት እና ተቋማዊ አደረጃጀት፤ ለስልጠናና ለብቃት ማረጋገጫ የሚሆን ተቋማዊ አውታር መመስረት
- የወረዳ የማህበራዊ ሥራ ቡድንን ማስፋፋት፤ በእያንዳንዱ ቀበሌ ቢያንስ አንድ የማህበራዊ ሰራተኛ እንዲኖር ማድረግ
- የማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶችን[42] ሚና ማስፋትና ለሚጨመርባቸው የሥራ ጫና ማበረታቻ የሚያገኙበትን ስልት ማጎልበት
- የማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች የሚሰጡትን ድጋፍ እና አገልግሎቶችን ለሥራቸው በሚያግዝ የጋራ አውታር አማካኝነት ደረጃ እንዲወጣለት ማድረግ
- ለማህበራዊ ሰራተኛና ለኮሚቴዎች/ለማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች ትርጉም ያለው የሥራ ላይ ሥልጠናና የአቅም ግንባታ ማካሄድ
- የደንበኞችን/ተጠቃሚዎችን ለመለየት ሁሉንም አስፈላጊ አገልግሎቶች የሚያገኙበት አካሄድ ለመኖራቸው እና ውጤታቸውን ለመከታተል የሚያስችል ግልፅና ቀላል ሂደቶች ያሉት ጉዳይ (ኬዝ) አያያዝ ሥርዓት እና መመሪያ ማዘጋጀት
- ያሉትን ልዩ አገልግሎቶች ዳሰሳ ማድረግ እና ክፍተቶችን መለየት
- ደንበኞች/ተጠቃሚዎች የተለዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚላኩባቸውን ዕውቅና የተሰጣቸው አጋሮች (ለትርፍ ያልተቋቋሙ እና የግል) መረብ እንዲመሰርቱ እና አገልግሎት ሰጪዎች ዝቅተኛ ተደራሽነት ወደአላቸው አካባቢዎች እንዲሄዱ ማበረታታት (እነዚህ የትኩረት መስክ 4 እና 5 ን የሚሸፍኑ ሲሆን ለአካላዊ/ወሲባዊ ጥቃትና ብዝበዛ ምላሽ በመስጠት ረገድ የተለዩ ባለሙያ የሆኑትን ያካትታሉ)
- የጉዳይ አመራር ሥርዓቱን ከማህበራዊ ጥበቃ የአንድ ወጥ ምዝገባ ስርዓት ጋር የሚያሳልጥ ስልት

## 4.6 የትኩረት መስክ 5፡ ለጥቃት፣ ለብዝበዛ እና ለኃይል ድርጊት ለተጋለጡ ዜጎች ሕጋዊ ጥበቃና ድጋፍ መስጠት

### 4.6.1. ዓላማዎች

የትኩረት መስክ 5 ስትራቴጂያዊ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ጥቃትን (በተለይም የህፃናት ጥቃትን) የኃይል ድርጊትን (በተለይም ፆታን መሰረት ያደረገ የኃይል ድርጊትን) ብዝበዛን ችላ መባልንና መድሎን መከላከል፡፡
- ጥቃት፣ የኃይል ድርጊትና ችላ መባል በሚከሰቱበት ጊዜ ድጋፍ መስጠት
- በሕብረተሰቡ ውስጥ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑትን ለመብታቸው እንዲቆሙ ለማብቃት
- በብዙዎች ባለድርሻ አካላት (የመንግስት ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ኤጀንሲዎች፣ የተወካዮች ምክር ቤት ፍትህና ፖሊሲ) መካከል በትኩረት መስከ 5 ሥር ለሚነሱት ጉዳዮች ዙሪያ በትብብር እንዲሰሩ ማበረታታት፡፡

### 4.6.2. ዋና ዋና የትግበራ መሣሪያዎችና የመፍትሄ እርምጃዎች

በትኩረት መስክ 5 ስር ሁለት ዋንኛ የድርጊት ቋቶች ይገኛሉ፡፡ እነሱም መከላከል እና ፈጣን ምላሽ መስጠት ናቸው፡፡ ለሁለቱም ቁልፍ የሚሆነው ከላይ በክፍል 4.4.2.7 እንደተዘረዘረው የማኅበራዊ ሥራ ሠራዊት ምሥረታ ነው፡፡ የመከላከል እና የምላሽ እርምጃዎች የሚቀረጹት እንደ አካባቢው ባህል፤ በከተማም ሆነ በገጠር የተለያዩ ተጨባጭ ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ ነው፡፡

**በመከላከል ሥር** ያሉት ዋና ዋና ተግባራት  የሚከተሉት ናቸው፡-

- ጥቃትን፣ የሀይል ድርጊትን፣ ችላ መባልን እና ብዝበዛን የመከላከል ተግባቦት/ግንዛቤ ማሳደግ
- ጥበቃን የሚሰጥ የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፍ መፍጠር

**በአፋጣኝ ምላሽ** ስር ያሉት ዋና ዋና ተግባራት  የሚከተሉት ናችው ፡-

- ከኃይል ድርጊት፣ ከጥቃት፣ ከብዝበዛ፣ ከመገለል ለተረፉ ሰዎች የሚሰጥ ድጋፍደህንነታቸው የተጠበቀ የመንከባከቢያ ማዕከላትና ቀጥታ ስልክ አገልግሎት
- ልዩ አገልግሎት ሰጪዎች በይነመረብ መመስረት
- ጥበቃ ካላቸው ቤተሰብ ማዕቀፍ ውጪ ለሚገኙ ሰዎች እንክብካቤ ማድረግ፤

ለእነዚህ የትግበራ (ማስፈጸሚያ) መሣሪያዎች ለእያንዳንዳቸው የሚሆኑ ጠቃሚ የመፍትሄ እርምጃዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

#### 4.6.2.1. ጥቃትን፣ የኃይል ድርጊትን፣ ችላ መባልን መከላከል ዙሪያ ተግባቦት/ግንዛቤ ማሳደግ

ይህን ለማስፈጸም የሰው በሰው እና በመገናኛ ብዙሃን በሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

- በማኅበራዊ ሠራተኞች የሚደገፉ የማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች በሚከተሉት ርዕስ ጉዳዮች ዙሪያ የየማህበረሰባቸውን ግንዛቤ የማሳደግ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡-
- የህፃናት፣ የሴቶች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ከኤች አይቪ ጋር አብረው የሚኖሩ ሰዎች እና ሌሎች ተጋላጭ ሰዎች መብት
- አዎንታዊ ጥበቃን የሚያደርጉ የህፃናት እንክብካቤ ተግባራት

- የህፃናት የጉልበት ሥራ፣ የህፃናት መገለል፣ የህፃናት ዝውውር፣ በህፃናት ላይ የሚፈፀም ኃይል ድርጊት (ወሲባዊ የኃይል ጥቃትን ጨምሮ)፣ የህፃናት በውልደት ጊዜ አለመመዝገብ በስደት ምክንያት የተጠቁ ህፃናት የመሳሰሉ የህፃናት ጥበቃ ጉዳዮች፤
- የአንዳንድ ባህላዊ ድርጊቶች ጎጂ ውጤቶች (በተለይ የህፃናት ጋብቻ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እንዲሁም እንጥል መቁረጥን ጨምሮ)፡፡ ለእነዚህ የመረጃ ልውውጥ መድረኮች በስራ ላይ ያሉትን የሕዝብ መገኛ መድረኮችን በከፍተኛ ደረጃ መጠቀም (ለምሳሌ ለማኅበራዊ ድጋፍ ክፍያ የተሰባሰቡ ተጠቃሚዎች)
- የወረዳ እና የቀበሌ ማኅበራዊ ሠራተኞች በተለይ ለአካባቢ የሀገር ሽማግሌዎች ምክር ቤቶችና፣ በባህላዊ ፍርድ ቤቶች ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎች ጨምሮ በአካባቢያቸው ተፅዕኖ ፈጣሪ ሊሚሆኑ ሰዎች ልዩ የመረጃ መለዋወጫ መድረኮችን ለማካሄድ ይችሉ ዘንድ የማኅበረሰብ እንክብካቤ ማዕከላትን ያግዛሉ፡፡
- መገናኛ ብዙኃን በአንፃራዊነት አነስተኛ በሆነ ዋጋ ለብዙዎች መልዕክት የሚያደርሱ እንደመሆናቸው መጠን ማኅበራዊና ባህላዊ እንቅፋቶችን ለመከላከልና ለመቋቋም ጥቅም ላይ ይውላሉ (በገጠር አካባቢዎች ሬዲዮ በከተሞች ደግሞ ሬዲዮና ቴሌቪዥን)፡፡
- የፈጠራ ፕሮግራሞች (ለምሳሌ ድራማዎች፣ ትዕይንተ ውይይቶች) የሚጎለብቱ እና የሚሰራጩ ይሆናል፡፡ የሚዲያ አይነት ምርጫና የፕሮግራም ይዘት ዝግጅት ጥናትን መሠረት ያደርጋል፡፡ ጥናቱም የተደራሲውን የማዳመጥ ሁኔታ (ከፍተኛ የአድማጭ ቁጥር የሚገኝበት ሰዓት እና በአንድ አካባቢ ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸው የመገናኛ ብዙሃን) ለውጥን ከማምጣት አንፃር እንቅፋቶችንም ሆነ መልካም አጋጣሚዎችን የሚፈጥሩ ማኅበራዊ ባህላዊ ሁኔታዎችን የሚዳስስ ትንታኔ ነው፡፡
- ሥርዓተ ትምህርቱ በትምህርት ቤት የሚገኙ ህፃናት ዕድሜአቸውን በሚመጥን በቂ መረጃ ስለህፃናት ጥበቃ ጉዳዮች ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ይከልሳል፡፡

#### 4.6.2.3. ጥበቃን የሚሰጥ የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፍ

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር፤ እና የፍትህ ሚኒስቴር በአጠቃላይ ጥበቃን የሚሰጥ ህጋዊ ማዕቀፍ ይበልጥ ዳብሮ በሥራ ላይ እንዲውል በተለይ ደግሞ በቤታቸው ጥቃት እንዳደረሰባቸው የሚያመለክቱ ህፃናት እና አዋቂዎች በጊዜያዊነት ደህንነታቸው ተጠብቆ የሚቆይባቸው ቦታዎች (ለምሳሌ ህፃናትን አስጠግተው እንክብካቤ የሚሰጡ አካላት) ስለሚኖሩበት ሁኔታ ህጋዊ መዋቅር እንዲጎለብት በትብብር ይሠራሉ፡፡

#### 4.6.2.4. ማኅበራዊ ሠራተኞችና የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት ከችግሩ ለተረፉ ተጠቂዎች ድጋፍ

ከኢትዮጵያውያን ባህልና ልማድ አንፃር ሲታይ የኃይል ድርጊት፣ የጥቃት፣ የብዝበዛና ችላ የመባል ሰለባዎች አብዛኛውን ጊዜ በደላቸውን አይናገሩም፡፡ የማኅበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች ዕድርን ከመሳሰሉት ባህላዊ መዋቅሮች ጋር በመተባበር የጥቃት ሰለባዎች ጥቃታቸውን እንዲናገሩ በማበረታታት ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫዎታሉ፡፡

- በገጠር የሚኖሩ ከጥቃት የተረፉ ሰዎች ከሕግ አካላት የራቁ በመሆናቸው የማኅበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች ሚና ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ኮሚቴዎች የመጀመሪያ ደረጃ ድጋፍ የሚሰጡ ሲሆን ከፍተኛ ስጋት ያዘሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ብቃት ወዳላቸው ማኅበራዊ ሠራተኞች ይልካሉ፡፡

- ማኅበራዊ ሰራተኞች ሥነ ልቦናዊ ድጋፍ ከመስጠት ባሻገር ከችግሩ የተረፉት ተጠቂዎች ተገቢውን ልዩ አገልግሎት እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው ጋር በቅርበት ይሰራሉ፤ ውጤቱንም ይከታተላሉ፡፡ ለምሳሌ የህክምና አገልግሎት በአፋጣኝ ማግኘታቸውን ከጤና ማዕከላት ጋር፣ ስለወንጀሉ ማመልከታቸውን እንዲሁም ህጋዊ ድጋፍ ማግኘታቸውን በተመለከተ ከፖሊስ ጋር በአገናኝነት ይሰራሉ፡፡
- ማህበራዊ ሰራተኞች በጥቃቱ/ብዝበዛው መፈፀም ማግስትና ከዚያም በኋላ የጥቃቱ ሰለባ የሆኑት/ከጥቃቱ የተረፉ ተጎጂዎች የሕግ አገልግሎት እንዲያገኙ ከፍትህ ሥርዓቱ ያገናኛሉ፤ ሥነ ልቦናዊ ምክር ወደሚሰጡ ልዩ አገልግሎት ሰጪዎችም ይልኳቸዋል፡፡

#### 4.6.2.5. ደህንነታቸው የተጠበቀ የመንከባከቢያ ማዕከላትና ቀጥታ ስልክ አገልግሎት

የእነዚህ አገልግሎቶች ፍላጎት እንዲሟላ የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት ፤ የሰለጠኑ ማኅበራዊ ሠራተኞችና የሪፈራል አገልግሎቶች በህብረት ይሰራሉ፡፡ በከተማና ከተማ ቀመስ በሆኑ አካባቢዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ የማኅበረሰብ እንክብካቤ ማዕከላትና ሀገር አቀፍ የቀጥታ ስልክ ጥሪ አገልግሎት ይቋቋማሉ፡፡

#### 4.6.2.6. ልዩ አገልግሎት ሰጪዎች ህብረት መመስረት

ለተለያዩ ጥቃቶች  ተጋልጠው ከችግሩ ለተረፉ ሰዎች ውጤታማና ተገቢ የህግ፣ የሥነልቦናዊና የሕክምና ድጋፍ ለማድረግ እንዲችሉ ዕውቅና ያላቸው ልዩ የአገልግሎት ሰጪዎች (የሕግ፣ የሲቪል ማኅበረሰብና የግል ዘርፍ) የሚያካትት ህብረት (አውታር) ይመሰረታል፡፡ ህብረቱን የመመስረት ሂደት የሚከተሉት ናቸው፡-ልዩ አገልግሎቶች ዓይነት ዝርዝር ማዉጣት፣ አገልግሎቶቹ መኖራቸውን ማረጋገጥ እና ክፍተት ካለ ማሳየት፤ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መመዘኛ እና ሂደቶች ማዘጋጀት፣ የሙከራ ትግበራ፤ ስምምነት የተደረሰባቸው አገልግሎቶች ለማስፋት የድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀት ያካትታል፡፡

#### 4.6.2.7. ጥበቃ ካላቸው ቤተሰብ ማዕቀፍ ውጪ ለሚገኙ ሰዎች እንክብካቤ ማድረግ

ጥበቃ ከሚደረግላቸው ቤተሰብ ማዕቀፍ ውጪ የሚገኙ ህፃናት፣ አዋቂዎችና አረጋውያን በተለየ የጥቃት ስጋት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ በጎዳና የሚኖሩትን ወይም በተቋማት መጠለያ የሚገኙትን ጨምሮ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትና አዋቂዎች በማኅበራዊ ሠራተኞች የሚጎበኙ እና የሚደገፉ ሲሆን ወደ ልዩ አገልግሎቶችና ደህንነታቸው ወደተሟላ ቦታዎች መላክ (ለምሳሌ ድጋፍ የሚደረግለት የቤተሰብ መልሶ ማገናኘትና ማዋሃድ፣ የዝምድና/ጎሳ እንክብካቤ ወይም መጠጊያ ሰጥቶ መንከባከብ እና ጉዲፈቻ መስጠት)፡፡

መጠለያዎችንና ደህንነታቸው የተጠበቀ ማቆያዎችን ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች ያቋቋሙ ሰብአውያን የሚደነቁ ሆነው የእንክብካቤ ደረጃዎችን እንዲያሟሉ ይጠበቅባቸዋል፤ ቀጣይነትም ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

### 4.7. ማጠቃለያ

እንደ ማጠቃለያ ሰንጠረዥ 6 የትኛው የትኩረት ቡድን በየትኛው የመፍትሄ እርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያሳያል ፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡ አመልካች ድጋፎችን ብሄራዊ ጥበቃ ፖሊሲው ከለያቸው ተጋላጭ ህብረት ክፍሎች**

| ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች | ጠቅለል ያሉ የመፍትሄ አይነት ጠቋሚዎች | የትኩረት አቅጣጫ |
|---|---|---|
| 1. በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ህፃናት (ለምሳሌ ወላጆቻቸውን ያጡ በጎዳና የሚኖሩ ህፃናት) | ትምህርታቸውን መከታተል ይችሉ ዘንድ እንደየሁኔታው የሚወሰኑ ማህበራዊ ድጋፍ (የትምህርት ቤት ምገባን ጨምሮ) | 1 እና4 |
| 2. ተጋላጭ የሆኑ ነፍሰጡር የሚያጠቡ ሴቶች | ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚደረጉ ያልተገደቡ ድጋፎች ፣ የሥራ ዕድልና መተዳደሪያ | 1፣2እና 4 |
| 3. አካላዊና አዕምሮአዊ ጉዳት ያለባቸው ሰዎች፣ ህጻናት | ያልተገደቡ ድጋፍ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አሰጣጥ፣ እንቅስቃሴን የሚጨምሩ መሳሪያዎች አቅርቦት | 1፣4እና5 |
| 4. ያለእንክብካቤ ብቻቸውን የሚኖሩ አረጋውያንና የሚሰጣቸው ድጋፍ | ያልተገደቡ ድጋፍ በመደበኛ (ለምሳሌ በማኅበራዊ ሰራተኞች) እና በማህበረሰብ አቀፍ ስልቶች ለምሳሌ ማህበረሰብ ክብካቤ ህብረት እድር አማካኝነት የሚሰጥ የሥነ ልቦና ማህበራዊ ድጋፍ፡፡ | 1፣4 እና5 |
| 5. ከመስራት የተገቱ ዜጎች በተለይ በሴቶች የሚመሩ ቤተሰቦች | በሕጋዊ ሥራዎች አማካኝነት የሥራ ዕድሎችን መፍጠር፣ ለሥራ ዕድልና ለተሰባጠረ መተዳደሪያ ዕድገት | 1፣2እና5 |
| 6. ለማኞችን፣ በጎዳና የሚኖሩ ልጆችን፣ የወሲብ ንግድ ሠራተኞችን ፣ በዕጽና በሌላ አይነት ሱስ ውስጥ ያሉትን የማህበራዊ ችግር ተጠቂዎች | እንደሁኔታው የሚወሰን ድጋፍ (ለምሳሌ የክህሎት ስልጠና) በሥነልቦናዊ ማህበራዊ ድጋፍ አማካኝነት የሚደረግ ማቋቋሚያ | 1፣4እና 5 |
| 7. በኤች አይቪና በኤድስ እንዲሁም የመሥራት ችሎታቸውን በሚገቱ ሌሎች ጽኑዕ ህመሞች ምክንያት የተጎዱ ዜጎች | እንደሁኔታው የሚወሰኑ በጊዜ የተገደቡ ዝውውሮች፣ የሥራና የመተዳደሪያ ዕድሎች | 1 እና 2 |
| 8. ለሃይል ድርጊትና ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰቡ ክፍሎች | የምክር አገልግሎት፣ ህጋዊ ድጋፍ፣ የሥራና የመተዳደሪያ ዕድሎች እንዲሁም እንደ ሁኔታው የሚወሰኑ በጊዜ የተገደቡ ዝውውሮች | 5፣2፣1 እና 4 |
| 9. ለተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች | ሰብዓዊ እርዳታዎች፣ በሕዝባዊ ሥራዎች የሥራ ዕድሎች፣ ዘላቂ የሥራ ዕድልና መተዳደሪያ | 1፣2 እና 5 |
| 10. ሥራ አጥ የሆኑ መንዶች፣ ሴቶችና ወጣቶች | እንደሁኔታው የሚወሰኑ የገንዘብ ድጋፎች (ለምሳሌ የክህሎት ሥልጠና) ወደሥራና መተዳደሪያ ማስፋፋት እቅዶች በሚደረግ ሽግግር ጊዜ | 1እ2 |
| 11. ያለምንም የመድን ሽፋን መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የተሰማሩ ዜጎች | ማህበራዊና ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድን | 3 |
| 12. የሕገወጥ የሰው ዝውውር ተጠቃሚዎችና ተመላሽ ስደተኞች | የአጭር ጊዜ ድጋፍ ፣ ስነልቦናዊ ማህበራዊ ድጋፍ፣ የሥራ ዕድል መተዳደሪያ | 1፣5፣ እና 2 |

## ክፍል 5 አፈጻጸም (ትግበራ)ና የጊዜ ሰሌዳ

### 5.1. ተቋማዊ ዝግጅት

ይህ ስትራቴጂ ዘላቂ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት የመገንባት ዓላማ አለው፡፡ ይህም የተለያዩ ተቋማትን ጊዜን፣ ሃብትንና ዝግጁነትን ይፈልጋል፡፡ በክፍል 2.4 እንደተቀመጠው በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት ተቋማትን፣ የልማት አጋሮች፣ ሀገር በቀልና አለምአቀፋዊ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራትን ማህበረሰብ አቀፍ መዋቅሮችንና የግሉን ዘርፍ ያካትታል፡፡ እነዚህ አካላት ሲያቀርቡ የነበሩትን አገልግሎት ማቅረባቸውን የሚቀጥሉ ሲሆን ለዚህ የስትራቴጂ ሰነድ ቁልፍ ባለድርሻዎች ናቸው፡፡

ነገር ግን እነዚህ አገልግሎቶች የላቀ ውጤት ለማስመዝገብና ድግግሞሽን ለማስቀረት በሚያስችል መልኩ በቅንጅት መስራት አለባቸው፡፡ የተዋረድና የጎንዮሽ ትብብር ለማጠናከር በቅድሚያ ለሽግግር ጊዜ የሚያስፈልገውን መሰረታዊ አቅም ለይቶ በማስቀመጥ እና በመቀጠልም ለረጅም ጊዜ የሚሆን የአቅም ግንባታ ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡ ውጤታማ የማስተባበር ሥራ በአቅም ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይሆን፤ ለአስተባባሪው አካል የተሰጠው ተገቢ ስልጣናት እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ለማሳተፍ በሚሰጥ ማበረታቻ ላይ ጭምር ነው፡፡ መንግስት አስተባባሪ አካላትን በየደረጃው መድቦ በተዋረድም ሆነ በጎንዮሽ አስፈላጊውን ትብብር ለማግኘት የሚያስፈልጋቸውን ህጋዊ ሥልጣን ይሰጣቸዋል፡፡ የስራ ድርርብ በሚኖርበት ወቅት ባለድርሻ አካላት ከመስሪያ ቤታቸው ጋር ተስማሚ ለሆኑት ስትራቴጂክ የትግበራ መሣሪያዎችና የመፍትሄ እርምጃዎች ቅድሚያ መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ ማበረታቻዎች ይደረጋሉ፡፡

ልማታዊ ሴፍትኔትንና ከመሳሰሉ ተመሳሳይ ፕሮግራሞች የተገኘ ልምድ ለአቅም ግንባታው መረጃ ይሰጣል፡፡ የአቅም ፍላጎቶች ብዙሀን እና ከቀላል ጀምሮ እስከ ውስብስብ ያለውን ክህሎት ያካተቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከሁሉም የሚመለከታቸው ዘርፎች ጋር የተቀናጀ የዘርፍ ሪፖርት ለማዘጋጀትና ውጤታማ የተግባቦት ስልት ለማጎልበት፤ ስብሰባዎችን ማቀድና ማደራጀት የሚችሉ፣ ቃለጉባኤና ሰነዶችን የሚያዘጋጁና ውሳኔዎችን የሚያሰራጩ አቅም ያላቸው ጽ/ቤቶች /ሴክሬታሪያት/ ለከፍተኛ ደረጃ ኮሚቴዎች ያስፈልጋሉ፡፡ መረጃን ወደ አንድ ምዝገባ ቋት ለማስገባት በቀበሌ፣ በወረዳና በክልል ደረጃ የዳበረ የኮምፒዩተር ችሎታ ያስፈልጋል፡፡ መረጃው ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ልዩ እና ቀላል ኮምፒውተር ፕሮግራም /ሶፍተዌር/ በመጠቀም መተንተን ለዘርፎቹ በጋራ ያገለግላል፡፡ ስዕል 3 የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓቱን የማስተባበር ስልት ያሳያል፡፡ በፌደራል ደረጃ አራት የማስተባበሪያ አካላት/ስልቶች ይኖራሉ፡-

- የፌደራል ማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት
- የማህበራዊ ጥበቃ አማካሪ ቦርድ
- የማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያ ክፍል
- የማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያ ክፍልተጠሪ ሰዎች/አስተባባሪዎች

### 5.1.1. የፌዴራል ማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት

ብሄራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ በመንግስት ከፍተኛ ተወካይ ሊቀመንበርነት የሚመራ የፌደራል ማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት ይኖረዋል፡፡ የፌደራል ማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት አባላት ከሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከግብርናና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር፣ ከእንሳሳና ዓሳ ሃብት ሚኒስቴር፤ ከሴቶችና ህፃናት ሚኒስቴር፣ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፤፣ ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ናቸው፡፡ የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፤የግል ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፤ የኢትዮጵያ የጤና መድን ዋስትና ኤጀንሲ፤ የምክር ቤቱ አባላት ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም የአሰሪዎች፣ የሰራተኞች፣ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የተ.መ.ድና ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲዎች፣ የምክር ቤት አበላት ይሆናሉ፡፡ ክልላዊ የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤቶች የፌደራል ምክር ቤት አባላት ይሆናሉ፡፡ የፌደራል ማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤቱ በየዓመቱ ሁለት ጊዜ የሚሰበሰብ ሲሆን ከዚህ በታች የተመለከቱት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

- ***ቁጥጥርና ማስተባበር***፡- የፖሊሲውን፣ የስትራቴጂውንና የተዛማጅ ፕሮግራሞችን አፈፃፀም ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤ ሊሻሻል የሚገባው ነገር ካለ ለሕግ አውጪው አካል ሀሳብ ይቀርባል፡፡
- ***ክትትል፣ ግምገማና ሪፖርት*** ፡- ለማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓቱ ተገቢውን የክትትል የግምገማ ስልቶች ማዘጋጀትና፤ ብቃትን ውጤታማነትን፣ቅልጥፍና ዘገባዎችን መገምገም
- ***የገንዘብ ድጋፍ***፡- ለማህበራዊ ጥበቃ የሚሆን ተገቢ ሀብት እንዲገኝ ምክረ ሃሳብ ማቅረብ
- ***የአቅም ግንባታ***፡- ስትራቴጂውን ለመተግበር የሚያስችል ተገቢ አቅም መኖሩን ማረጋገጥ

### 5.1.2. የፌደራል ማኅበራዊ ጥበቃ አማካሪ ቦርድ

ቦርዱ ቴክኒካዊ ደረጃ ያለው ኮሚቴ ነው፡፡ በማህበራዊ ጥበቃ መድረክ/ፕላትፎርም/ ተሞክሮ ላይ በመመርኮዝ የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን የማስፈጸም ሃላፊነት ካለባቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የሚውጣጡ ከፍተኛ የቴክኒክ ባለሙያዎችንና የልማት አጋሮችን፣ የሲቪል ማህበረሰብና የግሉን ዘርፍ ተወካዮችን ያካትታል፡፡ አማካሪ ቦርዱ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲኤታ የሚመራ ሲሆን በምክትልነት ደግሞ የልማት አጋሮች ተወካዮች በዙር ይመሩታል፡፡

የአማካሪ ቦርዱ አምስቱን ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎችን ተከትሎ ንኡሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል። ንኡሳን ኮሚቴዎቹ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ለማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤቱ ቴክኒካዊ ምክር እና ድጋፍ የመስጠት ሀላፊነት ይኖራቸዋል ። ባለብዙ ዘርፍ ለሆኑ ጉዳዮች ለምሳሌ እቅድን፤ ክትትል እና ግምገማ እንዲሁም የተጣጣመ ልየታ መስፍረቶች እና ብሔራዊ የመረጃ የምዝገባ ስርአት ማዳበርን ጨምሮ ለመሳሰሉ የተለያዩ ጉዳዮች ልዩ ንኡሳን ኮሚቴዎች ይዋቀራሉ።

**5.1.3 የፌዴራል ማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያ ክፍል**

የምክርቤቱ ሴክሬተሪያት የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲሆን ለስራው የሚመደብ የፌዴራል ማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያ ክፍልም ለዚሁ ዓላማ ሲባል በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር ይቋቋማል፡፡ ይህም የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ሌሎች ማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ለሚያስፈጽመው ክፍል/ዳይሬክቶሬት የተለየ ነው፡፡ ለዚህ ተልእኮ ሲባል የማስተባበሪያ ክፍሉ በፌዴራል ማህበራዊ ጥበቃ ምክርቤት አማካኝነት ህጋዊ ስልጣን ይሰጠዋል፡፡ የማስተባበሪያ ክፍሉ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት፣ ሀሳቦችን እና ምክሮችን ከማህበራዊ ጥበቃ አማካሪ ቦርድ ያገኛል፡፡ የማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያ ክፍል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባር እና ሀላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

- ***ቴክኒካዊ ቁጥጥር እና ማስተባበር***- የማህበራዊ ጥበቃ አካላት መካከል በፖሊሲ፣ ስትራቴጂያዊ እና ተግባር ደረጃዎች የተሻለ ቅንጅት መኖሩን ማረጋገጥ፡፡ ለማስተባበር ሂደቱ ተግባራዊ ድጋፍ እና ምቹ ሁኔታዎች መፍጠርን እንዲሁም ለምክር ቤቱ ማንኛውንም አስፈላጊ የሆነ የህግ ወይም የፖሊሲ ለውጦች ሀሳብ ማቅረብ፤

*ስዕል 3፡ ተቋማዊ አደረጃጀት እና የማስተባበር ስልቶች*



- ***የስርአት ቀረጻ፡-*** በምክር ቤቱ የሚጸድቅ የጋራ  መለኪያ ስርአትን ማዘጋጀት ለምሳሌ የተጣጣመ ልየታና፤ አንደ ወጥ የምዝገባ ስርአት እና የስራ አመራር መረጃ ስርአት(MIS)
- ***ክትትል ግምገማ እና ሪፖርት አቀራረብ-*** ለማህበራዊ ጥበቃ ስትራቴጂው የሚሆን የክትትል እና ግምገማ ስርአት ሀሳብ ለምክር ቤቱ ማቅረብ እና ማጸደቅ፤ ስርአቱን ማደራጀት  እና ጥቅም ላይ ማዋል፡፡ እንዲሁም የማህበራዊ ጥበቃውን ቅልጥፋና፤ ውጤታማነት እና ተፅእኖ የሚመለከት ሪፖርቶችን ማዘጋጀት።
- ***የገንዘብ ድጋፍ፡*** የበጀት አመዳደብን መቆጣጠር እና መጠቀም እንዲሁም ለምክር ቤቱ የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት እና የሀብት ምንጮችን ለማንቀሳቀስና ለማሰባሰብ የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ መቋቋሙን ማረጋገጥ፡፡
- ***የአቅም ግንባታ፡*** ለዘርፉ የአቅም ግንባታ እቅድ ማዘጋጀት እና መተግበር እንዲሁም በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ላሉ ባለድርሻ አካላት ቀጣይነት ያለው ድጋፍ መስጠት እና ለዘርፉ ተግባቦት ስትራቴጂ ማመንጨት።

### 5.1.4 የማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያ ክፍልተጠሪዎች/አስተባባሪዎች

ማህበራዊ ጥበቃን ተግባራዊ የማድረግ ሀላፊነት ያለው እያንዳንዱ ሚኒስቴር /ኤጀንሲ ለስራው ሙሉ ጊዜውን የሚሰጥ የማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያ ተጠሪ የሆነ ግለሰብ ወይም ክፍል እንደ ማህበራዊ ጥበቃ ተሳትፎው መጠን ይመድባል። ተጠሪው ወይም ክፍሉ-

- ስለኢትዮጵያ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራም ጥልቅ እውቀት ያላቸው፤
- በስትራቴጂው በተገለፀው መሰረት ከአቻ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ወይም ኤጀንሲዎች እና የተለያዩ አስተባባሪ አካላት በዋነኝነት ከሰራተኛ እና ማህበራዊ ሚኒስቴር ማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያ ክፍል እና የአማካሪ ቦርድ ጋር ትስስር የመፍጠር ሀላፊነት ይኖረዋል።
- ለአቻ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማስተባበሪያ ክፍል ሪፖርት ያደርጋል፡
- በማህበራዊ ጥበቃ አማካሪ ቦርድ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል፤ በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት ለስልጠና እና መረጃ ልውውጥ በመደበኛነት ይሳተፋል፤

እነዚህ ተግባራት እና ሌሎች የተጠሪዎቹ ወይም የክፍሎቹ የስራ መዘርዝር/ቢጋር እንደአስፈላጊነቱ ይመሰርታል።

### 5.1.5 በክልል፤ ዞን፤ ወረዳ እና በቀበሌ ደረጃዎች

ማስተባበሪያ ክፍል፤ አማካሪ ምክር ቤት እና ተጠሪዎችን ያካተተ ተመሳሳይ ተቋማዊ አደረጃጀቶች በክልል ደረጃ ይቋቋማል። አግባብነት ያላቸው አደረጃጀቶች በዞን ደረጃ ተግባራዊ ይሆናሉ፤ ይህም ሲሆን በየክልሉ ያለውን ለዞኖች የተሰጠ የሀላፊነት ልዩነት ያንጸባርቃል።

የወረዳ እና ቀበሌ ማስተባበሪያን የሚመለከት አጭር መዘርዝር ከዚህ በታች ቀርቧል።

በወረዳ ደረጃ የሚከተሉት የማስተባበሪያ አካላት ይመሰረታሉ።

- በወረዳ አስተዳዳሪ የሚመራ የወረዳ የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት ይመሰረታል። ሀላፊነቱም ከፌዴራሉ የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፤
- የወረዳው ማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያ ተቀማጭነቱ የወረዳዉ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ውስጥ ይሆናል። የማስተባበር፣ የማስተዋወቅ፣ የማመቻቸት እና የመደገፍ ስራዎችን ጨምሮ የማስተባበሪያ ክፍሉ የማህበራዊ ጥበቃ ተግባራትን በቀበሌ ደረጃ የመተግበር እና መከታተል ሀላፊነት ያለባቸውን መዋቅሮችን ቴክኒካዊ ስልጠና እና አቅም ግንባታ አገልግሎት ይሰጣል።
- የማህበራዊ ጥበቃ ተጠሪ በወረዳ ደረጃ በእያንዳንዱ የዘርፍ ጽ/ቤት/ኤጀንሲ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ውስጥ ይኖራል፡፡

የሰራተኛ ምደባን በተመለከተ፣ ማስተባበሪያ ክፍሉ ተጨማሪ የስራ ምደባን የሚጠይቅ ሲሆን በየመስሪያ ቤት ያሉ ተጠሪዎች እና የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት ተወካዮች ግን በየድርጅቶቹ ውስጥ ከሚገኙ ሰራተኞች መካከል የሚውጣጡ ይሆናል።

እያንዳንዱ አስተዳደር ደረጃ ከላይ ባለው ደረጃ ምክር ቤት ውክልና ይኖረዋል። ይህ ማለት የክልላዊ ምክር ቤቶቹ በፌዴራል ምክር ቤት ውክልና ሲኖራቸው የወረዳ ምክር ቤቶች በክልላዊ ምክር ቤቶች እንዲሁም የቀበሌ ምክር ቤቶች በወረዳ ምክር ቤቶች ውክልና ይኖራቸዋል።

በቀበሌ በአስተዳዳሪው የሚመራ የቀበሌ ማኅበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት ይኖራል፡፡ በቀበሌው ውስጥ ያሉትን የማኅበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ያስተባብራል፡፡ በተቻለ መጠን የሥራ ድግግሞሽ የሚወገድ ሲሆን አዳዲስ መዋቅሮችን በመፍጠር የቀበሌው አቅም መለጠጥ የለበትም፡፡ ስለዚህ የቀበሌ ምክር ቤት በሥራ ላይ ባሉት የማኅበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች ወይም የልማታዊ ስፍትኔት የቀበሌ ምግብ ዋስትና ግብረ ኃይሎች ላይ ይገነባል፤ አብረው ሲገኙም በሁለቱም በማጣመር ወይም በሌላ በማንኛውም በሚመለከተው ኮሚቴ ላይ የሚመሰረት ይሆናል፡፡ እንዳስፈላጊነቱ ቀበሌው ያለውን የሰው ኃይል ሊጠቀም ይችላል፤ ተገቢ ሆኖ ከተገኘ የቀበሌውን ስራ አስኪያጅ (አስፈላጊውን ሥልጠና ከወሰደ/ች በኋላ) ጨምሮ ሁሉንም የማኅበራዊ ጥበቃ ሥራዎች እንዲያስተባብር ወይም የማኅበራዊ ጥበቃ ኤክስቴንሽን ወኪል ይሾማል ፡፡

### 5.2. የትግበራ አቅሞች

ይህ ስትራቴጂ ውጤታማና ዘላቂ እንዲሆን በሁሉም ደረጃ የተጠናከረ አቅም ይጠይቃል፡፡ በመጀመሪያው የትግበራ ደረጃ ላይ (በ2008/2010 የበጀት ዓመት) የሚከተሉትን የአቅም ግንባታ ተግባራት የሚያካትት ዕቅድ ይዘጋጃል፡-

- ለትግበራው የሚሆን የአቅም ፍላጎትን ይለያል፤
- ያሉትን አቅሞችና የታቀዱ የአቅም ግንባታ እርምጃዎች ይዳስሳል/ይመዘግባል፤
- የአቅም ክፍተቶችን ይለያል፣ ይተነትናል፤
- እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት የሚያስችሉ የመፍትሄ እርምጃዎችን ያጎለብታል፣ ያቅዳል

(1) **የአቅም ግንባታ ዕቅዱ አድማስ** - የአቅም ግንባታ ዕቅዱ አድማስ ሁሉንም አበይት ፈርጆች የሚሸፍን ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡-

*ሀ) ዘላቂ ቀጥታ ተጠቃሚዎችን ለመረከብ የሚያስችል መሰረታዊ አቅም መኖሩን ማረጋገጥ*- በአጭር ጊዜ ውስጥ በልማታዊ ሴፍትነት ቀረፃ ሰነድ ላይ እንደተቀመጠው የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ለመረከብ በክልል፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሚያስፈልገውን መሰረታዊ አቅም ይወስናል፡፡ ይህም በቀዳሚነት አሁን ያሉትን የመንግስትም ሆነ የማኅበረሰብ አቀፍ መዋቅሮች በማጠናከር ወይም አዳዲስ በመመስረት መጠቀምን ይጠይቃል፡፡

ለ) *የሽግግር አቅም ግንባታ ለውጤታማ ትግበራ በ2008/2009*፡ የአቅም ግንባታ ዕቅዱ የጋራ የድርጊት መርሀ ግብሩን የረጅም ጊዜ አድማስ ከግምት በማስገባት፤ የዚህን የ2008/2009-2012 ስትራቴጂ ውጤታማና ወቅታዊ በሆነ መልኩ ለመተግበር ቁልፍ የአቅም ክፍተቶችን በሽግግር ጊዜው መሙላት እንደሚቻል ይመለከታል፡፡ ይህ በአጠቃላይ በዘርፉ ውስጥ ላሉት ሰራተኞችና በጎ ፈቃደኞች የሚሰጡትን ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን፣ ከሲቪል ማኅበራት፣ ከግሉ ዘርፍ አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የሚመሰረትን አጋርነት በጥምረት የሚያካትት ሲሆን ተጨማሪ የሰለጠነ የሰው ኃይል በጊዜያዊነት ለቴክኒክ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ ቅጥርን ይጨምራል፡፡

ሐ) *የረጅም ጊዜ የሰራተኛ ኃይል ዕቅድ ለማኅበራዊ ጥበቃው ዘርፍ*- የሰራኞች ቁጥር፣ የክህሎት ደረጃ አምስቱንም የትኩረት መስኮች ለማስፈጸሚ የሚያስፈልግ ልዩ ሙያ /ስፔሻላይዜሽን/ ፡፡ የረጅም ጊዜ እቅዱ በማኅበራዊ ጥበቃ ዘርፉ የሰው ኃይል የሚፈለገውን ክህሎት ለመገንባት የሚያስችሉ ዕውቅና ያላቸው የቅድመ አገልግሎትና የአገልግሎት ላይ የስልጠና ፕሮግራሞች ማጎልበትን ያካትታል፡፡ ከእነዚህ መስኮች መካከል በአንዳንዶቹ ላይ ሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር/የትምህርት ሚኒስቴር ጥምር የድርጊት መርሀ ግብር በመሆን ስራ ተጀምሯል፡፡ በእቅዱ መሰረት ለአዳዲስ መደቦች እንዲሁም ለማሰልጠኛ ማዕከላትና ለፍቃድ ሰጪ ተቋማት እውቅና አሰጣጥ የሚሆኑ ምክረ ሀሳቦች አሉ፡፡

መ) *የማኅበራዊ ጥበቃ ሰራተኞችን በስራቸው ላይ ማቆየትና ሙያ ማጎልበት*- የሰራኞች ስራ መልቀቅ በአነስተኛ የሲቪል ሰርቪስ ደረጃ ባላቸው ሚኒስቴሮች (የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ጨምሮ) እንደ አጠቃላይ ችግር በከፍተኛ ደረጃ እየተባባሰ መጥቷል፡፡[43] ደረጃ አሰጣጡ በሰራተኛው ቁጥርና ደመወዝ ላይ በተዋረድ ጫና ያሳድራል፡፡ የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ጋር በመሆን በዘርፉ ያለውን ሰራተኛ በስራው ላይ ከማቆየት አንጻር ያሉትን ተግዳሮቶች፣ የስራና ደመወዝ እድገትን እንዲሁም በማኅበራዊና በሌሎች ዘርፎች መካከል ያለውን የክፍያ ልዩነት ጨምሮ መፍትሄ ለማስገኘት በጋራ ይሰራሉ፡፡ ይህ አይነቱ ትብብር የማኅበራዊ ጥበቃ አላማዎች በሁሉም ሚኒስቴሮችና፣ ኤጀንሲዎች የሚገኙ የማኅበራዊ ጥበቃ ሰራተኞች የስራ መዘርዝር ውስጥ ማካተት ያስችላል፡፡

ሠ) *የስራ አፈፃፀም አመራር እና የማስተባበሪያው ማትጊያ ሥርዓት*፡ በአብዛኛዎቹ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ከሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና አጀንሲዎች ጋር በትብብር መስራት ከባለሙያ አበይት የስራ መዘርዝር ይዘቶች መካከል ተጨማሪ (ትርፍ ስራ) ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

ረ) *የማኀበራዊ ጥበቃ ሰራኞተች ሁለንታዊ ክህሎት፡*  የዚህ ስትራቴጂ ትግበራ  በተለዩ ልዩ በሆኑ የማኀበራዊ ጥበቃ ክህሎቶች ላይ ብቻ ሳይሆን የኮምፒዩተር ችሎታን የመሳሰሉ ሁሉን የሚያጠቃልሉ ሙያዎችን ይጨምራል፡፡ የጋራ ተጠቃሚ ብሔራዊ ምዝባ ስርዓት (CBRS) ማቋቋምና መምራት በቀበሌ ደረጃ የመረጃ ማስገባት ክህሎትን፣ በወረዳ፣ በክልልና በፌዴራል ደረጃ ደግሞ የመረጃ ትንተና ክህሎትን ይጠይቃል፡፡ የአቅም ግንባታ እቅዱ በዚህ መስክ ያሉትን ዋና ዋና ክፍተቶችን ለይቶ ለመሙላት የሚያስችል ስልት ይነድፋል፡፡

ሰ/ *በሁሉም ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ዘንድ (ግብር ከፋዮችን ጨምሮ) ሰፊ መሰረት ያለው የማኀበራዊ ጥበቃ ግንዛቤ ይፈጠራል፡፡*ማኀበራዊ ጥበቃ ለኢትዮጵያ በአንጻራዊነት አዲስ ስልትና የፖሊሲ መስክ ነው፡፡ ማኀበራዊ ጥበቃ ለኢኮኖሚና ለሰው ሀብት ልማት ያለው አስፈላጊ አስተዋፅኦ በህዝቡ ወይም በፖሊሲ አውጪዎች ዘንድ ሁልጊዜ ተገቢውን ግንዛቤ የማያገኝ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ የህዝብ ገንዘብ የሚያሚጥጥ የአጭር ጊዜ እርዳታ የሚያካትት ተደርጎ በተሳሳተ መንገድ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም በውሳኔ ሰጪዎች፣ በመንግስት ሰራተኞችና በሁሉም ደረጃ ላይ ባለው ምልዓተ ህዝቡ ዘንድ ግንዛቤን መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡እነዚህን ጉዳዮች ለመድረስ፡-

- ዘላቂ የስራ ላይ የማኀበራዊ ጥበቃ ትምህርትና ግንዛቤ የማሳደግ ፕሮግራም ለውሳኔ ሰጪዎች/ ለመንግስት ሰራተኞች ይዘጋጃል፣ እንዲሁም
- እያንዳንዱ የክልል የሰራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ ቢሮ የአሰልጣኞች ቡድን ያዋቅራል፡፡
- የማህበራዊ ጥበቃ ተግባቦት እቅድ መዘጋጀቱ የህዝቡን እውቀት እና ድጋፍ በማህበራዊ ጥበቃ ዙሪያ ለማሳደግ ይጠቅማል።

**ሸ.** *ተፈላጊ ቁስ እና ሎጀስቲክሱ-* ምንም እንኳ የዚህ ክፍል እና የአቅም ግንባታ እቅዱ ትኩረት የሰው ሀይል ልማት ቢሆንም መሟላት  ያለባቸው እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የተወሰኑ የሎጂስቲክስ አቅሞች አሉ። የአቅም ግንባታ እቅዱ ለቀበሌ እና ወረዳ ሰራተኞች የትራንስፖርት ተደራሽነትን፤ ሰራተኞች ተግባራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን የስራ መሳሪያዎች እና አገልግሎቶች ማሟላትን ታሳቢ ደርጋል። በወረዳዎች አካባቢ የመረጃ መረብ አግልግሎትን እና በተወሰኑ ሩቅ ወረዳዎች ደግሞ የኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት ተደራሽነትን ታሳቢ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

2. **የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት የአቅም ግንባታ ተግዳሮቶች**:- በዚህ ስትራቴጂ በተሰጠው አቅጣጫ እና ውሳኔ መሰረት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ተግባር እና ሀላፊነት መቀየሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት የአቅም ግንባታ ተግዳሮቶች በስትራቴጂው ትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ ይሆናል።

- የማህበረሰብ  ስራ የመቅረፅ እና የመተግበር  አቅም:- በገጠር አካባቢ የማህበረሰብ  ስራዎች ጉዳይ የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሀላፊነት ሆኖ ይቀጥላል። በከተማ  ልማታዊ የሴፍትኔት ፕሮግራም ላይ በተጠቀሰው መሰረት የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚ/ር በከተማ አካባቢ ለሚካሄዱ ህዝባዊ ስራዎች ሀላፊነት ይኖርበታል።
- ሌሎች ማህበራዊ ድጋፎች የመቅረፅ እና የመተግበር አቅም:- የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር  ለገጠር እና ለከተማ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች  ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የማህበራዊ ድጋፍ  የመቅረፅ እና የመምራት ሀላፊነት አለበት። ይህ ሽግግር በሁሉም ደረጃዎች ማለትም በፌደራል፤ክልል እና ወረዳ ደረጃ የሚካሄድ ሲሆን በቅድሚያ የማህበረሰብ  ስራ እና ቀጥተኛ ድጋፍ ክፍያ ዝርዝር /ፔይሮል/ መለየት ያስፈልጋል፡፡  የቀበሌ ማህበራዊ ጥበቃ

ምክር ቤት ወይም ተገቢው መዋቅር የልየታ ሀላፊነት ይኖርበታል። የሰማጉሚ የአቅም ግንባታ ዕቅድ በተለዩ ክፈተቶች መሰረት ይዘጋጃል፡፡

- የማህበራዊ ሠራተኞች ስርአት መዘርጋት ፡ትኩረት መስክ 4 እና 5 ተግባራዊ ለማድረግ የወረዳ ሰማጉሚ፣ እና ሴቶች እና ሕፃናት ጽ/ቤቶችን፤ የቀበሌ መስተዳር እና ከማህበረሰብ ኮሚቴ በሕፃናት ጥበቃ' ያታዊ ጥቃትን መከላከል ና ምላሽ መስጠት እንዲሁም ለተጋላጭ ህብረተሰብ ክፍል መሰረታዊና ልዩ አገልግሎት ተደራሽነትን የመምራት ሀላፊነት አለባቸው። የማህበረሰብ ፖሊሶች እና ፍትህ ሚኒስቴር ጉዳት አድራሾችን ለፍትህ በማቅረብ ጠቃሚ ሚና የሚጫወቱ ሲሆን የማህበራዊ አገልገሎት ዘርፍ ስርዓት (የማህበረሰብ ግንዛቤ ማሳደጊያ ጥቃት ለደረሰባቸው ድጋፍ መስጠት) ሊቋቋም እና ሊጠናከር ይገበዋል።

ለምሳሌ የትኩረት መስክ 5 መፈጸም ማለት ባለ ብዙ እርከን ስርአትን መዘርጋት ማለት ነው። ይህም ማለት የሰለጠኑ የማህበረሰብ በጎፈቃደኞች/ኮሚቴ፣ ከፊል /'ፓራ/ ማህበራዊ ስራተኞች በቀበሌ ደረጃ፣ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑ ልዩ እውቅና የተሰጣቸው ማህበራዊ ሰራተኞች ደግሞ በወረዳ ደረጃ ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህ ከፍተኛ ስጋት ያለባቸውን ጉዳዮች የመምራት ስራን ያከናውናሉ ።[44] ይህም የግል ተበዳይ ጉዳይ (የኬዝ) የሚታይበት አመራር ስርአት ማቋቋም እና ልዩ አገልግሎት ከሚሰጡ እውቅና ከተሰጣቸው አጋሮች ጋር ትስስር መመስረትን ያካትታል። በዚህ ረገድ ያለው የአቅም ግንባታ ፍላጎት ከፍተኛ ነው።

- **ማህበራዊ የመድን ሽፋን**፡- የመደበኛው የመድን ሽፋን ስርአት ውሱንነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ ማህበረሰብ አቀፍ በሆኑ በሺዎች የሚቆጠሩ እድሮች ውስጥ ሰፊ አቅም አለ። የማህበራዊ ጥበቃ ስርአቱ ይህ ሀገር በቀል እውቀትን ታሳቢ በማድረግ ተደጋጋፊ አነስተኛ የመድን አገልግሎት ስርአት ቀረፃን የሚያረጋግጥ ሲሆን የእድሮችን ሀላፊነት ማስፋፋት ሲባል በአሁኑ በመጫወት ላይ ያሉትን ሚና ዝቅ እንዳይል መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

### 5.3 የስርአትዝርጋታ

የተቀናጀ ስራ እና የተጣመረ አገልግሎት ለድሆች እና ችግር ተጋላጮች መስጠት ይቻል ዘንድ ውጤታማ የሆነ የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ብዛት ያላቸው የጋራ ስርአቶች ያስፈልጉታል።

በዚህ ስትራቴጂ የሚከተሉት ስርአቶች ይዘረጋሉ።

- የብሔራዊ ወጥ የተጠቃሚ ምዝገባ ስርአት
- የተቀናጀ ልየታ ስርአት
- መደበኛ የክትትል እና ግምገማ ማእቀፍ
- የጊዜ ሰሌዳ እና ታሳቢዎች
- የፋይናንስ ጉዳይ/ክፍል 6 ይመልከቱ/

### 5.3.1 የብሔራዊ ወጥ የተጠቃሚዎች ምዝገባ

አንድ ብሔራዊ እና ወጥ የሆነ የተጠቃሚ ምዝገባ ስርአት ማቋቋም ለድሆች እና ለችግር ተጋላጮች የሚሰጠውን የማህበራዊ ጥበቃ ስራ ያሻሽላል። ይህን አላማ ለማስፈፀም ብሔራዊ እና ወጥ የሆነ የተጠቃሚ ምዝገባ ስርአት የሚከተሉትን ፍላጎቶች ማሟላት አለበት፡-

- በፈፃሚ ደረጃ /በቀበሌ ደራጃ/ የሚገኙ የማህበራዊ ጥበቃ ሰራተኞች እና በጎፈቃደኞችን አቅም በማጠናከር የቤተሰብ አባልነት እና ባህሪ ምዝገባን፣ የተጠቃሚ ልየታ መደገፍ፣ የትኛው ቤተሰብከ ከትኛው አገልግሎት ተጠቃሚ እንደሆነ እና ቤተሰቦች ማግኘት የሚገባቸውን አገልገሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ።
- ወደላይኛው እርከን የሚደረጉ ሪፖርቶችን፣ተሞክሮዎችን እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የተሻሻለ የመረጃ ማሰባሰብ እና ትንታኔን መደገፍ
- ህጋዊ ያልሆነ ተደጋጋሚ ተጠቃሚነትን ማስወገድ

እነዚህን ፍላጎቶች ማሟላት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይጠቁማል።

በሀገሪቱ ከሚገኙ የተመረጡ በአስፈጻሚ ደረጃ የሚገኙ የቀበሌ ሰራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች ንቁ ተሳትፎ የጋራ የሆነ ሀገራዊ የተጠቃሚዎች ምዝገባ መለያ እና ቅፅ ማዘጋጀት። በሌላ አገላለፅ የቀረፃ ሂደቱ የአስፈፃሚ አካላትን ፍላጎት ከሚሟላት አንጻር ከታች ወደ ላይ የሆነ መንገድ የሚከተል ሲሆን ይህም ሂደት አንድ ወጥ የሆነና ብሔራዊ እና ወጥ የሆነ የተጠቃሚ ምዝገባ ቀረፃን ለማስረፅ ይጠቀማል፡፡

1) በኮምፒዩተር የተደገፈ የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ የስራ አመራር መረጃ ስርአት በሂደት በወረዳ ደረጃ እና ከዚያም ባሻገር ሽፋን የሚኖረው ሲሆን ይህም ከተለያዩ የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፎች የስራ አመራር መረጃ ስርአት ጋር እንደ አስፈላጊነቱ የሚጣጣም ይሆናል።
2) በቀበሌ ደረጃ የሚደራጀው አንደ ወጥ ተጠቃሚ ምዝገባ ስርአት ከመረጃ ስራ አመራር ስርአት ጋር ተመሳሳይ ይሆናል።መረጃዎች ከቀበሌ ወደ ወረዳ በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ማለትም ፍላሽ ዲስክ፣ወረቀት ወይም መረጃ መረብ የሚተላለፍ ሲሆን ወደ የመረጃ ስራ አመራር ስርአት ስርአት ውስጥ የሚመዘገበው በወረዳ ደረጃ ነው።
3) ስትራቴጂው ያነገበውን ለተጋላጭ ቤተሰቦች አገልግሎቶችን የማሻሻል አጠቃላይ አላማን ታሳቢ በማድረግና በቀበሌ ደረጃ አንደ ወጥ ተጠቃሚ ምዝገባ ቅድሚያ የሚሰጠው ሲሆን በወረዳ ደረጃ የሚከናወነውን በኮምፒዩተር የታገዘ የመረጃ ስራ አመራር ስርአት ዝግጅት እና ትግበራ ይቀድማል። በዚህ አግባብ ከቀበሌዎች የምንማረው ልምድ ለመረጃ ስራ አመራር ስርአት ዝግጅት ይጠቅማል።

### 5.3.2 የተቀናጀ የልየታ ስርአት

የተቀናጀ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የመለየት ስርአት የሚያመለክተው የሁሉንም ፕሮግራሞች ተጠቃሚዎች ለመለየት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በአሳታፊ መንገድ ከቤተሰቦች ማሰባሰብ፣ በመረጃ ቋት መመዝገብ እና የሁሉንም ፕሮግራሞች አላማ ለማሳወቅ መጠቀም ነው። ቅንጅታዊ አሰራር የተመሳሳይ ፕሮግራም ተጠቃሚዎችን ድግምግሞሽ በማስወገድ

ውጤታማነትነት ያሳድጋል። በተጨማሪም ሀብትን እና አቅምን በማቀናጀት ፕሮግራሞች የላቀ ውጤት እንዲያመጡ እና ብክነትን ለመቀነስ ያስችላል። ቤተሰቦችም የማህበራዊ ዋስትና ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት የሚያስፈልጓቸውን ሁሉ አቀፍ አገልግሎት ያገኛሉ።

ይህን መሰሉ የተቀናጀ ስርአት የሚከተሉትን ተጨማሪ ጥቅሞች ያስገኛል።

- ቤተሰቦች ሁሉን አቀፍ አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ለማስቻል የልየታ መስፈርቶችን እና ሂደቶችን ያጣጥማል
- ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ለመስጠት እጅግ ያቀላል
- በሰብአዊ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ የሚሆኑ ቤተሰቦችን በፍጥነት ለመለየት ያስችላል
- የተጠቃሚዎችን ዝርዝር በቀላሉ በማውጣት ያልተፈለገ ድግግሞሽን ያስቀራል
- በፕሮግራሞች ቅንጅት በሚፈጠረው ተጨማሪ ጥንካሬ በአንድ ጊዜ ተደራራቢ ችግሮችን ለመፍታት ያስችላል - ጥቂት ተጠቃሚዎች ከአንድ በላይ ከሆነ ተቋም ድጋፍ ሊፈልጉ ይችላሉ።

1. **ማጣጣም**:- ፕሮግራሞች ተመሳሳይ የልየታ መስፈርቶች በሚኖራቸው ጊዜ በጋራ ተጠቃሚዎችን በመለየት አንድ የተጠቃሚዎች ዝርዝር ይኖራቸዋል። የተወሰኑ ፕሮግራሞች ደግሞ በከፊል ተመሳሳይ መስፈርቶች ሊኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ አረጋውያን ያሉበት ድሀ ቤተሰቦች እና ሕፃናት ያሉበትን ድሀ ቤተሰብ ኢላማ ያደረጉ ፕሮግራሞች። በዚህ ጊዜ ተመሳሳይ የሆነ ዋና አንድ ወጥ የድሀ ቤተሰቦች ዝርዝር በማውጣት አንደኛው ፕሮግራም አረጋውያን ላይ ሲያተኩር ሌላኛው ደግሞ ሕፃናት ላይ ያተኩራል።

2. **ተከታታይነት ያለው ድጋፍ**:- በሌላ በኩል የተቀናጀ ልየታ ማለት ሁሉም የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ተመሳሳይ የሆነ ልየታ መስፈርት ወይም የተጠቃሚዎችን ዝርዝር ይኖራቸዋል ማለት አይደለም። ይልቁንም የተለያዩ የፕሮግራም አላማዎች በሚኖሩበት ጊዜ ቤተሰቦች በአግባቡ ከአንዱ ፕሮግራም ወደ ሌላው ፕሮግራም እንዲሸጋገሩ ያስችላል። ለምሳሌ በስራ እድል ወይም ኑሮ ማሻሻያ ላይ ያተኮረ ፕሮግራም ልየታ መስፈርት ሁሉንም የሚመረቁ እና የተመረቁ የሴፍትኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎችን ያካተተ ሲሆን ፕሮግራሙ ስኬታማ በሆነ መልኩ ከተተገበረ በአንድ ምዝገባ ስርአት ተከታታይነት ያለው ድጋፍ በመስጠት በዘላቂነት ከድህነት እንዲወጡ ማድረግ ይቻላል።

3. **ለሰብአዊ ፕሮግራሞች በፍጥነት ተጠቃሚዎችን መለየት**:- የሰብአዊ ፕሮግራሞች ለአደጋ ምላሽ እንዲረዳቸው ድሆች እና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቤተሰቦች ሙሉ ዝርዝር በፍጥነት ማግኘት ይፈልጋሉ። ብሔራዊ እና ወጥ የሆነ የተጠቃሚ ምዝገባ ስርዓት  ቀልጣፋ እና የተሟላ መረጃ በድህነት፤ አደጋ ተጋላጭነት እና የማህበራዊ ጥበቃ ድጋፍ ያገኙ ቤተሰቦች እንዲሁም በቅርቡ ከድጋፍ የተመረቁ ቤተሰቦችንን ለማግኘት ያስችላል።(ለምሳሌ ከተወሰኑ ፕሮግራሞች የተጠቃሚነት አግባብ የተሰረዙ ሰዎችን ዝርዝር) ። ይህም የሰብአዊ አገልግሎት ፕሮግራሞች ልየታ በማፈጣን ምላሽ እንዲሰጡ እና ውጤታማነታቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳል።

4. ***ያለተፈለጉ ድግግሞሾችን ማስወገድ፦*** ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ፕሮግራሞች ለቤተሰቦች ተመሳሳይ አገልግሎት ለአንድ ቤተሰብ ሁለት ጊዜ እና ከዚያ በላይ ተመሳሳይ አገልግሎት እንዳይሰጡ ያስችላል። የተቀናጀ የልየታ ስርአት ያልተፈለገ ድግምግሞሽን ያስወግዳል።

5. **የፕሮግራሞች ውህደት ጥንካሬን ማሳለጥ**፦ በሌላ መልኩ ቤተሰቦች በህጋዊ መንገድ ተደራራቢ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ከአንድ በላይ ከሆኑ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ለአረጋውያን፤ ለአካል ጉዳተኞች፤ ከኤች አይ ቪ ቫይረስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ወይም ሕፃናት ልዩ አገልግሎት የሚሰጥ ኘሮግራም አለ እንበል። በነዚህ ሁኔታ የተቀናጀ ልየታ ስርአት ቤተሰቦች ሊያገኙ የሚገባቸውን ሁሉንም አገልግሎቶች እንዲያገኙ ያስችላል።

### 5.4 የጋራ የክትትል እና ግምገማ ማእቀፍ

ባለድርሻ አካላት የሚመለከታቸውን እና የራሳቸው የሆኑትን ፕሮራግሞች ለውጥ ክትትል ማድረግ እና የክትትልና ግምገማ ሪፖርቶችን ለማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያ ክፍል ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንዲሁም በተስማሙባቸው የጋራ አላማዎች፣ አመላካቾች፣ ልየታ፣ ግቦች በጋራ የመረጃ ሥርዓት መሰብሰብና ሂደቱን ለመከታተል ሁሉም ባለድርሻ መሳተፍ አለባቸው፡፡ ክትትልና ግምገማው ተመሳሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ ለብሄራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት ሪፖርት በመላክና በዓመት ሁለቴ በሚያካሂዷቸው ስብሰባዎች መወያየት አለባቸው፡፡፡የፌዴራል እና የክልል የመንግስት አካላት 'የማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለማህበራዊ ጥበቃ ካውንስል ሴክሬተሪያት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው። የጋራ የክትትል እና ግምገማ ማእቀፉ ቀላል እና ለተጠቃሚዎች ምቹ መሆን አለበት። ማእቀፉ የሚከተሉት ይዘቶች ይኖሩታል።

**ግብ**፦ ሁሉም ኢትዮጵያኖች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት፣ዋስትና እና ማህበራዊ ፍትህ ያገኛሉ።

**የመጨረሻ ወጤት**፦ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ስጋቶችን፤ ተጋላጭነትንና የሀብት መሟጠጥን እና ለሁሉም ሰዎች በእኩልነት ለማቀላጣፍ የሚያስችሉ መደበኛ እና ኢ መደበኛ አገልግሎቶችን የያዘ የማህበራዊ ጥበቃ ስርአት መዘርጋት እና ፍትሀዊ እድገትን ማሳለጥ።

**መሀከለኛ ውጤት**፦ አምስቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

የክትትል አመላካቾች እና ግቦች ሳይበዙ፣ የተካሄዱ ወይም በመካሄድ ላይ ያሉ ዳሰሳዎች እና የክትትል ሂደቶች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለመረጃነት ይውላሉ። ጠቋሚ የክትትል እና ግምገማ ማእቀፍ በአባሪ 2 ላይ ተያይዞ ቀርቧል። በግብ፣ አላማ እና ውጤት ደረጃ ለውጦችን ሊጠቁሙ የሚችሉ የክትትል ጠቋሚዎች ቀርበዋል። ቀጣዩ ትግባራ ማእቀፉን ማጥራት፣ የቀረቡ ጠቋሚዎች ትርጉም ሰጪ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የሚለኩ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና አመታዊ ግብ ማስቀመጥ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ የክትትል እና ግምገማ ማእቀፍ ውስጥ የሴክተሮች የውጤት አመላካቾች፣ግቦች እና መነሻ መረጃ/baseline/ ተሰብስቦ አገልግሎት ላይ ይውላል። ፈታኙ የሚሆነው ዘርፈ ብዙ የሆኑ ፕሮግራሞች ውጤት መለየት እና ትርጉም ባለው መልኩ ከማህበራዊ ጥበቃ ጋር ማያያዝ ነው። ተከታይነት ያለው ግምገማ በሴክተር ደረጃ እንደማይካሄድ ታሳቢ በማድረግ፣ መንግስት በሚያከናውናቸው ሌሎች የዳሰሳ ጥናቶች ውስጥ የማህበራዊ ድጋፎች ጠቋሚዎች እንዲካተቱ

በማድረግ ነው፡፡ ፡፡ ሌሎች ዘርፎች ከማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር፡- የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራም ተጠቃሚዎች በብሄራዊ የድህነት፣ የደህንነት እና የህዝብ ጤና የዳሰሳ ጥናቶች ላይ የሚካተቱበትን እንዲሁም በነዚህ ጥናቶች ውስጥ አንድ ክፍል እንዲኖረው ለማድረግ እና ተጨማሪ ናሙናዎች የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት ለመጀመሪያ ጊዜ በሚሰጥባቸው ቦታዎች መውሰድ የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባል። ይህም የረዥም ጊዜ/ተከታታይነት ያለው እና የአንድ ጊዜ በብዙ ክፍሎች/የተሰባጠረ ዳሰሳ የሚገኝ ውጤት መተንተን ያስችላል።

## 5.5 የጊዜ ማእቀፍ እና ታሳቢዎች

በኢትዮጵያ መንግስት ይህ ስትራቴጂ ከፀደቀ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የሚሆነው በፌደራል 'በክልል እና በወረዳ ደረጃ የድርጊት መርሐ-ግብሮችእቅድ ማዘጋጀት ነው። አፈፃፀሞች በየጊዜው ክትትል የሚደረግባቸው ሲሆን የመካከለኛ ጊዜ ግምገማ የእቅድ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ያገለግላል። ግምገማ እና የተጽእኖ ጥናት/impact assessment/ ከተካሄደ በኋላ በሁለተኛው ዙር ስትራቴጂው ይከለሳል። ጠቋሚ የጊዜ ሰሌዳ እንደሚከተለው ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ 7 የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት ተግባራዊነት የጊዜ ማእቀፍ እና ታሳቢዎች ማሳያ**

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ተግባራት | የጊዜ ሰሌዳ | ታሳቢዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | በኢትዮጵያ መንግስት ስትራቴጂው ይፀድቃል | ሰኔ 2016 እ.ኤ.አ | በፖሊሲ ዝግጅት የታየው ፖለቲካው ቁርጠኝነት ይቀጥላል |
| 2 | የማስተባበሪያ/ቅንጅት ዘዴዎች በሁሉም ደረጃ ይቋቋማሉ | ከሐምሌ-ታህሳስ 2016 እ.ኤ.አ | ባለድርሻ አካላት በመተባበራቸው የሚያገኙትን ጥቅም ተረድተው አብሮ ለመስራት ዝግጁ ይሆናሉ |
| 3 | የድርጊት መርሐ-ግብሮችን ወይም ኢንቨስትመንት ማእቀፍ በፌደራል እና ክልል ደረጃ ይዘጋጃል | ከሐምሌ-ታህሳስ 2016 | ሰማጉሚ ብቁ የሆነ የሂደቱ አመቻች ያገኛል |
| 4 | ሶሻል ወርከሮችን/የሰራተኛ ሃይል ለማብቃት የሚያስችል ስርአት ይቋቋማል | ከሐምሌ - ታህሳስ 2016 | ቴሙትተ እና ሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሶሻል ወርከሮችን ለማሰልጠን አስፈላጊውን አቅም ያሳድጋሉ |
| 5 | ቋሚ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች ወደ ለሰ.ማ.ጉ.ሚ ይተላለፋል | ሐምሌ 2016 | ዝቅተኛው ተፈላጊ አቅም በሁሉም የሰማጉሚ ደረጃ ይሟላል |
| 6 | የብሔራዊ ምዝገባ ስርአት ተዘጋጅቶ የሙከራ ትግበራ ይከናወናል | 2017-2018 | ብቁ ማኢስ እና የአንድ ጊዜ ምዝገባ ዲዛይነሮች ይኖራሉ |

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ተግባራት | የጊዜ ሰሌዳ | ታሳቢዎች |
|---|---|---|---|
| | | | ሌሎች በማህበራዊ ጥበቃ/ማህበራዊ ደህንነት እና ሴፍትኔት ዙሪያ የመረጃ ባለቤቶች አብረው ይሰራሉ |
| 7 | በሁሉም ደረጃዎች በብሔራዊ ምዝገባ ስርአት ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል | 2017-2018 | በአንድ ወጥ ምዝገባ ስርአት አስተዳደር እና የማህበራዊ ጥበቃ ማኔጅመንት እና ኢንፎርሜሽን ስርአት ዙሪያ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች ይገኛሉ |
| 8 | ሀገር አቀፍ የማህበራዊ ጥበቃ የማኔጅመንት እና ኢፎርሜሽን ስርአት ይዘጋጃል | 2019-2020 | የማህበራዊ ጥበቃ ማኔጅመንት እና ኢንፎርሜሽን ስርአት ዲዛይን ዙሪያ ብቁ ባለሙያዎች ይገኛሉ |
| 9 | የመረጃ ትንታኔ ክህሎት በወረዳ እና ክልሎች ደረጃ ይጠናከራል (በስልጠና ወይም ልዩ ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር) | 2019 | በአንድ ወጥ ምዝገባ ስርአት አስተዳደር እና የማህበራዊ ጥበቃ ማኔጅመንት እና ኢንፎርሜሽን ስርአት ዙሪያ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች ይገኛሉ |
| 10 | የመረጃ ግብአት ብቃት በወረዳ ደረጃ ይጠናከራል | 2019 | |
| 11 | የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት በስፋት ይሰጣል | 2020 | |
| 12 | የመካከለኛ ጊዜ ግምገማ እና የተግባር እቅድ ማሻሻያዎች ማድረግ | 2022 | |
| 13 | የተግባር እቅድ ክለሳ | 2023 | |
| 14 | የስትራቴጅው ግምገማ/ተፅእኖ ጥናት | 2024 | |
| 15 | ሁለተኛው ሀገራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ስትራቴጂ ይዘጋጃል | 2024 | |
| 16 | ሁለተኛው ሀገራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ስትራቴጂ ወደትግበራ ይገባል | 2025 | |

## ክፍል 6: ስትራቴጅውን ማስፈጸሚያ የፋይናንስ ጉዳይ

የማህበራዊ ጥበቃ ስትራቴጅው ተግባራዊ ለማድረግ በርከት ያለ መዋዕለ ንዋይ ይስፈልጋል። ከዚህ ስትራቴጂ በኋላ የሚዘጋጀው የኢንቨስትመንት ማእቀፍ የሚያስፈልገውን የገንዘብ  መጠን በግልጽ ያሳያል፤ የሚሰጡ መሰረታዊ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶችን በመለየት በጀት ይመድባል። የዚህ ክፍል ዋና አላማ ለማህበራዊ ጥበቃ በሀገሪቱ የገንዘብ አቅም ውስጥ ማህበራዊ ጥበቃ ቦታ /fiscal space/ አለው ወይ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፤ ጥቅል የበጀት ምንጭ እና ይዘቶችን ለመጠቆም ነው።

### 6.1 ለማህበራዊ ጥበቃ በሀገሪቱ የገንዘብ አቅም ውስጥ ያለውን ቦታ መጠቆም

መንግስት ለማህበራዊ ጥበቃ ያለው ቁርጠኝነት በሀገሪቱ የገንዘብ አቅም ውስጥ ያለውን ስፍራ ይለካል። ይህን ቁርጠኝነት የምንለካበት የተለያዩ መንገዶች አሉ። ለምሳሌ :-

አንደኛ-በሃገራዊ ጥቅል ምርት /GDP/ ውስጥ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች ያላቸው ድርሻ።[45] በክፍል 2.3 ላይ የተዘረዘሩት መደበኛ የሆኑ እና ማበረሰብ አቀፍ የማህበራዊ ጥበቃ አቅርቦቶች የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ከመንግስት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት፣ በመዋጮ ፣በማህበረሰብ ተሳትፎ እና አንድንድ ጊዜ በግለሰቦች አስተዋጽኦ ነው። ከእነዚህ ዘርፎች የሚገኘውን ድጋፍ ዝርዝር ማቅረብ በማይቻልበት ሁኔታ ለሶስቱ ዋና ዋና የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፎች የሚያስፈልግ የበጀት አቅራቦትን እንጠቀማለን። እነርሱም የመንግስት ዘርፎች ማህበራዊ ዋስትና መዋጮ፣ ገጠር እና ከተማ ልማታዊ ሴፍትነት ናቸው።[46]

በዚሁ መሰረት፣ ለገጠር እና ከተማ ልማታዊ ሴፍትነት የተመደበው አመታዊ በጀት እንደየቅደም ተከተላቸው 600 ሚሊዩን ዶላር እና 98.7 ሚሊዮን ዶላር ነው።[47] አጠቃላይ ድምሩም ወደ 700 ሚሊዮን ዶላር አካባቢ ነው። ይህም 14 ቢሊዮን ብር ገደማ ነው። በየአመቱ መንግስት ለማህበራዊ ዋስትና መዋጮ 2 ቢሊዮን ብር ይከፍላል (ክፍል 2.3 ይመልከቱ)። የነዚህ ሶስቱ ዘረፍ አጠቃላይ ወጪ 16 ቢሊዮን ብር ገደማ ሲሆን ይህም የ2013/14 እ.አአ. በሃገራዊ ጥቅል ምርት 1.43 በመቶኛ ይሆናል።[48] ይህም ከሰሀራ በታች ካሉ ሀገሮች አማካኝ  2.8 በመቶኛ ያነሰ ነው።[49]

ሁለተኛ-ሌላኛው የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት ወጪን ማስያ መንገድ የድህነት ልዩነትን መሰረት በማድረግ ነው። ይህም ማለት ከድህነት ወለል በታች ያለ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት እና ይህ ህዝብ ከድህነት ለማውጣ የሚያስፈልግ የገንዘብ መጠንን ታሳቢ በማድረግ የሚሰላ ነው። ይህም ታሳቢ የሚያደርገው ዜሮ አስተዳደራዊ ወጪ፣ ፣ ፍጹም የተሟላ ልየታ እና ሁሉንም ተጠቃሚዎች መድረስን ነው።

ጥቅል የድህነት ልዩነት ማለት የድህነት ልዩነት ኢንዴክስ በአጠቃላይ የህዝብ ብዛት እና የድህነት ወለል ሲባዛ ነው። በ2011 የድህነት መረጃ መሰረት የድህነት ወለል እና የህዝብ ብዛት መረጃ መሰረት (የቅርብ መረጃን መሰረት በማድረግ) ጥቅል የድህነት ልዩነቱ 7.8 በመቶኛ * 87 ሚሊዮን * 3781 ብር (አመታዊ የድህነት ወለል) ። ይህም 25.7 ቢሊዮን ብር ገዳማ ሲሆን  በሃገራዊ ጥቅል ምርት 5 በመቶ ነው። [50] ይህም ከሰሀራ በታች ካሉ ሀገሮች ማለትም 2.8 በመቶ በእጅጉ ከፍ ያለ ነው።

ሶስተኛ- ከአመታዊ ወጪ ያለው ድርሻ ሌላው የመንግስትን ቁርጠኝነት ማሳያ ዘዴ ነው። በዚህ ረገድ መንግስት ለድህነት ቅነሳ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ደሀ ተኮር ዘርፎችን[51] የለየ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአመት 70 በመቶ ወጪ ይደረግባቸዋለ። በቅርቡ ባለው ኢኮኖሚያዊ እድገት እና አውንታዊ ለውጥ በመበረታታት መንግስት በሁሉን አቅፍ እና ድሀ ተኮር የሆነ የልማት ስትራቴጂ ያለው ቁርጠኝነት በቀጣዮቹ አመታት የሚቀጥል ሲሆን የድህነትን እና የስራ አጥነትን ችግር የሚቀርፍ ይሆናል።[52]

ይሁን እንጂ ድሀ ተኮር ዘርፍ ለድሀ ድሃ ብቻ መሆኑ ይቅር እና ለድሆችም ብቻ አይደለም። ለምሳሌ በገጠር የሚካሄድ የመንገድ ስራ ለድሀ እና ለተሻሉ ጭምር የሚያገለግል ነው። ስለዚህ በጠንካራ አገላለጽ ድሀ ተኮር ዘርፎች ላይ የሚካሄዱ ወጭዎች የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ኢንቨስትመንቶች ብቻ አይደሉም። ከላይ እንደተገለጸው በአሁኑ ወቅት ታቅደው እየተተገበሩ ከሚገኙ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች የከተማ እና ገጠር ልማታዊ ሴፍትነት እንዲሁም የማህበራዊ ዋስትና ክፍያዎች ዋናዎቹ አገልግሎቶች ሲሆኑ ምን አልባትም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የማህበራዊ ዘርፍ ጥበቃ ወጪዎች የሚያሳዩ ይሆናል።

በአጠቃላይ መንግስት የማህበራዊ ጥበቃን በፋይናንስ ለማገዝ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ያሳየ ሲሆን ይህ ጥቅል ስሌት የሚያሳየው ማህበራዊ ጥበቃ በመንግስት የገንዘብ አቅም ውስጥ በቂ የሆነ ስፍራ መኖሩን ያሳያል።

**6.2 ዋነኛ የፋይናነስ ምንጭ**

የማህበራዊ ጥበቃ ወጪ ለሁሉም መንግስታት (ትልቅም ይሁን ትንሽ 'ሀብታም ይሁን ደሀ) ከአቅማቸው በላይ አይደለም። ይህም ማለት የተለያዩ አማራጮችን በማፈላለግ እንዲሁም በሀገሪቱ የገንዘብ አቅም ውስጥ ያለውን ስፍራ በማስፋት እና ሀብቶችን በማሰባሰብ የማህበራዊ ጥበቃን ፋይናንስ ማድረግ ይቻላል። ይህም የሚያካትተው 1. የመንግስትን ወጪዎችን ውጤታማ እንዲሆኑ እንደገና በመደልደል፤ 2. የታክስ ገቢን በመጨመር 3. የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንን በማስፋት እና የመዋጮ ገቢን በመጨመር 4. እርዳታና ድጋፍን በማፈላለግ 5. ብድር እና ወቅታዊ እዳዎችን በማስተካከል 6. ሁሉን አቀፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ማእቀፍ በመፍጠር (ዱራን ቫልቨርዴ እና ፓኪኮ 2012፤ ኦረቲዝ ኢታል 2015)።

አሁን ባለንበት ወቅት በማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ያለው የገንዘብ ምንጭ ሁለት መሰረታዊ ክፍሎች አሉት።

- **በመካሄድ ላይ ያሉ ኢንቨስትመንቶች፡-** በተለያዩ መንገዶች የሚተገበሩ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በማህበረሰብ አቀፍ መዋቅሮች (ለምሳሌ እድር) እና የማህበረሰብ ጥምረት ኮሚቴ እየተተገበሩ ይገኛል። ሀብትን በማሰባሰብ ረገድ የነዚህ ማህበረሰብ አቀፍ መዋቅሮች ሚና እጅጉን ጠቃሚ ነው።የግል ረጂዎች በማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ያላቸው አስተዋጽኦም ከፍተኛ ነው። የኢንቨስትመንት ማእቀፉ ወይም እቅዱ በሚዘጋጅበት ወቅት እነዚህን ምነጮች ታሳቢ ያደርጋል። የሚያደርጉትን አስተዋጽኦም ለማስላት የተለያዩ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። (ለምሳሌ እድር ባይኖር የአንድ ዜጋ የቀብር ስነስርአት ምን ያክል ወጪ ይጠይቃል?)።
- **አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች፡-** እነዚህ ኢንቨስትመንቶች የሚያካትቱት አዳዲስ ተግባራትን እና አገልግሎቶችን ሲሆን ወጭያቸውም በመካሄድ ላይ ባሉ ኢንቨስትመንቶች ላይ ይደመራል።[53]

ትክክለኛውን ወጪ ለማስላት ሁለት ተጨማሪ ክፍሎች አስፈላጊ ናቸው።

- ***መዋጮ፡-*** ይህም የመጨረሻ ተጠቃሚው በራሱ ወይም በአሰሪው አማካኝነት በእድሜ ዘመኑ የሚያደርገው አስተዋፅኦ ነው። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት ያለው የመንግስት እና ግል ድርጅቶች ማህበራዊ ዋስትና እንዲሁም የማህበረሰብ ጤና ኢንሹራንስ
- ***መዋጮ ላይ ያልመሰረተ፡-*** ይህ መንግስት ሙሉ በሙሉ ከታክስ እና ሌሎች ገቢዎች የሚከፍለው ክፍያ ነው። ለምሳሌ ማህበራዊ ጡረታ፣ የህፃናት ጥቅማጥቅሞችና የአካል ጉዳተኞች አበል ነው፡፡

### 6.3 የፋይናንስ ስትራቴጂ ሲዘጋጅ ታሳቢ ሊሆኑ የሚገባቸው ጉዳዮች

**1. በማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ ውጤታማነትን ማሳደግ፡-**

ድግግሞሽን ማስወገድ' ስርአቶችን ማጣጣም እና በምዘና መሰረት ውጤታማ ለሆኑ አገልግሎቶች ሀብት መመደብ፡፡ ይህም የገንዘብን እሴት ያሳድጋል። ለምሳሌ ነጻ የጤና አገልግሎት እና የጤና ኢንሹራንስ ድጎማ ተጠቃሚዎች ልየታን በማሻሻል ውጤታማ የሆነ የማህበራዊ ጥበቃ ለድሆች በአነስተኛ ወጪ መስጠት ይቻላል። ታሳቢ ከሚሆኑት ጉዳዮች አንዱ በአሁኑ ወቅት ለጥራጥሬ ምርቶች የሚደረገው ብር 1.6 ቢሊዮን የአመት ድጎማ ወደ የከተማ ሴፍትኔት ፕሮግራም መመደብ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም የከተማ ሴፍትኔት ፕሮግራም ድሆችን ኢላማ በማድረግ ውጤታማ እንደሚሆን ስለሚታሰብ።

2. **የፋይናንስ ምንጮችን ለማስፋት ዘለቄታዊ የሆነ ዘዴ መፍጠር፡-** የመንግስት በጀት የፌደራሉን መንግስት ብቻ ታሳቢ ያደረገ ሳይሆን የክልል/ወረዳ እና ቀበሌ እንዲሁም የህብረተሰቡን ሀብት ጭምር ያካትታል። መንግስት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ለማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይበረታታል። ለንግድ ተቋማት የማህበራዊ ሀላፊነት መወጫ አንዱ መንገድ ሆኖ ይቀርባል። ይህም የሚተዳደረው በሠ.ማ.ጉ.ሚ (ፌዴራል) እና ሰ.ማ.ጉ.ቢ (በቢሮዎች) ነው። አካባቢያዊ ሀብቶችን ማሰባሰብ በማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረት በአንዳድ ክልሎች ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል።[54]

3. **ጥምር ድጋፍ**/ዘርፍ ለ ዘርፍ፤ ክልል ለ ክልል የሚያደርጉት ድጎማ/፡- የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ የሀብት ፍላጎት የሚወሰነው በድህነት እና የችግር ተጋላጭነት ስፋት እና ጥልቀት እንዲሁም ቀበሌዎች/ወረዳዎች ራሳቸውን በራሳችው ፋይናንስ የማድረግ ውስንነታቸው ነው። ስለሆነም ጥምር ድጋፍ አስፈላጊ ይሆናል። የተወሰነ የማህበረሰብ ክፍል አስተዋጽኦ የሚያደርግ ሆኖ አገልግሎቱን የማይጠቀም ወይም በከፊል ብቻ የሚጠቀም ከሆነ ገንዘቡ ችግሩ በስፋት በሚታይበት ቦታ ላይ ይውላል። የጤና እና ተሽከርካሪዎች ኢንሹራንስ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። አንድ የጤና ኢንሹራንስ ባለቤት ወይም የመኪና ኢንሹራንስ ባለቤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ አደጋ ካልደረሰበት የኢንሹራንስ ተቋሙ ለሌላ መዋጮው አነስተኛ ለሆነ ባለኢንሹራንስ ገንዘቡን ማወል ይችላል።

4. **የስነ ህዝብ አወቃቀር ለወጥ**፡- የስነ-ህዝብ አወቃቀሩን ስንመለከት ሰራተኛ የሆነ የህዝብ ክፍል እየጨመረ ስለሆነ ሰፊ የስራ እድል ከተፈጠረ የታክስ መሰረቱን ማስፋት ይችላል። የተሻሻለ የጤና ተደራሽነት ማለት ደግሞ የአረጋውያን ቁጥር ሲጨምር ለጤና ኢሹራንስ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ስርአት በመቀየስ አረጋውያን በሚሆኑበት እና መስራት በማይችሉበት ጊዜ

የጤና አገልግሎት የሚያገኙበትን እድል መፍጠር ነው። በማህበራዊ ጥበቃ ፋይናንስ አደራረግ ውስጥ ጠቃሚ የሆነ ታሳቢ ጉዳይ ነው።

5. የኑሮ ሁኔታ **ማጣሪያ ስርአት**:-ተጋላጭ የሆኑ ግለሰቦች ዝርዝር ቢኖረንም፤ ሁሉም ግለሰቦች አፋጣኝ የሆነ ድጋፍ ላይፈልጉ ይችላሉ። ለምሳሌ ጡረታ የወጡ የመንግስት ሰራተኞች የማህበራዊ ዋስትና ያላቸው ሲሆን የግል ድርጅቶች ሰራተኞች የማህበራዊ ዋስትና መዋጮ ጀምረዋል። የማህበራዊ ጥበቃ ስርአቱ በመጀመሪያ ደረጃ ትኩረት የሚያደርገው ምንም አይነት የገቢ ምንጭ ለሌላቸው ነው።የተወሰነ የገቢ ምንጭ ላላቸው የሚያገኙት ገቢ ፍላጎታቸውን ለማሟላት በቂ መሆንና አለመሆኑን የሚያጣራበት ስርአት መፍጠር አለበት።

## 6.4 ለማህበራዊ ጥበቃ የፋይናንስ መሰረት ለመፍጠር ሊወሰዱ የሚገባ ቀጣይ እርምጃዎች

ቀጣዩ እርምጃ  የሚከተሉትን ታሳቢዎች ያካተተ የተግባር/ኢቨስትመንት እቅድ ማዘጋጀት ነው፡-

- በብሄራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ እና በዚህ ስትራቴጂ እንዲሁም በአምስቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ዙሪያ በአሁኑ ጊዜ እየተከናወኑ የሚገኙ የማህበራዊ ጥበቃ ኢንቨስትመንቶችን መለየት
- በዚህ ስትራቴጂ በተገለጸው መሰረት አዳዲስ የማህበራዊ ጥበቃ ኢንቨስትመንቶችን ወጪ ማስላት እና በተግባር እቅዱ ላይ ማብራራትና ለእያንዳንዱ ትኩረት መስክ ወጪ ማስላት እንዲሁም በእያንዳንዱ ክልል ለእያንዳንዱ የትኩረት መስክ ወጪ ማዘጋጀት
- በእያንዳንዱ ክልል ከተለያየ የፋይናንስ ምንጮች ሊገኝ የሚችለውን ጠቋሚ የገንዘብ መጠን ማዘጋጀት እና የፋይናንስ ክፍተቱን መለየት
- በተለየው የፋይናንስ ክፍተት መሰረት የቅደም ተከተል ውሳኔ መስጠት የማስፋፍያ ፍጥነትን መወሰን እና  በዚህ ስትራቴጂ የተገለጹ አገልግሎቶች ቅደም ተከተልን መለየት
- በተለየው የክልሎች የገንዘብ አቅም ልዩነት መሰረት ተገቢ የሆነ የጥምር ድጋፍ የተግባር እቅድ እና ዘዴ ማዘጋጀት
- ለዘርፉ ተገቢ የሆነ የፋይናንስ አስተዳደር ስርአት መዘርጋት፤ የተገኙ ሀብቶች በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ እና ወጪ ቆጣቢ በሆኑ አገልግሎቶች ላይ መመደብ ናቸው፡፡

### አባሪ 1 ቁልፍ ባለድርሻ አካላት

**መግቢያ**

ሦላሳ ስድት ባለድርሻ አካላት ስልጣንና ተግባራት መስረት በማድረግ ከማህበራዊ ጥበቃ ጋር የተያያዙ እንደ ልማታዊ ሴፍትኔት፣ካሽ ትራንስፈር ፣የማህበራዊ ዋስትና ክፍያ ነጻ ህክምና አገልግሎት ተለይቷል ፡፡ ከነዚህም አብዛኞቹ (25) የመንግስት ተቋማት፡፡

